ፍኖተ

# ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ማክሰኞ ሚያዝያ 16 ቀን 2004 ዓ.ም. ዋጋ ብር 6.00

2ኛ ዓመት ቅጽ.2 ቁ.39

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!



## የምንታገለው የመደብ ክፍፍልና አድሏዊነትን ለማስቀረት ነው

አቶ ብሩ ብርመጂ

6

# የኃይማኖት ነፃነትና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሁሉንም የመቆጣጠር አባዜ ግጭት



## በኦሮሚያና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ግጭት 22 ሰው ሞተ

በኦሮሚያ ክልልና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ድንበር ላይ ሰሞኑን በተፈጠረው ግጭት 22 ሰው ሲሞት በርካታ ሰዎች ቆስለው በለቀምት ሆስፒታል በመታከም ላይ መሆናቸው አካባቢው ነዋሪዎች ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎች ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት ከሆነ "በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ኦሮሚያ ዞን ልዩ ሥፍራው ጊዳ ኪራሞ እና ጊዳ አያና በተባሉ ወረዳዎች የተነሳው ግጭት መንስዔ አቤንቱ፣ ቄሎና ዋስኪ የተባሉ አካባቢዎች የይገባኛል ጥያቄ ነው፡፡ "ከዚህ በፊት በ2000 ዓ.ም የተፈጠረውና ለ200 ሰዎች የህይወት መጥፋት፣ለበርካቶች መቁሰልና መፈናቀል ምክንያት ከነበረው ግጭት የቀጠለ ነው፡፡" ሲሉ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የአካባቢው ነዋሪዎች ጨምረው እንደሚሉት "ለዘመናት በጉርብትና በሠላም ይኖር የነበረው ሕዝብ መሀከል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተፈጠረ ያለው ግጭት የኢህአዴግ የዘር ፖለቲካ የወለደው ነው፡፡" ብለዋል፡፡

ወደ ገፅ 16 ዞሯል

## ክቡር ሆይ እኔ የአንድ እምነት እና አንድ ሀገር አራማጅ ነኝ

ግርማ ሠይፉ ማሩ

5

## የአርበኞች ማህበር በሙስና ተምሷል ተባለ

11

# መንግሥት በሙስሊሙ ማህበረሰብ እንቅስቃሴ መደናገጡን አንድ የመንግስት ምስጢራዊ ሰነድ አጋለጠ

-ሰነዱ ለጥቂት ከፍተኛ ባለስልጣናት ብቻ የተሰጠ ነው ተብሏል
-በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የአልቃይዳ ሴል ተገኝቷል ብሏል

መንግሥት በከፍተኛ አመራሮች ደረጃ "የሰላምና ህገ-መንግስቱ ዙሪያ በሀገራዊ መግባባት መፍጠር የዜጎችና የመንግሥት መብትም፣ግዴታም ነው!" በሚል ርዕስ እየተወያየበት እንደሆነ ምንጮቻችን ጠቆሙ፡፡

ወደ 8 ዞሯል

## በጋሞ ጐፋ ዞን ለተቃውሞ የወጡ ሰዎች በታጣቂዎች ተገደሉ

በጋሞ ጐፋ ዞን መለኮዛ ወረዳ ለሀ ከተማ በተነሳ ግጭት አንድ ሴት እና አንድ ወንድ በታጣቂዎች መገደላቸውን የደቡብ ክልል ምንጮች ለፍኖተ ነፃነት አስታወቁ፡፡

የአንድነት የደቡብ ቀጠና ኃላፊ የሆኑት አቶ ዳንኤል ሺበሺ ለፍኖተ ነፃነት እንዳስታወቁት ግጭቱ የተከሰተው ሰኞ ሚያዝያ 8 ቀን 2004 ዓ.ም ሲሆን የግጭቱ መንስኤ ህዝቡ ከማንነት ጥያቄና ከመልካም አስተዳደር እጦት ጋር በተያያዘ ባነሳው ተቃውሞ ነው፡፡ ከአካባቢው

ወደ 16 ዞሯል

## ዴሞክራሲን ማምጣት ያቃተው ኢህአዴግ በቁሳዊ "ልማት" አፍኖ ሊገድለን ነው

ዶ/ር ኃይሉ አርአያ

3

## አገዛዙ የተዘፈቀበት መረጃ የ"መጋገር" ልክፍትና "ድህነት ቀንሷል" ዲስኩር

4



ሰለሞን ስዩም
era4st@yahoo.com

በአለም ወቅታዊ ሁኔታ የኃይማኖታዊነት መነቃቃት እየታ መሆኑ እያስማማ መጥቷል፡፡ ነገር ግን የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ «አንድ ሀገር አንድ አይዲዮሎጂ» በመሆኑ ጣልቃገብነቱ ለወቅቱ ተቃዉሞ ዳርጎታል የሚለዉ ሰለሞን ስዩም ኢህአዴግ የኃይማኖት ጉዳይን እንደ ዋዛ ማየቱ ዋጋ ያስከፍለዋል ይላል፡፡

# የኃይማኖት ነፃነትና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሁሉንም የመቆጣጠር አባዜ ግጭት

ሳሙኤል ሀተንግተንን ልዩ የሚያደርጋቸው አብዛኛዎቹ ተሰሚነት ያላቸው የፖለቲካ ተንታኞች ዘመናዊነት ላይ ከጣሉት ተስፋ በተቃራኒ «የኃይማኖት ጉዳይ ይበልጥ እየከረረ ይሄዳል» የሚለው አቋማቸው ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ተንታኞች በተለይ ከሉላዊነት (Globalization) የተነሳ ባህልም ሆነ ሀይማኖት የመበረዛቸው ዕድል ሰፊ በመሆኑ የግጭትም ሆነ የአክራሪነት ምንጭነታቸው ያከትማል የሚለው ሀሳብ ገዥ ሆኖ ነበር፡፡ ሚካኤል ጌብ የተባሉ የኃይማኖትና ስልጣኔ አንጻራዊ ተግባቦት አጥኚ "ሀይማኖት የቅድመ አያቶች መለያ ብቻ የሚሆንበት ዘመን ደርሷል" ሲሉ ፅፈዋል፡፡ ዶ/ር ሚካኤል ጌብ "Religion and Civilization a Comperative Study" በተባለ ጥናታቸው "በዚህ በኩል ያለን መረጃ ቢኖር የኢ-አማኒያንና አምላክ የለሾች (Atheist) ቁጥር በ1900 ዓ.ም ከነበረበት 0.2 በመቶ በ1980 ዓ.ም ወደ 20.9 በመቶ ማደጉ ነው" ሲሉ ስልጣኔ ሀይማኖቶችን ከፉኛ መፈታተኑን ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡ በዚያ ላይ ከቋንቋ ተናጋሪዎች መረጃ ይልቅ የተለያዩ ሀይማኖት ተከታዮች መረጃ ተለዋዋጭ መሆኑን በማስረዳት የሀይማኖታዊነት መፃኢ ጊዜ ብሩህ እንደማይሆን ለማስገንዘብ ጥረዋል፡፡

የዚህን ተቃራኒ የሚተነትኑ ሳሜኤል ሀቲንግተን "የ20ኛው ክ/ዘ/ማብቂያ የሀይማኖት ከፍተኛ መነቃቃት በሉል ደረጃ ጎልቶ የወጣበት ነው" ሲሉ ይከራከራሉ፡፡ ሀቲንግተን ይህንን "የሀይማኖት ንቃት መጨመር እና የአክራሪዎች ማቆጥቆጥ የታየበት ነው" ይላሉ፡፡ ሌላው የዚህ ዘርፍ አጥኚ ሬጂስ ዴብራይ (Regis Debray) የሀይማኖት መነቃቃት ከሁሉም የህይወት ዘዬ የሚመጣ መሆኑን አውስተው በተለይ ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሱት "ማህበራዊ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ እገዛና ምሪት" የሚፈልጉ ሲሆን ይህን በመስጠት ደግሞ የኃይማኖት ተቋማትን የሚስተካከል ያለመኖሩን ያወሳሉ፡፡

ከ "Juxtaposition" እስከ "Islam is a solution"

ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ በሚያዝያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም የፓርላማ ውሏቸው በኢትዮጵያ በክርስትያኑና ሙስሊሙ መካከል የነበረውን የአብሮነት ታሪክ ሲያወሱ "የነበረውን የአገዛዙን አድልኦ ሳንረሳ" የሚል ሀረግ በተደጋጋሚ ይጠቀሙ ነበር፡፡ የአክሱም ስልጣኔ ሁለት የመውደቂያ ምክንያቶች ይቆጠርለታል፡፡ ውስጠኛ የሚባለው ምክንያት የቤጃ ህዝብ አመፅ ሲሆን ሁለተኛው ግን ከእስልምና መወለድ ጋር ይያያዛል፡፡ በዚህ ሁኔታ እንኳን ለውጭ ሀይሎች ስጋት ሲሆኑ በውስጣቸው በነበራቸው መከፋፈል የማንም ሀይሎች መጫወቻ የነበሩት አረቦች ከነዳጅ በፊት ዋነኛ የጥንካሬ ምንጫቸው እስልምና ነበር፡፡ አረቦች በእስልምና አንድ ከሆኑ በኋላ የአክሱምን ገናናነት ያስገኘውን የቀይ ባህር ንግድ ለመቆጣጠር አፍታም እንዳልፈጀባቸው የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ፡፡ ከዚያን ዘመን ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻል ሁኔታ በወቅቱ ክርስትያኖች በሚመሯት ኢትዮጵያ ሙስሊሞችን እንደ አደጋ መቁጠር የማይስተዋል (Unconscious) ስነ ልቡና መሆኑ ይነገራል፡፡

በአፄ ዮሐንስ ርዕዮተ ዓለም ውስጥ "እስልምና የሚባል ነገር . . . ከቶም ሥፍራ አልነበረውም" የሚሉት ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ "ስለሆነም በሙስሊሞች ላይ፣ በተለይ በፈረደባቸው የወሎ ሙስሊሞች ላይ የጥፋት ሠይፉን መዘዘ" ይላሉ፡፡ በግብፅ የእስልምና መስፋፋትን በተመለከተ የተፃፉ ሰነዶች እንደሚያስረዱት ሙስሊም ያለመሆን ንብረት የማውረስ መብት የሚያሳጣ፣ በህይወት የመኖር መብትና ደህንነት የሚነሳ ነበር፡፡ ስቃዩን ከፍ የሚያደርገው ደግሞ አንድ ሰው ክርስትያን ለመሆን መሬቱን ባብዛኛው ማጣቱ ብቻ ሳይሆን ክርስቲያን ለሆነበት ተጨማሪ ግብር መክፈሉና ቄስ / የክርስትና ሀይማኖት መምህር ከሆነ ደግሞ ክርስትያን በመሆኑ ከሚከፍለው ውጭ ተጨማሪ ግብር መጠየቁ ነበር፡፡ ፈረንሳይ ለጋሲዮን በሚገኝ መስጂድ ፍኖተ ነፃነት የግብፁን ታሪካዊ ደራ በማስረዳት የጠየቀቻቸው ዮሱፍ አሊ (ስማቸው የተቀየረ) ሁኔታውን በሁለት መልኩ ያስረዳሉ፡፡ እንደ አለማቲ ዮሱፍ አሊ አባባል በግብፅ ግፍ አድራሾቹ ሙስሊሞች ሲሆኑ ተቀባዮቹ ደግሞ ክርስትያኖቹ ነበሩ፡፡ በኢትዮጵያ የዚህ ተገላቢጦሽ እውነት መሆኑን የሚያስረዱት ዮሱፍ አሊ "በወሎ የነበሩ ክርስትያኖች ሀይማኖታችሁን ለውጡና ክርስትናን ተቀበሉ፤ አለበለዚያ መሬትና ንብረታችሁን አስረክቡ" መባላቸውን በማስታወስ "ዛሬም በሌላ መልኩ የሚጫንብንን የአስተሳሰብ ቅያስ ሳስብ ሰቆቃችን ዘለዓለማዊ ይመስለኛል" ይላሉ፡፡ ፕ/ር ባህሩ ይህንን ሁኔታ "አንዳንዶቹ ለይስሙላ ተጠምቀናል ብለው ውስጥ ውስጡን ግን የእስልምና ሀይማኖታቸውን ቀጠሉ፤ ቀን ለእግዚአብሔር ማታ ለአለህ መፀለይ (Juxtaposition) ያዙ" በማለት ይገልፃሉ፡፡ ፕ/ሩ በተለይ ሁኔታውን አስመልክቶ የተነሳውን አመፅ ለማስቆም አርዓያ ሥላሴ ዮሐንስና ምኒልክ ከፍተኛ ግፍ ማካሄዳቸውን ዘርዝረዋል፡፡

ሁለተኛው አተናተናቸው ይህ የሚሆንበት የጊዜ ልዩነት ለንፅፅር የማይቀርብ መሆኑን በማስረዳት ነዉ፡፡ ዩሱፍ «በዚህ ዘመናዊ አለም እንዲህ አይነት ጣልቃገብነት በየትኛዉም ሀይማኖት መታየቱ የሚኮነን ነዉ» ይላሉ፡፡

አሁን በሆነው የአለም አቀፍ እስልምና መነቃቃት በሙስሊሙ ዘንድ አንድ ጊጤ (focus) መፈጠር ችሏል፤ "እስልምና መፍትሄ ነው"(Islam is a solution) የሚል» የሚሉት ዩሱፍ አሊ «ቅዱስ ቁረአን የጅብሪል እንጅ የአላህ ቃል አይደለም የሚል ሀይማኖት ለመስበክ መንግስት ለምን እንደሞከረ አልገባኝም» ይላሉ፡፡

የሃይማኖት ዜግነቱ ወዴት ነው?

ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረ ወዲህ ህገ መንግሥቱ ሦስት ዋና ዋና ሀይማኖታዊ ጉዳዮችን አንስቷል፤ ማንም ሰው የፈለገውን ኃይማኖት መከተል መቻሉን፤ ኃይማኖትና መንግሥት የተለያዩ መሆናቸውና መንግሥት በኃይማኖት ሀይማኖት በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገቡ፡፡ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ነገሮች የተጠበቁትን ሳይመስሉ ቀሩ፡፡ በተለይ ከሉአላዊነት ጋር በተያያዘ ቀድመው "ሀገራዊ ዜግነት" የነበራቸው ሁለቱ ዋነኛ ኃይማኖትቶች አለማቀፋዊ ይዘት መያዝ ጀመሩ፡፡

የኢትዮጵያ እስልምና አመጣጥ ከሌሎቹ የትኛውም እስልምና ከተስፋፋባቸው አካባቢዎችና ሀገራት በእጅጉ ይለያል፡፡ በተለይ በሰሜን አፍሪካ እስልምናውም አረባዊነቱም በመስፋፋታቸው ተቀባዮቹ ህዝቦች ኃይማኖቱንም አረባዊ ባህሉንም መቀበላቸው ይታወቃል፡፡ ወደ ኢትዮጵያ የገባው እስልምና ንፁህ ስነ መለኮታዊ አስተምህሮት ብቻ ነው፡፡ ከዚያ ውጭ ያለው ኃይማኖታዊ ባህል ኢትዮጵያዊ መሆን ችሏል፡፡ ነገር ግን "ከዘመናት በኋላ የቴክኖሎጂ መስፋፋት ሌሎች የእስልምና አስተምህሮዎችን እንዲሁም ሀይማኖታዊ ባህሉ ቤታችን ድረስ መጣልን" ይላሉ ዩሱፍ አሊ፡፡ እንደ እርሳቸው አባባል «ማንኛውም ሰው የአረብ ቻናሎችን ከፍቶ ኃይማኖታዊ ስነመለኮቱንም ኃይማኖታዊ ባህሉንም መከታተልና መውረስ ይችላል ይላሉ፡፡ መንግሥት "ነባር እና አዲስ" ለማለት የተገደደውም በዚሁ ምክንያት መሆኑ በስፋት ይነገራል፡፡ አንዳንድ የዘርፉ ተንታኞች በዚህ የተቀራረበችና ድንበር የለሽ አለም ማንኛውም ነገር ዜግነቱ አለም አቀፋዊ እየሆነ መምጣቱን ያወሳሉ፡፡

የቅቡልነት ፍላጎትና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የመቆጣጠር አባዜ ግጭት

የኢህአዴግ መንግስት ከኦርቶዶክስ ክርስትና ውጭ ላሉት የሀይማኖት ተከታዮች ውለታ በመዋል ቅቡልነቱን ያረጋግጥለት ዘንድ ይፈልግ ነበር፡፡ በህገ መንግሥቱ የተካተቱትን ከላይ የተጠቀሱ ሦስት ሀይማኖታዊ ድንጋጌዎችን የምድራችን አዲስ ግኝት እስኪመስሉ ድረስ ስብኳቸዋል፡፡ ፕ/ር መዲሃኔ ታደሰ "AL-ITTIHAD: Political Islam and Black Market in Somalia" በተባለ መፅሃፋቸው ከ1983-1990 ድረስ የነበረውን የኢህአዴግ መንግሥት ሁኔታ ከደርግ ተቃራኒ ብቻ ለመቆም የተደረገ "መርህ ያልገዛው የሀይማኖት ነፃነት ነበር" ይላሉ፡፡ ደርግ የወረሳቸው የኃይማኖት ተቋማቱን ህንፃዎችም መልሷል፡፡ ይህ ግን ከምዕመናኑ ይሁንታ ለማግኘት እንጅ ውሎ አድሮ ሀይማኖቱን መቆጣጠር እንዳለበት ሳይዘነጋ መሆኑን ክፍሉ ቸሬ የተባሉ ፀሐፊ ያትታሉ፡፡ አንዲት በህትመት ላይ የማትገኝ ጋዜጣ «የኢህአዴግን የመንግሥትና ኃይማኖት ግንኙነት ታሪክ የመጀመሪያ ወሳኝ እርምጃም በደርግ ይሁንታ ተመርጠዋል፤ ደርግንም ይደግፋሉ የሚባሉትን ፓቲርያርክ ማርቆሪዮስ ከመንበራቸው መውረድ ነው፡፡ ኢህአዴግ ንፅህናውን ለማሳየት ቢደክምም ከእስር ተፈተው "ኃይማኖተኛ" የሆኑት የቀድሞ ጠ/ሚ/ር ፓቲሪያርኩ ሲባረሩ መፈረማቸውን አምነዋል፡፡ በሁለቱም ዋነኞቹ ኃይማኖቶች ያሉ አማኞች የኢህአዴግን የሀይማኖት አመራር ቁጥጥር ፍላጎት የተገነዘቡት ወዲያዉ ነበር፡፡ በሌላ መልኩ ኢህአዴግ በወቅቱ ሀገሪቷን በማረጋጋት ሥራ ተጠምዶ ስለነበር ከየትኛውም የሀይማኖት ተቋም ተቃውሞ እንዲመጣበት ባለመፈለጉ ጊዜያዊ ነፃነታቸውን መስጠት ይመርጥ እንደነበር ክፍሉ ቸሬ ያትታሉ፡፡

አብዮታዊ ዴሞክራሲን የሚያቀነቅነው ኢህአዴግ "አዲስቷ ኢትዮጵያን ለመገንባት ከዚህ ቀደም የተመሠረተችበትን ኃይማኖታዊና ባህላዊ መሠረት መናድ ተፈጥሯዊ ግዴታው ሆነ፡፡ በአብዮታዊነት የታወረው ኢህአዴግ ይህንን ሲያደርግ በተለይ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ተይዞ የቆየውን የሀገሪቷን የረዥም ዘመን የመንግሥትነት ፅንሰ ሀሳብ በመንካቱ ይህንን ታሪካዊ የመንግሥትነት ፅንሰ ሀሳብ የሚደግፉ አካላት ኢህአዴግን የኢትዮጵያ አንድነት አደጋ አድርገው እንዲመለከቱት ሆነ፡፡ ደርግ ኢህአዴግን ስወቅስበት የነበረው አስገንጣይነት፣ ለታሪክ ክብር ማጣትና ባንዲራን ማቃለል ፍንትው ብሎ ታየ፡፡

ክፍሉ ቸሬ «እንግዲህ ይህ ነው ኢህአዴግን ከሲኖዶሱ በተጨማሪ ከማህበረ ቅዱሳን ጋር የሚያወዛግበው» ይላሉ፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት ማህበረ ቅዱሳንን በኃይማኖት አክራሪነት ከመክሰሱም በላይ "ኢትዮጵያ የክርስትያን ደሴት ናት" የሚል ሀሳብ ያራምዳሉ ሲል ከሌሎች እምነት ተከታዮች ጋር ለማቃረን መሞከሩን ክፍሉ ቸሬ ይሞግታሉ፡፡ ጠ/ሚ/ሩ በፓርላማ ውሏቸዉ «አንድ ሀገር አንድ ኃይማኖት እያሉ ያራግባሉ » ብለዋል፡፡ እንደ ተንታኙ ኢህአዴግ ከሲኖዶሱ ይሁንታን ቢያገኝም የኢትየጵያ ታሪክን ከነሙሉ ክብሩ ከኋላ ጀምሮ በመተንተንና የቤተክርስቲያኒቱን አስተዋፅኦ የሚተነትነው "ማህበር ቅዱሳን" የ"የነፍጠኞች፣ አፄያዊና ደርጋዊ" መጠራቀሚያ እንደሆነ ማመኑን ይናገራሉ፡፡ በተቃራኒው ሙሉ በሙሉ ግልፅ ያልሆነው ይህ የኢህአዴግ አቋም በምርጫ 97 ክርክር ወቅት በወቅቱ የአቅም ግንባታ ሚኒስትር አቶ ተፈራ ዋልዋ ቤተክርስቲያና የነፍጠኞች መሸሸጊያ እና በታሪክም ብዙ ስህተት መፈፀሟን መናገራቸው የኢህአዴግን ዓለማ ግልፅ ማድረጉ ይነገራል፡፡ በዚህ ወቅት እስከ መጨረሻው እድሉን ለመጠቀም ሙስሊሙና ፕሮቴስታንቱ ሲሯሯጡ በሌላ በኩል ቤተ ክርስቲያኒቱ "ነፃነቱን ለመጠቀምም ሳትችል ራሷን በተከላካይነት ቦታ ማግኘቷን" አንድ የማህበረ ቅዱሳን አመራር ይናገራሉ፡፡

በወቅቱ በኢትዮጵያ ረሃብና ጦርነት በተከታታይ በመከሰታቸው መንግሥት "አትቃወሙኝ እንጂ እደግፋችኋለሁ" የሚለውን የመጀመሪያ ፖሊሲ ተቋማቱ የተለያዩ እርዳታዎችን ማስተባበርና ህብረተሰቡን የማሳመን ሥራ እንዲሄዱ አደረጋቸው፡፡ በወቅቱ ሌላው ውስብስብ የነበረው የ "አልነጃሺ" ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ንጉሥነት ሲሆን መንግሥት ከጉዳዩ ራሱን ማራቁ "ለሙስሊሞች ታደላለህ፤ የሀገሪቷ ታሪክ ሲበረዝም ከቁብ አትቆጥርም" የሚል ወቀሳዎች እንዳስነሱ ይነገራል፡፡

እስከ ምርጫ 97 የሀይማኖት መሪዎችን ብቻ በመያዝ ተወስኖ የነበረው ኢህአዴግ ወደ ምዕመናን መውረድ እንደሚገባው አምኗል፡፡ በመሆኑም ከምርጫ ቅስቀሳ ጀምሮ ሙስሊሞችን ለብቻ ያነጋገረው ኢህአዴግ በክርስቲያኖቹ ላይ "የግራኝ ድንጋጤ" (Gragn's Syndrome) እና የግብፅ ጠላትነትን ማስታወሱን አንድ ታዛቢ ተናግረዋል፡፡

የኃይማኖት አክራሪነት ኢትዮጵያን ያሰጋታል?

በቅርቡ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ዶ/ር ሽፈራው ተክለ ማሪያም "ዶክትሪናቸውን ለመቃወም አይደለም፤ በህቡዕ በመደራጀት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ግን ፀረ ህገ-መንግሥት ነው" ሲሉ የወቅቱን የሙስሊም እንቅስቃሴ ኮንነዋል፡፡ ሚኒስትሩ የደም መፋሰስ ባስከተለ መልኩ የወሃቢ ሙስሊሞች መስጊዶችን መውረራቸውን ለማስረዳት በሀረር፣ ጅማ፣ ወለጋ፣ ኢሉባቦር እና ባሌ ደርሰዋል ያሏቸውን ግጭቶች አብራርተዋል፡፡ ሚኒስትሩ የመንግሥት ጣልቃ መግባትን ከመከላከል ይልቅ የወሃቢ ሙስሊሞቹ ሁኔታ ሀገሪቷን ወደ ቀውስ የሚከት በመሆኑ መንግሥት ጣልቃ ለመግባት መገደዱን መስክረዋል፡፡

የፌደራል ጉዳዮች የወሃቢ አክራሪዎች በረመዳን ፆም ወረቀት በድብቅ አስራጭተዋል ያላቸው ፓምፍሌት በማሰራጨት ወሃቢ ያልሆኑ ሙስሊሞች ላይ ጭምር መቀስቀሳቸውን ይፋ አድርጓል፡፡ ፍኖተ ነፃነት ያገኘችው "በዲናችን እንፅና!!" የሚል በራሪ ወረቀት ሲሆን "አህባሽ" የተባለው መጤ ሀይማኖት ብዙ የእስልምና አስተምህሮዎችን እንደሚፃረር በመግለፅ ላለመቀበል እንደተዘጋጁ የሚገልፅ ነው፡፡ ፕ/ር ሀጋይ ኤርሊች "እስልምና ለኢትዮጵያ አደጋ አለመሆኑን መገንዘብ አለብን» ይላሉ፡፡ ነገር ግን አንዳንድ የዘርፉ ምሁራን «ሀይጋ የአህባሽ አቀንቃኝ በመሆኑ ለዘብተኝነት ይመጣል በሚል ነዉ» ይላሉ፡፡

ነገሩ እንዲህ ነዉ

የመንግስት የሀይማኖት አማካሪዎች አንድ ነገር ግልፅ ማድረግ አለባቸው፡፡ የሀይማኖት ጉዳይ

ወደ 12 ዞሯል

# ዴሞክራሲን ማምጣት ያቃተው ኢህአዴግ በቁሳዊ "ልማት" አፍኖ ሊገድለን ነው

ዶ/ር ኃይሉ አርአያ

ሰውየውን አቶ ሀብታሙ እንበለው:: የፈጠራ ስም ነው:: አቶ ሀብታሙ እንደ ሰሙ ሀብታም ነጋዴ ነው:: ትዳር የለውም:: ቤተሰቦቹ ትዳር ካልመሠረትክ እያሉ ይጨቀጭቁታል:: አቶ ሀብታሙ አንድ መሠረታዊ ችግር አለበት:: ማፍቀር አይችልም:: ፍቅር የሚባል ነገር ፈጽሞ አልፈጠረበትም:: የሚገርመው ታዲያ ሰዎች በተለይም ሴቶች እንዲፈቅሩት ይፈልጋል::

የሴት ጓደኛ ሲይዝ እንዲወደድ ካለው ጉጉት የተነሳ በገንዘብ፣ በጌጣጌጥ፣ በተለያዩ ገጸበረከቶች ያጥለቀልቃቸዋል:: ፍቅርና አክብሮት ግን አይሰጣቸውም፤ ስለሌለው:: ራሳቸውን የሚያከብሩና ከግንኙነቱ ቁምነገር እንዲወጣ የሚጠብቁ ሴቶች ከእሱ ጋር ብዙም አይቆዩም:: እማይሆናቸው መሆኑን ሲገነዘቡ ትተውት ይሄዳሉ:: ታዲያ የፍቅር መካኑ አቶ ሀብታሙ ደግሞ ይህን ሁሉ እያደረግሁላቸው ለምንድን ነው የማይወዱኝ? ለምንድን ነው ትተውኝ የሚሄዱት? እያለ ይበሳጫል:: ፍቅር በገንዘብ፣ በጌጣጌጥ፣ በተለያዩ ስጦታዎች፣ በየውድ ሆቴሎች በግብዣ በማንበሽበሽ፣ በውድ መኪና በማንሸራሸር እንደማይገኝ አልተረዳውም:: ፍቅር የሚገኘው በፍቅር ብቻ እንዲሆነ አላውቀውም:: ፍቅርን በፍቅር መግዛት እስካልቻለ ድረስ እውነተኛና ዘላቂ ጓደኛ አያገኝም::

አቶ ሀብታሙ የፈጠራው ሰውና በእውን ያለው የኢህአዴግ መንግሥትን የሚያመሳስላቸው አንድ ባህሪ አለ:: ሁለቱም መውደድ ወይም ማፍቀር አይሆንላቸውም:: በሰውና በሰው መካከል ማፍቀር ማለት የበርካታ "ንጥረ ነገሮች" ኬሚስትሪ ነው:: ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው:- ለዚያ ሰው በጎ ማሰብና፣ መመኘት ያንሰው ማክበር፣ ማመን፣ መንከባከብ፣ ማስደሰት ከራስ አብልጦ ማየት፣ እንዳይከፋ መጠንቀቅ ናቸው::

በሕዝብና በመንግሥት መካከል መውደድ ወይም ፍቅር ለመኖሩ መገለጫው የዴሞክራሲ መኖር ነው:: አንዱና ዋናው የዴሞክራሲ መገለጫ ነፃነት ነው:: ነፃነት ማለት ማሰብ የፈለጉትን ማሰብ መቻል፣ ማድረግ የፈለጉትን ማድረግ መቻል እንዲሁም መሆን የፈለጉትን መሆን መቻል ማለት ነው:: የእነዚህ መቻሎች ገደብ የሌላው ሰው ነፃነትና የህብረተሰብ ደህንነት ነው:: የዚህ ዓይነት ነፃነት ያለበት የመንግሥትና የሕዝብ ግንኙነት ጥሩ የመውደድ ወይም የማፍቀር መሠረት አለው:: ሌሎች ይህን መሠረት ከሚያጠናክሩ ነገሮች ዋናዎቹ የፍትሕ መኖር፣ የግልጽነት መኖር፣ የሕግ የበላይነት መኖር፣ ከሙስና የፀዳ አስተዳደር መኖር፣ የነፃ ፕሬስና ነፃ ሲቪክ ማህበራት መኖር የነፃና ፍትሐዊ ምርጫ መኖር ናቸው:: እነዚህ ነገሮች የሉም:: አሉ ከተባለ ደግሞ ከቃልና ከወረቀት ያለፉ አይደሉም:: እነዚህ ነገሮች ከሌሉ ወይም ከቃልና ከወረቀት ያላለፉ ከሆኑ የኢህአዴግ መንግሥት የሕዝብን መውደድ ወይም ፍቅር መግዛት የሚያስችሉ ባህሪያት የሉትም ማለት ነው:: እውነታውም ይኸው ነው:: በአጭሩ የኢህአዴግ መንግሥት ዴሞክራሲ በተግባር የማምጣት ችሎታ የለውም:: የዴሞክራሲ መሀን ነው ማለት ይቻላል::

የኢህአዴግ መንግሥት አጣብቂኝ በአንድ በኩል በሕዝብ እንዲወደድ፣ እንዲመረጥ መፈለጉ፣ በሌላ በኩል እንዲወደድ፣ በዘረፋ ሳይሆን በፍላጎት እንዲመረጥ የሚያስችሉት ባህሪያትን አለመያዙና ባዶ መሆኑ ነው:: ይህንን ዴሞክራሲን ለማምጣት አለመቻል ባዶነቱን ወይም መሀንነቱን ለማካካስ ሌት ተቀን የሚጥረው በ "ልማት" ነው፤ ያውም በቁሳዊ ልማት:: ስለዚህ ሰፊ የቁሳዊ ልማት ፕሮግራም ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ ነው:: መንገድ ዘረጋሁላቸሁ፣ የጤና ተቋማት ትምህርት ቤቶች ገነባሁላችሁ፣ የተማሪዎችን ቁጥር አሳደግሁላችሁ፣ የባቡር መሥመር ዘረጋሁላችሁ ነው እያለን ነው:: የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በሁለት አሀዝ አሳደግሁላችሁ እያለን ነው:: የኢህአዴግ የቁሳዊ ልማት ዝርዝሩ ረጅም ነው:: የኢትዮጵ ቴሌቪዥንና ሌሎች የመገናኛ ብዙሃን እንዲሁም በየመድረኩ የሚደረጉ ዲስኩሮች የሚሉትን የሚሉት ይህን የቁሳዊ ልማት ረጅም ዝርዝር እያገላበጡ ነው:: በየደቂቃውና በየሰዓቱ የሚወራው ስለ አምስት ዓመቱ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድና ስለ ሚለኒየም ግድብ ነው:: ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ላይ ድርስ መድረክ ይዘው፣ ማይክሮፎን ጨብጠው የሚናገሩ ደቂቃንና ልሂቃን የኢህአዴግ መንግሥት የሚያከናውናቸው የቁሳዊ የልማት ሥራዎችን በየደቂቃው ሳይጠቅሱ ከአለፉ ንግግር ያደረጉ አይመስላቸውም::

በእርግጥ ቁሳዊ ልማት በራሱም ቢሆን የሚጠላ አይደለም:: ሆኖም ቁሳዊ ልማት ብቻውን የተሟላ ልማት አያመጣም:: የተሟላ ልማት የቁሳዊ ልማትና የመንፈሳዊ ወይም ሰብአዊ ልማት ድምር ውጤት ነው:: መንገድ መሠራቱ ጥሩ ነው:: በዚያ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ነፃ ሰዎች ካልሆኑ፤ ማለትም በነፃነት መሳብ፤ በነፃነት መናገር በነፃነት ሃሳባቸውን በቃልም ሆነ በጽሑፍ መግለጽ የማይችሉና በፍርሃት ድባብ ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች እስከሆኑ ድረስ መንገዱ የተሟላ ልማት መግለጫ አይደለም:: ኮንዶሚኒየሞች መሠራታቸው ጥሩ ነው:: ሆኖም አንደኛ ኮንዶሚንየሞቹ በጥራት የተሠሩ ካልሆኑ፣ ቤቶቹ ለዜጎች የሚሰጡበት መንገድ ፍትሐዊ ካልሆነ ቤቶቹን ያገኙ ሰዎች ከዛሬ ነገ ትፈለጋለህ ተብዬ እወሰድ ይሆን? ፖለቲካዊ በሆነ ግምገማ ከሥራ እባረር ይሆን እያለ የሚሰጋ ከሆነ የነፃ ዜጋ ቤት አይደለም:: ስለዚህ ኮንዶሚኔሙ በመሠራቱ ብቻ የተሟላ ልማት ምልክት አይደለም:: መንፈሱ የተረጋጋ በአገሩ ሥርዓት የሚተማመን ነፃ ዜጋ የሚኖርበት ቤት አልሆነም ማለት ነው:: ካልሆነ ደግሞ የተሟላ ልማት መግለጫ አልሆነም ማለት ነው:: ትምህርት ቤት መሠራቱ ጥሩ ነው:: ሆኖም በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት ጥራት ያለው ካልሆነ፤ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በመማርና ማስተማር ሂደቱ በሙሉ የአካዳሚክ ነፃነት የማይሰሩ ከሆነ፤ ትምህርት ቤቶች የአንድ ፓርቲ ርዕዮተ ዓለም ማስፋፊያ፣ የአንድ ፓርቲ ካድሬዎች መፈልፈያና በአንድ ፓርቲ አባላት የአስተዳደር ቁጥጥር ውስጥ የገቡ ከሆነ የእውነተኛ ልማት መሣሪያዎች መሆናቸው ይቀራል:: እንዲህ ከሆነ ከኤለመንታሪ ጀምሮ እስከ ዩኒቬርሲ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ለኢህአዴግ መንግሥት የሚገለጽ መውደድ ወይም ፍቅር አይኖርም፤ ምናልባት ከጥቂት ከሥርዓቱ ጥቅም ተካፋዮች ወይም አድርባዮች ጭልጭል ከሚል በስተቀር::

ማንኛውም ልማት ማዕከሉ ሰው ነው:: ሰው ብቻ አይደለም፤ ነፃ ሰው ነው:: ማንኛውም ዓይነት ልማት የነፃ ሰውን ቁሳዊና መንፈሳዊ ህይወት የሚያዳብር ካልሆነ የተሟላ ልማት ነው ማለት አይቻልም:: ነፃነት የሌለው ልማት ጎደሎ ልማት ነው:: ዴሞክራሲ የሌለው ልማት ኮስማና ልማት ነው:: ግዙፍ የሚባለው የሚሌኒየም ግድብም ቢሆን እየተገነባልህ ነው የሚባለው እያንዳንዱ ዜጋ ነፃ ካልሆነ፤ በዚች አገር ዴሞክራዱ ካልሰፈነ ኮስማና ነው:: ከንጋት

ወደ 10 ዞሯል

# አቶ መለስ ይፋ ያደረጉት የመምህራን ማባረሪያ ስትራቴጂ

ዳንኤል ተፈራ

ማክሰኞ ሚያዝያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም ረፋድ ላይ ነው:: ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በመቅረብ ከአባላቱ ለሚነሱ ወቅታዊና አንገብጋቢ ለተባሉ ጥያቄዎች ላይ ማብራሪያ ሰጥተዋል:: ማብራሪያቸው የተዋጣላቸውና የተናነቃቸው እንዳሉ ሆነው ማለት ነው:: ለአንዳንዶቹ ደግሞ ከማብራሪያነቱ ይልቅ ማደናገሪያነቱ ልቆም ቢሆን ማብራሪያ ሰጥተዋል::

እኚሁ ጠቅላይ ሚንስትር ወደ ፓርላማ ሲመጡ "ያው የተለመደው ማደናገሪያ ነው! ምን አዲስ ነገር ሊኖር?" ብለው የመስማት ፈላጐታቸውን ጠርቅመው የዘጉ የመኖራቸውን ያህል ጆሯቸውን አቁመው ላለብን የማህበረ-ኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግር አንዳች ነገር ጠብ ያደርጋሉ ብለው በጉጉት የሚሰሟቸው አሉ::

ሚያዝያ 9 ቀን የአቶ መለስን አፍ በጉጉት ሲጠብቁ ከነበሩት መካከል መምህራኑ ዋነኞቹ ይመስሉኛል:: የሚከፈላቸው ደመወዝ ባግባቡ በልተው ቆመው እንዳያስተምሩ ያደረጋቸው መምህራን ከደመወዝ ጥያቄ ተነስተው እስከ ሥራ ማቆም አድማ መምታት ደርሰው ነበር:: ነበር ብቻ ሳይሆን እየሞቱም ነው:: ጥያቄያቸውም የቆመ አይመስለኝም:: በዚህ ሂደት የአቶ መለስ ወደ ፓርላማ መምጣት ለመምህራኑ ተስፋ ለማድረግም ተስፋ ለመቁረጥም ወሳኝ ነበር::

መምህር ቁምላቸው (ስሙ የተቀየረ) ለባለፉት 10 ዓመታት በአንድ የመንግሥት ት/ቤት ተቀጥሮ እያስተማረ ይገኛል:: ከዚህ በፊትም ህይወት "ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ" አይነት ነበር የሚለው ቁምላቸው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደመወዛችን ያንኑ የተለመደ የውሃ ቅዳ ውሃ መልስ" ህይወት እንኳ መግፋት እንዳልቻለ ይናገራል:: ኑሮ በጣም ከመክበዱ የተነሳ ህይወት እጅግ ከባድ ሆኗል:: ማስተማር ደግሞ ከትውልድ መቅረፅ ጋር የተያያዘ ስለሆነ መምህሩ በራሱ የሚተማመን፣በአግባቡ ምግብ የሚያገኝና የሞራል ጥንካሬ ያለው መሆን ይገባዋል:: እነዚህ ተደማምረው ለሙያው ክብር መስጠትን እንዲለማመድ ይጋብዛሉ::

መምህሩ እንደሚለው የጠ/ሚ መለስ ፓርላማ መቅረብ ጋር ተያይዞ የመምህራኑ ጉዳይ እንደሚነሳ ገምቷል:: አቶ መለስ ሲናገሩ ፈፅሞ ንግግራቸውን መስማት ከማይፈልጉት ኢትዮጵያውያን በተቃራኒ ያሉት ኢትዮጵያውያን ንግግራቸውን ከሬድዮ ይልቅ በቴሌቪዥን ማየት ይፈልጋሉ:: እንደ ምክንያት የሚያቀርቡት ደግሞ ሰውየው በአፋቸው ብቻ ሳይሆን በእጃቸውም፣ በግንባራቸውም፣ በቅንድባቸውም ይናገራሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው:: አንዳንዴ ደግሞ ለመሳቅ የሚጓጉ "ዝንጉ" የፓርላማ አባላትን መመልከት ዘና ስለሚያደርግ ይሆናል:: አሊያም በጠቅላይነታቸው ዝና እያተረፉ ስለመጡ በተለይ ደጋፊዎቻቸውና የፓርቲያቸው ካድሬዎች "ከስተው ይሆን፣ጠቁረው ይሆን ወይስ ድንቡሽቡሽ ብለው ይሆን" የሚለውን ለማየትም እዚያው ቴሌቪዥን ፊትለፊት ዐይኖቻቸውን የሚያፈጡ አሉ:: በቴሌቪዥን ማየት ያልተሳካላቸው የድምፅ ማስተላለፊያ ቱቦውን ጆሮአቸው ላይ ሰክተው "ደሞ ምን ሊሉ ነው?" በማለት ያዳምጣሉ:: በቴሌቪዥን ከተከታተሉት ውስጥ ደግሞ መምህር ቁምላቸው አንዱ ነው:: ያው በተከፋና በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ተንጠልጥሎ ማለት ነው::

እዚህ ላይ አቶ መለስ ወደ ፓርላማ ሲመጡ ለምን በጉጉት ይጠበቃሉ? የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል:: መልሱ ግን ብዙ አይከብድም:: ከተለያዩ አስተያየቶች እንደምንሰማው አቶ መለስ ያው ጠቅላይ ናቸው፤ ያው ኢህአዴግ ማለት መለስ፤መለስ ማለት ኢህአዴግ ናቸው:: ብቸኛው ልሂቅ፣ብቸኛው አድራጊና ፈጣሪ፤አሳሪና ፈቺ... ናቸው:: ስለዚህ አቶ መለስ የሚናገሩት እውነትም ይሁን ሐሰት በፈፃሚዎቻቸው ተግባራዊ ይደረጋል:: እነ መምህር ቁምላቸው ቴሌቪዥን ላይ አፍጥጠው ማርፈዳቸውም ከዚህ የተነሳ ነው:: እና "አቶ መለስ ምን አሉ?" በጣም ብዙ ነገር አሉ:: በጉጉት ሲጠብቁ ለነበሩት መምህራን ወሽመጣቸውን ቁርጥ የሚያደርግ መርዶ ከመናገራቸው በፊት ያነሷቸውን አንዳንድ አንኳር ጉዳዮች ላንሳ::

ባለፈው ፓርላማ እንደቀረቡ ለመንግሥታቸው ፈተና የሆነ "የመንግሥት ሌባና የግል ሌባ" የሚባሉ ሁለት ምድቦች እንዳሉ ነግረውን ነበር:: የግል ሌባው ዘራፊ ሲሆን የመንግሥት ሌባው ደግሞ የዘረፋው አመቻች ነው:: ከዚያ በኋላም ዝርፊያው አልቆመም ማለት ነው:: አሁን ጠ/ሚኒስትር መለስ ሕዝቡ ሌቦችን ለማደን ከጐናቸው እንዲቆም ልመና ቢጤ አስተላልፈዋል:: አገዛዛቸው በሙስና ከፋኛ እንደተዘፈቀ፤ሙስና እጅና እግሩን አስሮ አላላውስ እንዳለው አመላካች ንግግር ነው:: "አንድ እጃችን ታስሮ መታገል ስላልቻልን ሕዝቡ ይድረስልን" እያሉ ነው:: መንግሥታቸው በሙሰኞች መጥለቅለቁን እንዲህ በማለት ነበር የገለፁት:-

"መንግሥት መዋቅሩ ውስጥ ኪራይ ሰብሳቢዎችና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት ያላቸው ግለሰቦችን መንግሥት አንድ እጁን ታስሮ እየታገላቸው ነው::" የመንግሥት መዋቅር ነቀዝ እንደበላው በቆሎ ውስጡ ባዶ ሆኗል ማለት ነው:: ልብ አድርጉ መለስ ያሉት የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ነው:: ይሄ ሥርዓቱ የገደል ጫፍ ላይ እንደቆመ የሚያመላክት ይመስለኛል:: መስጥ እንደበላው እንጨት ነኩቷል ማለት ነው::

በሀገሪቱ ስለተከሰተው የኑሮ ውድነትም ቢሆን ምንም አዲስ ነገር አልተናገሩም:: እንደውም እዳቸውን የሚወስድላቸውን ፍለጋ ሲዋትቱ እንደነበር ሁኔታቸው ያሳብቁባቸዋል:: የሸቀጦችን ዋጋ መቆጣጠር አለመቻል የመንግሥታቸውንም ደካማ መሆን ከማሳየት ባለፈ ሌላ ነገር ያለው አይመስልም:: ግን መለስ ለዚህ ተጠያቂ የሚሆን አንድ አካል ነግረውናል:: "ሕገ-ወጥ ነጋዴዎች ናቸው::" በማለት:: በርግጥ ህገ-ወጥና ስግብግብ ነጋዴዎች ችግር እንደሚፈጥሩ እውነት ነው:: ነገር ግን ህገ-ወጥ ነጋዴዎችን መቆጣጠር ለምን አልተቻለም? ከጀርባቸውስ ማን አለ? የሚሉት ጥያቄዎች ተከድነው ቢበስሉ ይሻላል::

ሌላው ወቅታዊና ከአቶ መለስ አጥጋቢ መልስ ይሰጥበት ይገባ የነበረው ጉዳይ መንግሥት በሀይማኖት ጣልቃ መግባት የሚለው ነው:: ጠ/ሚኒስትሩ የመንግሥት እጅ አጭር እንደሆነ ለማሳየት ሞክረዋል:: ግን ግን የካዱ አይመስለኝም:: እኛ የሃይማኖት አባቶች ሲያስተምሩ አልተገኘንም አላሉም:: ሕገ-መንግሥት ለማስተማር እንደሚሄዱ ተናግረዋል:: በክርስትና መጽሐፍ ቅዱስ የያዘ ሰባኪ ጐን ሕገ-መንግሥት የያዘ ካድሬ ይቆማል እንደማለት ነው:: መለስ እንዲህ አሉ:- "ኡላማዎች ዕምነታቸውን ሲያስተምሩ እኛ ደግሞ ሕገ-መንግሥት አስተምረናል::" ይሄ ንግግር ቢያንስ መንግሥት ከሃይማኖት ተቋማት ደጅ እንደማይጠፉ ፍንጭ የሚሰጥ ነው:: ህገ-መንግሥት በነካካ አፋቸው ሃይማኖቱንም ቀጥለውትስ እንደሆነ ማን ያውቃል?

በወፍ በረር ወደ ሌላው ጉዳይ ስናልፍ ደግሞ የጉራፈርዳ ተፈናቃዮችን እናገኛለን:: እንደ አቶ ሽፈራው "አይ የተባረሩት ይሄን ያህል ብቻ ናቸው::" አላሉም:: ኧረ ጭራሽ ተባረሩም አልተባረሩም አላሉም:: ይልቁንም ባልተደራጀ አኳኋን የሰፈሩ እንደሆኑና ጉራፈርዳ ምስራቅ ጐጃም እንደሆነ ነገሩን:: ይሄን አያውቁም ነበር:: ሌላም ጨመሩ:: "ሞፈር ዘመቶች" ናቸው የሚል:: እሳቸው የተፈናቃዮችንና የአፈናቃዮችን ችግር በአጭሩ ዘግተው ኃላፊነት ስለጐደለው የሌሎች ቅስቀሳ ዘለቁ:: የዜጐችን ጥቅም የፖለቲካ ቅጥም ከሚፈልጉት ጋር በማያያዝ ለመሹለክ ፈለጉ:: መቼስ ህፃናት ልጆቻችንና በፌስታል ጥቂት ነገር አንጠልጥለው ጽ/ቤታቸው ድረስ በመሄድ ስለተማፀኗቸው ተፈናቃዮች አልሰማሁም ሊሉን አይችሉም:: ብአዴን በመኪና እየጠረዘ ከጽ/ቤታቸው ገለል እንዳደረገላቸው አላውቅም አይሉም:: እዚህ ጋ ግን አንድ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል:: አቶ ሽፈራውም ሆኑ አቶ መለስ የተባረሩት ደን ጨፍጫፊዎችና አውዳሚዎች እንደሆኑ ሊነግሩን ሞክረዋል:: እሺ ይሁን:: ታዲያ ህገ-ወጥ የሆነ ሰው በህግ ይጠየቃል እንጅ እንዴት ወደ ሀገርህ ሂድ ይባላል? ይሄን እንዲመልሱ ይጠበቃል::

አቶ መለስ ከመለሷቸው መካከል ጥቂት ነገር ካነሳሁ ይበቃኛል:: አሁን ወደ ዋናው ርዕሴ ላምራ:: የመምህራን ጉዳይ:: የመምህራን ጉዳይ ሲነሳባቸው የተቆጡ ይመስላል:: ለምን ይቆጣሉ? የዕውቀት ብርሃኖችን ተስፋ ለምን ያሳጣሉ? በዕለቱ ያነሷቸው ዕውነታዎች (facts) አከራካሪና አደናጋሪ ናቸው:: መለስ በማንና የት፣መቼ እንደተጠና ሳይነግሩን 99.9% መምህራን

ወደ 10 ዞሯል

ፍኖተ -ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም
ተመሠረተ። ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሥር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በወቅታዊ ጉዳዮችና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር የፓርቲው ጋዜጣ ነው።

**ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል ይፈልጋል። የማንኛዉም ሰዉ ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን። ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለዉ ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲዉን ለማቅረብ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነዉ**

ዋና አዘጋጅ፡-
ሰለሞን ስዩም
አድራሻ፡-
የካ ክ/ከተማ ወረዳ 1
የቤ.ቁ 028

አዘጋጆች፡-
ብዙአየሁ ወንድሙ
ብስራት ወ/ሚካኤል

አርታኢ፡-
አንዳርጌ መሥፍን

አምደኞች፡- ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ወንድሙ ኢብሳ
አንዱዓለም አራጌ
ግርማ ሞገስ
ደረጀ መላኩ
ቀለሙ ሁነኛው
በለጠ ጎሹ

ኮምፒውተር ጽሑፍ፡-
የሺ ሃብቴ
ብርቱካን መንገሻ

ህትመት ክትትል፡-
አያክሉህም ጀንበሩ

አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ

አሣታሚው፡-
አንድነት ለዴሞክሲና ለፍትህ ፓርቲ(አንድነት)

አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤ.ቁ አዲስ

አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07 የቤ.ቁ 984

የዝግጅት ክፍሉ
ስልክ +251 118-44 08 40
+251 922 11 17 62
+251 926 81 46 81
+251 913 05 69 42
+251 923 11 93 74


ፖ.ሳ.ቁ፡ 4222

ኢሜይል፡- fnotenetsanet@yahoo.com
udjparty@gmail.com
andinet@andinet.org

ፋክስ ቁጥር፡- +251-111226288



# ርዕሰ አንቀፅ




# አገዛዙ የተዘፈቀበት መረጃ የ"መጋገር" ልክፍትና "ድህነት ቀንሷል" ዲስኩር

መረጃ "መጋገር" ማለት ነባራዊን ሁኔታ አጣሞ፣ ለራስ በሚመች ሁኔታ መረጃ የማቅረብ ኢ-ሞራላዊ ተግባር ነው፡፡ መረጃዎች በቀጥታ የሚሰጡንን ውጤት ሳይሆን፣ እኛ የምንፈልገውን ውጤት እንዲሰጡን መረጃዎችን የማሸት ሂደት ነው፡፡ ፈረንጆች እንደሚሉት "If you torture the data long enough, it will confess" ማለት ነው፡፡

መረጃ "መጋገር" የብዙ አምባገነን መንግስታት መለያ ነው፡፡ አምባገነን አገዛዞች ለዚህ ዓላማ ይረዳቸው ዘንድ ዋና ዋና የመረጃ አመንጪ ተቋማትን ነጻነት ይነፍጋሉ፡፡

ጥራት ያለው የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ መረጃዎች ጥቅማቸው ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ በመሬት ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በተሻለ ቅርበት የሚገልጽ መረጃ፣ የታሻለ ፖሊሲ ለመቅረፅ፣ ዕቅድ ለመንደፍና ለአፈጻጸም ግምገማ ወሳኝ ናቸው፡፡

በሌላው መልኩ ከነባራዊ ሁኔታ ባፈነገጡ መረጃዎች ግባትነት የሚመራ ሀገር፣ ኮምፓስ/አቅጣጫ ማሳያ ከሌለው መርከብ ጋር አንድ ናቸው፡፡ የቁማር መንገድ ይሆናል፤ በማዕበል የመስጠም ዕድሉም ሰፊ ነው፡፡ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡

በሀገራችን መረጃዎችን የማመንጨት ሂደት ትልቅ ክፍተት አለበት፡፡ ከመረጃ አሰባሰብ አንጻር ተያያዥ የሆኑ ህጋዊና ተቋማዊ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ በተጨማሪም የሙያ ብቃት ክፍተቶች፣ የግልፅነት መጋደል፣ የመረጃዎች አሰባሰብ ዘዴዎች ደካማነት፣ ከሌሎች መረጃዎች ጋር ያለው የወጥነት ችግር፣ የመረጃዎች ትክክለኛነትና አስተማማኝነት እጦት፣ መረጃዎች ወቅታቸውን ጠብቀዉ ያለመውጣትና በቀላሉ ለህዝብ ተደራሽ ያለመሆን ጉዳይ በግልጽ የሚታይ ነው፡፡

ሀገሪቷ በካድሬያዊ መረጃዎች ከጫፍ እስከ ጫፍ ተጥለቅልቃለች፡፡ ስኳር ከገቢያ በጠፋበት ወቅት፣ ስኳር በሽበሽ ነው የሚል መረጃ፤ የግሉ ሴክተር የባንክ ብድር ፈጽሞ ማግኘት ባልቻሉበት ወቅት፤ የባንክ ብድር በሽበሽ ነው የሚል መረጃ፤ የጤፍ ዋጋ ጣሪያ እየነካ ባለበት ሰዓት፣ የጤፍ ዋጋ ተረጋግቷል የሚል መረጃ፤ አርሶ አደሩ በቀን ሁለቴ መብላት ባቃተው ሰዓት፣ አርሶ አደሩ ሚሊየነር ሆነ የሚል መረጃ፤ በየቀኑ የምንታዘበው ነው፡፡ እነዚህን መረጃዎች መፈብረክ አገዛዙ የታከተው አይመስልም፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ያለው የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ ራሽያ በኮሚኒስታዊ ስርዓት ውስጥ በነበረችበት ጊዜ የምታደርገው ዓይነት ይመስላል፡፡ በአንዲት ራሽያ መንደር ውስጥ የሚኖር ገበሬ በወረዳዋ ኋላፊ ሲጠየቅ፣ አንድ በግ ብቻ እንዳለው ይገልጻል፡፡ የወረዳው ኋላፊ ለበላይ አለቃው ገበሬው አራት በጐች እንዳለው ያሳውቃል፡፡ ሌላኛው ኋላፊ በተራው አራት በጐች ጨምሮበት፣ ገበሬው 8 በጐች እንዳለው ለበላይ ኃላፊው ያሳውቃል፡፡ እያለ እያለ ጓድ ስታሊን ጋር ሲደርስ ገበሬው የሚኖረው የበግ ብዛት ከ30 በላይ ይሆናል፡፡ ሀገሪቷ በካድሬዊ መረጃዎች የሃብታም አርሶ አደሮች አገር ሆነች ማለት ነው፡፡

የህወሓት/ኢህአዴግ አፈጻጸም ሪፖርቶች፣ በእንዲህ ዓይነት ካድሬያዊ መረጃዎች የታሹ ናቸው፡፡ የአንድ ዓመቱን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም "ስኬት"፣ የ11 በመቶ "ፈጣንና ቀጣይነት" ያለው የዕድገት ፕሮፓጋንዳና የ"ድህነት ቀንሶዋል" ዲስኩርን ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡

ለምሳሌ በኢትዮጵያ የሚመረቱትን የግብርና መረጃ እንመልከት፡፡ ለምሳሌ መንግስታዊው የማዕከላዊ ስታትስቲክ ኤጀንሲ መረጃ እንደሚያመላክተው በ1998 ዓ.ም. መህር ዘመን በኢትዮጵያ 11.2 ሚሊየን ሄክታር መሬት እንደታረሰ ሲገልፅ፣ የግብርና ሚኒስቴር በበኩሉ 13 ሚሊየን ሄክታር በላይ መሬት እንደታረሰ ገልፃőል፡፡

በሌላ በኩል ከዓለም ዓቀፍ ተቋማትና ከመንግስት የሚለቀቁ መረጃዎች የሰማይና የምድር ልዩነት ይስተዋልባቸዋል፡፡ ለምሳሌ የማዕከላዊ ስታትስቲክ ኤጀንሲ በ1998 ዓ.ም. መህር ዘመን በመላው ሀገሪቱ 28 ሚሊየን ኩንታል ማሽላ እንደተመረተ ሲያስታውቅ፣ ዓለም ዓቀፍ የምግብ ፖሊሲ ምርምር ተቋም በጥናቱ በተመሳሳይ ወቅትና ጊዜ በሀገሪቱ የተሰበሰበው ማሽላ 14 ሚሊየን ኩንታል ብቻ መሆኑን ነው፡፡ መንግስት ተመረተ ከሚለው ግማሽ ማለት ነው!

የማዕከላዊ ስታትስቲክ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅትና የዓለም የምግብ ድርጅት የምግብ ዋጋ ሁኔታን አስመልክቶ የሚሰበስቡት መረጃዎች እጅግ ከፍተኛ የሆነ ልዩነቶች አላቸው፡፡ በተለይ የማዕከላዊ ስታትስቲክ ኤጀንሲ የሚያወጣው የዋጋ ግሽበት መረጃ፣ ግሽበቱ ያለበትን መጠን እጅግ ዝቅ አድርጎ እንደሚዘግብ የተለያዩ ጥናቶችን ዋቢ ማድረግ ይቻላል፡፡

እነዚህን ለማሳያነት አነሳን እንጂ በሀገራችን የሚሰበሰቡ የትምህርት፣ የጤና፣ የኢንዱስትሪ፣ የግብርና የሌሎች ዘርፎች መረጃዎች ከፍተኛ የጥራት ችግር አለባቸው፡፡ የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲት ተመራማሪዎች የተደረገው ጥናት በግልጽ እንዳረጋገጠው፣ በመንግስት የሚወጡ መረጃዎች ከፍተኛ የሆነ የታማኝነት ችግር እንዳለባቸው ነው፡፡ በእነዚህ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ህወሓት/ኢህአዴግ 11.4 በመቶ ኢኮኖሚው ዕድገት ማስመዝገቡን ለማወጅ የሚደርስበት የለም፡፡ የውጭ ድርጅቶችም ይህን የኢህአዴግን መረጃ ይዘዉ ይቀበሉታል፡፡

በሀገሪቱ ድህነት እነደቀነሰ መንግስት በቅርቡ ገልጾዋል፡፡ በ1997 ዓ.ም. 38 በመቶ ከድህነት በታች ይኖሩ የነበሩ ዜጎች፣ በ2002 ዓ.ም. ከድህነት ወለል በታች ወደ 29 በመቶ መውረዱን መንግስት አብስሮናል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ የገቢ ክፍፍል (የኑሮ ደረጃ ልዩነት) በከተማ እንደቀነሰ ተነግሮዋል!

እንዲህ ዓይነት መረጃ ምን ያህል ታማኒነት ሊኖራቸው እንደሚችል ያነጋግራል፡፡ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው የገዥው መደብ አባላት ሚሊየነር ስለሆኑ ድህነቱ ቀነሶዋል የሚባለውን እንቀበል ብንል እንኳን፣ እንዴት የገቢ ክፍፍል (የኑሮ ደረጃ ልዩነት) እንደቀነሰ ግልጽ አይደለም፡፡ ያውም በከተማ!

ድህነት እንዴት እንደቀነሰ ዝርዝሩን የሚያውቁት መረጃውን የሰበሰሁት፣ "የቀቀሉት"ና "የተነተኑት" ምሁራን ካድሬዎች ቢሆኑም፣ የቀን ተቀን ኑሮዋችን የምንረዳው (common intuition) ግን ኑሮ እጅግ መክበዱን ነው፡፡

ይሁን እንጂ ህወሓት/ኢህአዴግ ኢኮኖሚው 11.2 በመቶ ፍጥነት እያደገነው በሚልበት በአሁኑ ሰዓት፣ ድህነት ባለበት እየረገጠ ነው ወይም ጨመሮዋል ማለት ላያዋጣ ይችላል፡፡ የድህነት ቀንሷል ዲስኩር፣ ሥርዓቱ ነኝ ከሚለው ልማታዊ መንግስትነት ጋር አብሮ እንዲሄድ ታቅዶ የተሰራ ይመስላል፡፡

በተለይ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ላይ የተቀመጡ ዋና ዋና ግቦችን (ለምሳሌ የአኮኖሚ ዕድገት ዕቅድ፣ የድህነት ቅነሳ ዕቅድ፣ ወዘተ) አላሳካውም ማለት፣ የኢህአዴግን "ልማታዊ መንግስት" የቆመበትን የፕሮፓጋንዳ መሰሶ እንደመነቅነቅ ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም ድህነት መቀነሱንና የኢኮኖሚ ዕድገቱ መቀጠሉን ማብሰር (እውነትም ይሁን ውሸት)፣ ለኢህአዴግ የህልውና ጥያቄ ሆኗል፡፡

ተስፋችን "የተቀቀሉ" መረጃዎች ከማምረት ወጥተን፤ ትክክለኛ (accuracy)፣ የተሟላ (completeness)፣ ወቅቱን የጠበቀ (timeliness)፣ አስተማማኝ (reliable) ና ሀቀኛ (integrity) መረጃ የሚያቀርቡ ጠንካራ ተቋማትን ማየት ነው፡፡

ትግላችን የፓርቲ አባልነትን/ደጋፊነትን/አደርባይነትን ከሙያው የማያስበለጥ ጠንካራ ሲቪል ሰርቪስ ማየት ነው፡፡ ለሆዳቸው፣ ለቤትና ለመኪና የሚሰሩ ሳይሆን ለሙያቸው በሀቀኝነት የሚሰሩ ባለሙያዎችን ማየት ነው፡፡ ተስፋችን አገዛዞች በተለዋወጡ ቁጥር፣ እንደ ገዥዎች ፍላጎት መረጃ የማያመረቱ ነጻ ተቋማትን ማየት ነው፡፡ በአጭሩ ትግሉ ህዝባዊ ታማኝነት ያላቸውን ተቋማትን መመስረት ነው፡፡

መረጃን ከማደረጀትና ከማስረጽ አንጻር ቁልፍ ሚና ያላቸውን ተቋማትን ነጻነት ማረጋገጥ፣ ለመረጃ ታማኝነት ቁልፍ ነው፡፡ በተለይም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲና ቤሔራዊ ባንክን አንጻራዊ ነጻነት መጠበቅ ወሳኝ ነው፡፡ በተለይ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ አጀንሲ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጽኖ ወጥቶ፣ ራሱን ብቃት ባላቸው የሰው ኃይል ማደራጀት አንዱ የተሻለ አማራጭ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በተለይ ከምርጫ 1997 በኋላ የማዕከላዊ ስታትስቲክ ኤጀንሲ አብዛኛዎቹ መምሪያዎቹ በኢሕአዴግ አባላት ወይም ደጋፊዎች ብቻ እንዲመራ ተደርጎዋል፡፡ ይህም ይበልጥ ነፃነት አሳጥቶታል፡፡

ባለፉት ሃያ ዓመታት እንዳየነው፣ ህወሓት/ኢህአዴግ ለዚህ ግብ መዳረሺያ የሚሰራ ኃይል አይደለም፡፡ በጠቅላይነት አስተሳሰብ የተለከፈ ነው፡፡ መረጃ በመፈብረክ "11 በመቶ ዕድገታችንን አስቀጥለናል" ማለት የህልውና ጥያቄ አድርጎ የያዘ ድርጅት ሆኗል፡፡

የሀገራችን ኢኮኖሚ ያደገበትን አሃዝ፣ በእጅ አዙር በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚጸድቅበት አሰራር የሚቆመው መቼ እንደሆነም ግልጽ አይደልም፡፡ ያአደጉ አገሮች ከስራ አስፈጻሚው ነጻ የሆኑ ተቋማት እውነተኛ የስራ አጥነት ቁጥር ስንት እንደሆነ፣ ኢኮኖሚ የፈጠረውን ስራ ስንት እንደሆነ፣ ኢኮኖሚው በስንት እንዳደገ/እንደወረደ፣ ወዘተ የሚነግሩን ነጻ ተቋማት ያስፈልጉናል፡፡

በመንግስት የሚወጡ መረጃዎችን ታማኝነት ሁላችንም እንድንቀበል ከተፈለገ፣ መንግስት መረጃ የሚያደራጁ ተቋማት ላይ እጁን ያንሳ፤ ነጻነታቸው በህግና በተግባር ይረጋገጥ፡፡ አሁን ያለው አካሄድ ግን ግልጽ ነው - Torture the data until it confess.

ጋዜጣችን "ፍኖተ-ነፃነት" ብለናታል፡፡ "ፍኖት" ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር "የነፃነት መንገድ" ማለት ነው!!

# ክቡር ሆይ እኔ የአንድ እምነት እና አንድ ሀገር አራማጅ ነኝ



ግርማ ሠይፉ ማሩ
girmaseifu32@yahoo.com

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በምክር ቤት ቀርበው መልስ የሰጡባቸው ጥያቄዎችና መልሳቸውን ስንመረምር ብዙ ነገር ማለት ይቻላል፡፡ ዋና ዋና ናቸው የሚባሉትን ስንመለከት ግን የሚመለከቱትን እናገኛለን፡፡

በሱማሊያ ስለተደረገው ወታደራዊ እንቅስቃሴ ማብራሪያ መስጠት ተገቢ እንደነበር አምናለሁ፡፡ የዚህ ጉዳይ ማጠቃለያ ግን መሆን ካለበት የወታደራዊው ወጪ ምንጭ ምንድነው? (ኢጋድ ጥሪ አድርጎልን ከሆነ መከፈል ያለበትም ኢጋድ እንደሆነ ታሳቢ መወሰድ ይኖርበታል)፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሆነ ምክር ቤቱ ለዚህ ተጨማሪ በጀት መጠየቅ አይኖርበትም ወይ? እንደምታውቁት እንደዚህ ዓይነት ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን የመወሰን ስልጣን የፌዴራል ምክር ቤቱ ስልጣን አይደለም፡፡ ምክር ቤቱ መረጃ የሚሰማው እንዲሁ በጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜ ነው፡፡ በእርግጥ ጦርነት የማወጅ ስልጣን የምክር ቤቱ ቢሆንም፤ አስፈፃሚው ይህ ጦርነት አይደለም፤ ሰላም ማስከበር ነው ካለ ምን ማድረግ ይቻላል፡፡ ምክር ቤቱ ባለው ስልጣን ግን ወጪው ከየት መጣ ብሎ መጠየቅ ይችል ነበር፡፡

በሱማሊያ የነበረው እንቅስቃሴ ውጤታማ እነደነበር የተገለፀበት መንገድ በግሌ አልተመቸኝም፤ የሱማሌ ህዝብ ሰላም የፈለገው ጫት ለመቃምና ቴቪ ለማየት ነበር ብሎ ማሳነስ ተገቢ አይደለም፡፡ ጫት መቃም በሱማሊያ ምድር ብርቅ ባይሆንም ግን ለእንደዚህ ያለ ግዙፍ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ስኬት መለኪያ መሆኑ ተገቢ አይደለም፡፡

ሌላው የሰራዊቱን እንቅስቃሴ ጉዳይ ውስጥ ትኩረት የምትሻ ሆና ያገኘኋት "የኢትዮጵያ ሰራዊት እያፀዳ ለጂቡቲና ለኡጋንዳ ወታደሮች ያስረክባል" የምትለው ነጥብ ነች፡፡ ምን ማለት ነው? መስዋዕትነት መክፈል ሲያስፈልግ የኢትዮጵያ ሰራዊት፤ ለጥበቃው ጊዜ ሌሎች፤ ምን ነው የሱማሊያ ህዝብ አሁንም የኢትዮጵያ ሰራዊት እዛ እንዲቆይ አይፈልግም ማለት ነው?

ኢትዮጵያ በምታደርጋቸው ማንኛቸውም እንቅስቃሴዎች መታየት ያለባቸው "ጓደኛ መምረጥ ይቻላል፤ ነገር ግን ጎረቤት መምረጥ አይቻልም" በሚለው መስፈርት ይኖርበታል፡፡ ሱማሊያ ጎረቤታችን እንዳትሆን ማድረግ አይቻልም፡፡

ብዙ ጉዳዮች እንደተርጓሚው እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡ ነገር ግን አንድ እምነት አንድ ሀገር ማለት ግን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር እንተረጎሙት ሳይሆን፤ አንድ ሰው ሊኖረው የሚገባው አንድ ዕምነት ብቻ ነው (ሰኞ፤ ዕሮብና አርብ ሙስሊም ማክሰኞ፤ ሀሙስና ቅዳሜ ክርስቲያን፤ ወዘተ መሆን አይቻልም) ይህ ደግሞ አምላካዊ ቃል ነው (እኔ ቀናተኛ አምላክ ነኝ ሲል) ይህ አምላካዊ ቃል ደግሞ የሚሰራው ለሚያምኑበት ነው፡፡ ቃልቻ ቤት እየሄዳችሁ ቤተክርስቲያን አትምጡ ማለት ነው፡፡ ሊኖረን የሚገባው አንድ እምነት ነው፡፡ በእርግጠኝነት ሙስሊም ሆኖም ክርስቲያን መሆን አይቻልም፡፡ ስለዚህ ይህ ለአንድ እምነት የመገዛት ፍልስፍና የሁሉም የእምነት ዘርፎች መለያ ነው፡፡ ጥንቆላ ብቻ ነው ይህንን የሚፈቅደው - ይህ ደግሞ በሁሉም እምነቶች የተወገዘ የመጥፎ መንፈስ ስራ ነው፡፡ ስለዚህ እኔ ያለኝ አንድ እምነት ብቻ ነው፡፡ መፍከሬም ይኸው ነው፡፡

ከአንድ እምነት ጋር ተያይዞ የመጣው የአንድ ሀገር ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በእርግጥ አከራካሪ ነው፡፡ አንድ አንድ ሀገሮች ጥምር ዜግነትን የሚፈቅዱ አሉ፡፡ ይህም ሆኖ እኔ በግሌ ኢትዮጵያ ከምትባል ሀገር በስተቀር ሌላ ሀገር የለኝም- እንዲኖረኝም አልፈልግም፡፡ ይህን አቋሜን ስገልፅ ግን እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ ስል ሌሎችን ኢትዮጵያዊ አይደላችሁም ተብሎ ልከሰስ አይገባም፡፡ አንድ የእስልምና እምነት ተከታይ ኢትዮጵያዊ ሊሆን እንደሚችል ብዥታ ኖሮብኝ አያውቅም ወይም የሌላ ክርስትና እምነት ተከታዮች ኢትዮጵያዉያን እንደሆኑ አልጠራጠርም፡፡ ኢ- አማኒያንም ቢሆኑ፣ አንድ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር አለችኝ ብዬ ነው ለዚህች ሀገር እድገት (ሁሉ አቀፍ እድገት ማለቴ ነው) የሚከፈል መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ የሆንኩት፡፡ ሌላ አማራጭ የለኝም - አማራጭ ያለው ግን ካልተመቸው ወደዛኛው ሊሄድ ይችላል፡፡ ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ እንደሚባለው፡፡ እኔ ግን ሀገሬ አንድ ነች፡፡ ኢትዮጵያ፡፡ ይህ ማለት ግን በምንም መመዘኛ ይህች ሀገር የኔ ብቻ ነች ማለት አይቻልም፡፡ አይሆንምም፡፡

እነዚህን መሰረት አድርጌ ክርስቲያን ወንድሞቼ አንድ ሀገር አንድ እምነት ብለው ቢሰብኩ፤ ቢዘምሩ፤ ቢፎክሩ ለክርስትና ወንድሞቻቸው በእምነትና ሀገር ፍቅር መፅናት በማለት እንጂ በዚህች ሀገር ሌላ እምነት ወይም ሌላ ዓይነት የዜግነት መግለጫ መኖር የለበትም ማለት አይደለም፡፡ ለዚህም ነው እኔም የአንድ እምነት አንድ ሀገር አዝማሪ ነኝ የምለው፡፡ ተግባባን፡፡

በመጨረሻ ወደ ኑሮ ውድነት ስንገባ ግልፅ ሆኖ የወጣውን መንግሥት የሚከተለውን የተንሸዋረረ ፖሊሲ አምኖ ከማስተካከል ውጭ አሰልቺ ወደ ሆነብን የዋጋ ንረት ምንጭ ትንተና መግባት በኑሮ ውድነት ለተሰቃየው ዜጋ ዳቦ የሚገዛለት አይሆንም፡፡ ለዳቦው ስንዴ ከውጭ ገዝተን እያመጣነው የሚለው መልስ በቅጡ አረጋግጦት ያለፈው ነገር ቢኖር መንግሥት ይህችን ሀገር በምግብ እህል ራሷን ለማስቻል እንዳልቻለ ብቻ ነው፡፡ ከሃያ አንድ ዓመት የኢህአዴግ አገዛዝ በኋላ የአፍሪካ የውሃ ማማ የምትባል ሀገር ስንዴ ትገዛለች ሲባል ፌዝ ነው፡፡ በቅርቡ በወጣው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የአንድ ዓመት የአፈፃፀም ግምገማ ይፋ የሆነው አነስተኛ አርሶ አደር ምርታማነት በበቂ ማሳደግ ያለመቻሉ ነው፡፡ ይህም በግልፅ የፖሊሲውን ሸውራራነት ከማሳየት የዘለለ ነገር የለውም፡፡ ገንዘብ ካለን እህል እንገዛለን የሚሉ የኢህአዴግ ፖለቲከኞች መፈክር፤ በምግብ እህል መቻል ስትራቴጂክ የሆኑ ወይም የሉአዋላዊነት ጉዳይ ከሚባሉት አንዱ መሆኑን የማይረዱ ናቸው፡፡ አሜሪካ የእህል ማምረቻ ዋጋ የፈለገውን ያህል ውድ ቢሆን የእህል ምርቷን ለውጭ አሳልፋ አትሸጥም፡፡ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ትደጉማላች እንጂ፡፡ ኢትዮጵያ ዳቦ ከውጭ የሚገዛላት መንግሥት ሳይሆን የምትፈልገው፤ ይህ በሀገር ውስጥ እንዲመረት የሚያስችል ፖሊሲ ያለው መንግሥት ነው፡፡

የፖለቲካ ምህዳር መጥበብን በተመለከተ ማለት የምፈልገው ያቀርብኳቸው ማስረጃዎች ከበቂ በላይ ናቸው ብዬ ስለማምን ድጋሚ ማለት አልፈልግም፤ አሁንም ፅዋው ሞልቶ እንዳይፈስ መንግሥት ይህችን ሀገር በጥበብ መምራት ይጠበቅበታል፡፡ ካልቻለ ከዚህ ቀደም የነበሩት መንግስታት ዕጣ እንደሚገጥመው ለመገመት ጠንቋይ መሆን አያስፈልግም፡፡

# ዴሞክራሲ በትግል የሚገኝ ነፃነት እንጂ ከአምባገነኖች በስጦታ የሚሰጥ ገፀበረከት አይደለም



ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
mesayewa2011@gmail.com

ለዛሬ ጽሑፌ መነሻ ያደረግኩት የአርቲስት ታደለ ገመቹን ዘፈን ነዉ፡፡ ልጆች የአባቶቻቸዉን ታሪክ በአጋጣሚው ሁሉ በማንሳት ታሪካቸዉን እንዳይረሱ ከማድረግ በተጨማሪ የቀደሙት አባቶች ለሀገራቸው የከፈሉትን መስዋዕትነት አዲሱ ትውልድ እንዲገነዘብ ያደርጋል፡፡ለአባቶቻችን አብዛኛውን ጊዜ ከኑሯቸው ይልቅ ሀገራቸውን ያስቀድማሉ፡፡ በአንድ ወቅት እኔ ከአንዲት ሀኪም ጓደኛዬ ጋር እየሄድን፤ በመኪናዬ ዉስጥ አንድ ዘፈን ሰማን፡፡ ዘፈኑ ኦሮምኛ ነዉ፡፡ ግን ዘፈኑ ኦሮምኛ ሆኖ አንድ የአማርኛ ቋንቋ ቃል አለበት፤ እኔ ነገሩ ገርሞኝ "ለምን እንዲህ አለ ብዬ" ጠየቅኳት፤ ጓደኛዬን፡፡ ዶክተሯ ጓደኛዬ ግን ለምን እንደተዘፈነ ጭምር ስትነግረኝ አባቶቻችን ለነጻነት የከፈሉት ዋጋና እኛ ግን ነጻነታችን ግለሰቦች እንዲሰጡን መፈለጋችንን እያውጠነጠንኩ ሀሳብ ይዞኝ ነጎደ፡፡

በወቅቱ አርቲስት ታደለ ገመቹ እና አጠገቤ ያለችዉ ዶክተር የነበራቸዉ ግንዛቤ የአሁኑን ዘመን ወጣቶች የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ብቻ የሚከታተሉ የሚመስለው በርካታ ሰው ባለበት በዚህ ሰዓት አርቲስት ታደለ ገመቹ አንድ ቀደምት የነበረ ዘፋኝ ዘፈን ከማስታወሱ በተጨማሪ ዶክተሯ ጓደኛዬ የመጀመሪያዉን አርቲስት ታሪክ በሚገባ ማወቋ አስገርሞኛል፡፡ በእስራኤል መከራ ጊዜ የተወለደውን ሙሴን እናቱ ታሪኩን እየነገረች እንዳሳደገችዉ ይህችን ሀኪም ልጃቸውን አባትና እናቷ ታሪኳን እየነገሩ እንዳሳደጓት ገባኝ፡፡ አደነኳቸውም፡፡ መቼም አርቲስት ታደለ ገመቹም ቢሆን ያን ጊዜ ያልነበረ ገና ልጅ ቢሆንም የኦሮሞ ልጆች ለኢትዮጵያ ሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር ለእኛ ለዚህ ዘመን ወጣቶች የገለጸበት ታሪክ ነው፡፡

ነገሩ እንዲህ ነዉ፤ አርቲስት ታደለ ገመቹ አዲስ ባወጣዉ አልበሙ ካወጣዉ ዘፈን አንዱ እንዲህ ይላል

እንቴኙ ማሉማቲ ቴኛ(inttenyu maalummatti tenyaa)

እንቴኙ ማሉማቲ ቴኛ(inttenyu maalummatti tenyaa)

ዓለም መንግስቲ ቢረ ዴምና (alam mangistii bira demnaa)

ወነ ጉባኤን ጃዱ ደጌኛ (wanna gubaa'en jadhu dhagenya)

ቀጥተኛ ትርጉሙ "እንቀመጥም፤ ምኑን እንቀመጣለን? /አንቀመጥም፣ ምኑን እንቀመጣለን

ወደ ዓለም መንግስታት ጉባኤ ሄደን

የዓለም አቀፍ ጉባኤ የሚለንን እንሰማለን፡፡" ማለት ነዉ፡፡

እውነትም ሀገር ተወሮና ነጻነት ጠፍቶ መቀመጥ አይቻልም፡፡

ወቅቱ ሀገራችን በፋሽስት ኢጣሊያ የተወረረችበት ጊዜ ነበር፡፡ ያን ጊዜ አርበኞች አባቶቻችን በሀገራቸዉ ስደተኛ ሆነዉ በየዱሩ እያደሩ የጣሊያንን ጦር እያርበደበዱበት የነበረበት ጊዜ ሲሆን፤ ጣሊያኖች እኛ ሀገራቸዉ ሳንሄድባቸዉ "አሁን የምንታገልበት እንጂ የምንቀመጥበት ጊዜ አይደለም፡፡" በማለት ነበር የዘፈነዉ፡፡ የጣሊያን መንግስት ይህችን ድሃ ሀገር በዓለም በተከለከለና በተወገዘ ቦንብና ባልተፈቀደ የጦር መሣሪያ ይጨፈጭፍ ስለነበረ ንጉሰ ነገስቱ አጼ ኃ/ሥላሴ የጣሊያንን መንግስት የግፍ ወረራ በግልጽ ለማስረዳት ወደ ዓለም መንግስታት ለክስ ሄደዉ ነበርና፤ አርቲስቱ እንደንጉሱ ህዝቡ ሁሉ ወደ ዓለም መንግስታት ጉባኤ ሄዶ ዓለም መንግስት በወራሪዉ ፋሽስት ጣሊያን ላይ የሚያስተላልፈዉን ዉሳኔ ሄደን እንስማ ነዉ ያለዉ፡፡ ዛሬም ቢሆን እኛ ሀገር ቤት ሁነን ስንታገል እንደንጉሱ ከሀገራቸዉ ሸሽተዉ የወጡ ወንድሞቻችን የዓለም መንግስት በአምባገነኑ ኢህአዴግ ላይ ጫና እንዲያደርግ መስራትና ሀገር ቤት ያለነዉን ልታግዙን ይገባል፡፡ አርቲስት ወሰን ዲዶም ህዝቡን ከማነቃቃት በተጨማሪ በዓለም መንግስታት ጉባኤ ላይ ጫና ለማሳደር ነው የዘፈነዉ፡፡ እኛም ይህንን ዘፈን እንዘፍን ዘንድ ግድ ነዉ፡፡ ህዝባችን መከራና መፈናቀል በዝቶበት መቀመጥ አይሆንም፡፡

ወራሪዋን ጣሊያንን በተመለከተ አንዳንድ ኢትዮጵያዉያን "ምናለ ጣሊያን 15 ዓመት እንኳዋን ገዝታን በነበረ" ሲሉ ይሰማሉ፡፡ ምክንየታቸዉ ጣሊያን ሀገሪቱን ገዝታ ቢሆን ኖሮ ሀገራችን እንደሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች በመሰረተ ልማት ያደገች ትሆን ነበር ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ በእጅጉ የተሳሳተ አመለካት ነዉ፡፡ የትኛዉም የአፍሪካ ሀገር በቅኝ ገዥዎች አላደገም፡፡ ቅኝ ገዥዎች በነበሩበት ሀገር የነበረዉ መሰረተ ልማት ምሳሌ መኪና መንገድ ከማዕድን ቦታ እስከ ወደብ ድረስ ብቻ ለዚያዉም ቀጭን መንገድ እንደነበር መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ መብራትም ቢሆን በማዕድን ቦታና በቅኝ ገዥዎች መኖሪያ አካባቢ ብቻ ነበር፡፡ የእነርሱ ዋና ዓላማ ቅኝ የገዟቸውን ሀገራት አንጡራ ሀብት ወደሀገራቸዉ ማጋዝ ብቻ ነበር፡፡ የትምህርት ዕድልም ቢሆን ከቲዎሎጂ ውጭ እንዲማሩ አይፈልጉም ነበር፡፡ ምክንያቱም ቲዎሎጂ በሚያስተምሯቸዉ ሰዎች አማካኝነት ያለ ቅኝ ገዥዎች ሌላ አማራጭ እንደሌለ እና ለገዥዎቻችሁ መገዛት የአምላክ ፈቃድ ነዉ እንዲሉ ለማድረግ ነው፡፡ ልክ ዛሬ የኢህአዴግ ካድሬዎች "የኢትዮጵ ብቸኛ አማራጭ እህአዴግ ብቻ ነው" እንደሚሉት ማለት ነው፡፡ ኢህአዴግ ከሌለ ሀገሪቱ አንድ ቀንም ውላ የማታድር የሚመስላቸዉ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ ስንፍና ነዉ፡፡ የኢትዮጵያ ትክክለኛ አማራጭ የኢትዮጰያ ህዝብ እንጂ ኢህአዴግ አይደለም፡፡ ዛምቢያ ነጻ በወጣች ጊዜ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ቲዎሎጂ የተማሩ ሰዎች የነበሩ ሲሆን አንድ እንኳን ኢንጅነር አልነበራትም፡

ወደ 8 ዞሯል

የዛሬው እንግዳችን የተከበሩ አቶ ብሩ ብርመጂ ይባላሉ፡፡ ያለፈው ፓርላማ አባል እና የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር ሲሆኑ በግል ህይወታቸው፣ በፓርቲያቸው እና በሀገሪቱ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ከባልደረባችን ብስራት ወ/ሚካኤል ጋር አጭር ቆይታ አድርገዋል፤እንድታነቡም በአክብሮት ጋብዘናል፡፡

# የምንታገለው የመደብ ክፍፍልና አድሏዊነትን ለማስቀረት ነው

➢ አቶ ብሩ የት ተወልደው አደጉ? የትምህርት እና የሥራ ህይወትዎስ ምን ይመስላል?

ተወልጄ ያደኩት ሞጆ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቴንም እዛው ነው የጨረስኩት፡፡ የ2ኛ ደረጃ ትምህርቴን ናዝሬት (አዳማ) በሚገኘው አፄ ገላውዲዎስ ት/ቤት በመጨረስ አየር ኃይል ገብቼ በቴክኒክ ዘርፍ ተምሬ ለዓመታት አገልግያለሁ፡፡ በመቀጠልም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመግባት በዋናነት በፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት በረዳትነትም በህዝብ አስተዳደር ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪ አለኝ፡፡ በሙያዬም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲፕሎማት በመሆን ኤርትራ ውስጥ ሰርቻለሁ፡፡ በመጨረሻም እዛ እያለሁ የኢትዮጵያን እና የሕዝባችንን ጥቅም ለማስጠበቅ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር በመሆን ስንጥር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አዲስ አበባ አስጠርቶ አሰናብቶኛል፡፡ ከዛ በኋላ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በአስተዳደር ጉዳይ ሰርቻለሁ፡፡

➢ ወደ ፖለቲካው ህይወትስ መቼና እንዴት ገቡ?

በ1992 ዓ.ም አገር አቀፍ ፓርቲ በነበረው ኢዴፓ ውስጥ በመሳተፍ የራሴን አስተዋፅዖ አበርክቻለሁ፡፡ በ1997 ዓ.ም ደግሞ ቅንጅትን (የቀድሞውን) በመመስረት በምርጫው በመሳተፍ ተመርጬ ፓርላማ በመግባት ለሀገራችን ይጠቅማል ያልኩትን አስተዋፅዖ አበርክቻለሁ፡፡ ከዚያም ቅንጅት እንደ ቀድሞው መቀጠል ባለመቻሉ አንድነት ፓርቲን መስርተን እኔም ከሌሎች ጓደኞቻችንንና አባሎቻችን ጋር በመሆን እየታገልኩ እገኛለሁ፡፡

➢ በሀገሪቱ ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች እያሉ እንዴት አንድነት ፓርቲን መረጡ?

እኛ ኢትዮጵያውያን ታሪክ እና አኩሪ ባህል ያለን ታላቅ ሕዝብ ነን፡፡ ስለዚህ ይህን ታላቅነታችንን አስጠብቀን የሕዝባችንና የሀገራችንን ቅጥም ለማስጠበቅ የሚያስችል ፓርቲ በመመስረት (ከሌሎች ጋር በመሆን) ፓርቲው ጥሩ ፕሮግራም ያለው በመሆኑ አብሬ ልታገል ችያለሁ፡፡ ይህን ስል በብሔር ተከፋፍለው የሚታገሉትን ዋጋ ማሳጣቴ ሳይሆን የእኔ ምርጫ ለኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም በጋራ ማስጠበቅ ካልተቻለ ለሚከፋፍሉን መንገድ መክፈት ስለሆነ የሚበጀን በአንድነት መታገልና ተያይዘን መጓዝ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ዋናው ደግሞ መለያዬም ሆነ ማንነቴም ኢትዮጵያዊነት ስለሆነ በኢትዮጵያዊነቴ ግዴታዬን እየተወጣሁ ነው፡፡ ከዚህ በፊት የተመኘሁት የዴሞክራሲ ስርዓት እውን መሆን ስላልቻለ አሁንም ቢሆን እስኪሳካ ትግሌን እቀጥላለሁ፡፡ በሰላማዊ ትግሉ ፅኑ እምነት ስላለኝ አንድነትን ልመርጥ ችያለሁ፡፡



➢ በፓርቲው ውስጥ ያልዎት የሥራ ድርሻ ምንድነው?

የብሔራዊ ም/ቤት አባልና የአንድነት ፓርቲ የፖለቲካ ጉዳይ ምክትል ኃላፊ ነኝ፡፡

➢ የፖለቲካ ጉዳይ በፓርቲው ውስጥ በዋነኝነት ሥራው ምንድነው?

የሀገሪቱን የፖለቲካ እንቅስቃሴ በመቃኘት ጥናት ማድረግና መገምገም፤ ሌላው የሕዝብን ማኅበራዊ፤ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በተለይም ችግሮችን በማጥናት የመፍትሄ አቅጣጫ መጠቆም፡፡ ፓርቲያችን የሚከተለውን የትግል ስልት አተገባበር መቀየስ፣በሀገሪቱ ጉዳይ ያገባኛል ከሚሉት ጋር ኢህአዴግንም ጨምሮ የጋራ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት ሀገራችንን ከገባችበት አጣብቂኝ ውስጥ ለመታደግ ስትራቴጂ መንደፍና መተግበር፣አንድነት የሚከተለውን ርዕዮተ ዓለም ፍልስፍና በማስተዋወቅ ለሀገር ያለውን ጠቀሜታ ከሌሎች የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን ወደ ሕዝብ እንዲደርስ ማድረግ ዋናዎቹ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

➢ የሥራ ክፍላችሁ እስካሁን የሰራውና ውጤታማ የሆኑ ክንውኖች ካሉ ቢገልፁልኝ፡፡

ፓርቲያችን ጠቅላላ ጉባዔ ከተካሄደ እና ሥራ አስፈፃሚውና የፖለቲካ ጉዳይ በአዲስ መልክ ከተዋቀረ ገና አምስተኛ ወሩ ነው፡፡ ባለፉት አራት ወራትም የሥራ ክፍሉን የሚመሩ ሰዎችን የማዋቀር እና የመመደብ፣የፓርቲውን ደንብና ፕሮግራም እንዲሁም የፓርቲውን የ5 ዓመት ስትራቴጂና ዕቅድ መሠረት በማድረግ እቅድ አውጥተን በምክር ቤቱ እንዲፀድቅ አድርገናል፡፡ ማኅበረሰቡ ውስጥ በመግባትም፡፡ ጥናት አጥንተናል፡፡ ነገር ግን ወርደን አልተገበርንም ይህንንም ለመተግበር እየተንቀሳቀስን ነው፡፡

➢ እንደ ባለሙያና የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊነትዎ የወቅቱን የሀገሪቱን ፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዴት ታዘቡት?

ለመግለፅ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ በሀገራችን ያሉት ችግሮች እየተባባሱና ውስብስብ እየሆኑ አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡

እዚህ ላይ ኢትዮጵያን እንደ አንዲት መርከብ ቁጠራትና ወዴት እየሄደች እንዳለ፤ ልትሰጥም እንደሆነና ወደፊት እየተጓዘች እንደሆነ ማወቅ አስቸጋሪ እየሆነ ነው፡፡ የኑሮ ውድነቱ መባባስ፣የዋጋ ግሽበቱ ከፍተኛ መሆን፣የፖለቲካው ቀውስ መባባስ፣የሕዝቡ ኑሮ መመሰቃቀልና ዜጎቻችን በሀገራቸው ላይ የመኖር ዋስትና ማጣት አሳሳቢ ሆኗል፡፡ በህገመንግሥቱ የተቀመጡ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንኳ በአዋጅ እየተሸረሸሩ ናቸው፡፡ ሕዝቡ በሀገሩ ላይ ንብረት የማፍራት መብቱ በሊዝ ስም ተነጥቋል፡፡ ብቻ በአጠቃላይ በአሁን ወቅት ሀገራችን አደጋ ላይ ነውና ያለችው የፖለቲካ ድርጅቶች፣የኃይማኖት ተቋማት እና የሕዝብ ማኅበራት ገዥውን ፓርቲ ጨምሮ ለመታደግ በአንድ ላይ ልንረባረብ ይገባል፡፡

➢ እርስዎ ያለፈው ፓርላማ አባል ነበሩና አሁን



ካለው ጋር አነፃፅረው ትንሽ ቢያወጉኝ፡፡
ያለፈው ፓርላማ በሀገር ጉዳይ ላይ የተለያዩ ጠቃሚ ሐሳቦች ባሉት ተቃዋሚዎች ይንሸራሸሩ ነበር፡፡ የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም ይጐዳል ያልነውንም ሐሳብ እንቃወም ነበር፡፡ ይህ ሲባል ግን በገዥው ፓርቲ የመጣው አይፀድቅም ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሚወሰነውና የሚፀድቀው መጀመሪያ ስለሆነ ኢህአዴግ በነበረው የእጅ ብልጫ ያመጣቸው ሐሳቦች ከመጽደቅ የሚያግዳቸው ነገር አልነበረም፡፡ ነገር ግን ይብዛም ይነስም ቢያንስ ተቃዋሚዎች የሕዝብን ድምጽ በማስተጋባትና አማራጭ ሐሳብ በማቅረብ ንቁ ተሳትፎ ያደርጉ ነበር፡፡ ለምሳሌ ባለፈው የኢትዮጵያ ጦር ሶማሊያ እንዲገባ ሲወሰን ተቃውመናል፤ምክንያቱም የእኛ መከላከያ ሰራዊት ነቅቶ ድንበር መጠበቅ ይችላልና ይህንንም የተቃወምነው ሰራዊታችን የእኛ ስለሆነ በሰው ሀገር እንዲቆስልና እንዲሞት ስለማንፈልግና የሀገራችንና የዜጐቻችንን ክብርና ደህንነት ያዋርዳል በሚል ነበር፡፡ ያኔ በመቃወማችን ብንወገዝም መጨረሻ የፈራነው ሆኖ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ተገድሎ ሬሳው እንደውሻ ሲጐተት በውጭ መገናኛ ብዙኃን በማየታችን እንደ ዜጋ አዝነናል፤አልቅሰናልም፡፡ ይህም የሆነው በገዥው ፓርቲ ሰሚ በማጣት ነበር፡፡

ይሁን እንጂ የአሁኑ ፓርላማ 99.6% ኢህአዴግ ስለሞላው ተቃዋሚ አንድ ለእናቱ ሆኖ የገባውን የሕዝብ ድምፅ እያስተጋባ ያለው አንድ ሰው ብቻ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ፓርላማው የፓርላማነት ፀባይ አይታይበትም፣የተለያዩ ሐሳቦች አይንሸራሸሩበትም፡፡ ስለዚህ የውሳኔ ልዩነት ባይኖርም የአሁኑ ፓርላማ ካለፈው ጋር የሚነፃፀር አይደለም፡፡ ለዚህም ነው ለጥቂት ቡድኖችና ግለሰቦች ሲባል ሕዝብንና ሀገርን የሚጐዱ አዋጆች እየወጡ፣እየፀደቁና እየተተገበሩ ያሉት፡፡

- የእናንተ ፓርቲ (አንድነት) የሚከተለው ርዕዮተ ዓለም (አይዲያሎጂ) ምንድነው?

ሊበራል ዴሞክራሲ ሆኖ ባሉት ተጨባጭ ሁኔታዎች ለሀገራችንና ለሕዝባችን የሚጠቅሙ ጥቂት የሶሻሊስት ሐሳቦችንም አካትተናል፡፡ በዋነኝነት የምንከተለው ግን ሊበራል ዴሞክራሲ ሲሆን ይህም በግለሰብ ነፃነት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን የቡድን መብት ይፃረራል ማለት ሳይሆን የግለሰብ ነፃነት ከማክበር ጐን ለጐን የቡድን ከዚያም የመላው ሕዝብ ነፃነትና መብት ስለሚከበር ነው፡፡ ለምሳሌ ግለሰቦች በነፃነት የመደራጀት፣ የመናገር፣ የመፃፍ፣ሀብት የማፍራት፣የመሰብሰብና የመጠቀም ሙሉ መብት ይከበርላቸዋል፡፡ ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅምም ቅድሚያ በመስጠት ይህንንም ለማስጠበቅ የሚያሰራ ርዕዮተ ዓለም ነው የምንከተለው፡፡ በዚህም ምክንያት በእኛ አመለካከት ዜጐች ሁሉ እኩል ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የብሔር ብሔረሰቦችንና የቡድኖችንም መብት አክብረን እናስከብራለን፤ለሀገራችንም የጋራ ጥቅም እንታገላለን እንሰራለን፡፡ በአጭሩ የምንከተለው ርዕዮተ ዓለም ይህን ይመስላል፡፡

- ከኢህአዴግም ሆነ ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር ያላችሁ የአይዲኦሎጂ (የርዕዮተ ዓለም) ልዩነት ምንድነው?

አሁን ያሉትን 76 የፖለቲካ ድርጅቶችን መዘርዘር ጊዜና ቦታ አይበቃም፡፡ ነገር ግን ገዥው ኢህአዴግ የሚከተለው "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ሲሆን ይህም የግለሰቦችን መብትና ነፃነት የማይቀበልና የሚነፍግ ነው፡፡ በፍልስፍና ደረጃም፣በቡድን መብት ስም የመደብ ክፍፍል የሚያደርግና ዜጐችን እና ቡድኖችን በማበላለጥ አድሏዊ ሥርዓት በመዘርጋት የመሪዎችን ፍላጐትና ጥቅም የሚያስጠብቅ ጊዜ ያለፈበት እና በተለያዩ ሀገሮች ተሞክሮ የተጣለ ርዕዮት ዓለም ነው፡፡ እኛ የምናራምደው ሊበራል ዴሞክራሲ ግን ዜጐች ሁሉ እኩል ናቸው ብለን በማመን የመደብና የቡድን ክፍፍልንና አድሏዊ አሰራርን የሚያስቀር በዚህም ዜጐች ሁሉ በሀገራቸው ጉዳይ እኩል የመወሰን እና የመጠቀም ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ እንለያለን፡፡

- ተመሳሳይ ርዕዮተ ዓለም ካላቸው በሀገሪቱ ካሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋርስ ለምን ውህደት ፈጥራችሁ በጋራ አልሰራችሁም?

እየሰራን ነው፡፡ ለምሳሌ ባለፈው ከብርሃን ፓርቲ ጋር ተዋህደን በተጠናከረ መልኩ ለሀገራችን በሚጠቅም ሁኔታ እየሰራን ነው፡፡ ይሄም የሆነበት ምክንያት የሁለቱም ፓርቲ አመራሮችና አባላት ከራሳችን ተራ ጥቅም እና ፍላጐት ይልቅ የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ በመወሰናችን ነው፡፡

ከሌሎች ጋርም ለመዋሀድና አንድ ሆኖ ለመስራት እየተንቀሳቀስን ነው፡፡ ነገር ግን በርዕዮተ ዓለም ተመሳሳይ ስለሆንን ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ እና ለሕዝባችን ጥቅም እንቆማለን ከሚሉት ጋርም በጋራ ለመስራት እየተንቀሳቀስን ነው፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ)ን ስንመሰርት የተለያየ ርዕዮተ ዓለም የሚከተሉም ነበሩበት፡፡ ነገር ግን ዓላማችን አንድ ስለሆነ ተቻችለን ልዩነታችንን በማጥበብ ሀገራችንን ለመታደግ እየሰራን ነው፡፡ ወደፊት በሂደት የመድረክ አባላትን ጨምሮ የሀገሪቱ ጉዳይ ያሳስበኛል ያገባኛል ከሚሉ ሌሎች ፓርቲዎች ጋርም ውህደት ለመፍጠር እየተንቀሳቀስን ነው፡፡ በዚህ አንድነት ፓርቲ ችግር የለበትም፡፡ ምክንያቱም አንድነት ፓርቲ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ቤት ስለሆነ ዋናው ዓላማ የሀገሪቱንና የሕዝቡን ጥቅም ማስጠበቅ ነው፡፡

- ከእናንተ ጋር ተመሳሳይ ርዕዮተ ዓለም ከሚያራምዱ ሀገሮችም ሆነ መንግሥታት ጋርስ ግንኙነት አላችሁ? ከሌላችሁ ለምን?

እኛ እየተንቀሳቀስን ያለነው እንደ ፓርቲ ስለሆነ ሰፊ ግንኙነት መፍጠር ባንችልም አዲስ አበባ ከሚገኙ የተለያዩ ሀገሮች ዲፕሎማቶች ጋር ግንኙነት እየፈጠርን ልምድ እየቀሰምን ነው፡፡ የሚኖረንም ግንኙነት እንደ መንግሥት ሳይሆን እንደ ፓርቲ ስለሆነ ለሥልጣን ብለን የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚጐዳ ተግባር እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እያደረግን ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን ግንኙነታችንን በሰፊው ሄደንበታል ማለት አይደለም፡፡ ባለን የአቅም ውስንነት እየተንቀሳቀስን ያለነው በጥቂቱ ነው፤ ወደፊት ግን በተጠናከረ መልኩ እንቀጥልበታለን፡፡ በዚህም ከፍተኛ ድጋፍ እናገኝበታለን ብለን እናስባለን፡፡

**ከሌሎች ጋርም ለመዋሀድና አንድ ሆኖ ለመስራት እየተንቀሳቀስን ነው፡፡ ነገር ግን በርዕዮተ ዓለም ተመሳሳይ ስለሆንን ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ እና ለሕዝባችን ጥቅም እንቆማለን ከሚሉት ጋርም በጋራ ለመስራት እየተንቀሳቀስን ነው፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ)ን ስንመሰርት የተለያየ ርዕዮተ ዓለም የሚከተሉም ነበሩበት፡፡ ነገር ግን ዓላማችን አንድ ስለሆነ ተቻችለን ልዩነታችንን በማጥበብ ሀገራችንን ለመታደግ እየሰራን ነው፡፡ ወደፊት በሂደት የመድረክ አባላትን ጨምሮ የሀገሪቱ ጉዳይ ያሳስበኛል ያገባኛል ከሚሉ ሌሎች ፓርቲዎች ጋርም ውህደት ለመፍጠር እየተንቀሳቀስን ነው፡፡ በዚህ አንድነት ፓርቲ ችግር የለበትም፡፡ ምክንያቱም አንድነት ፓርቲ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ቤት ስለሆነ ዋናው ዓላማ የሀገሪቱንና የሕዝቡን ጥቅም ማስጠበቅ ነው፡፡**

- በመጨረሻ ቀረ የሚሉትና መናገር የሚፈልጉት ነገር ካለ ዕድሉን ልስጥዎት፡፡

በሀገራችን ጉዳይ ለመነጋገር ብዙ ይቀራል፡፡ ቢሆንም በተለይ ለወጣቱ አጭር መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡ ይህም ወጣቱ ከሀገሪቱ ሕዝብ ብዛት ከፍተኛውን ቁጥር ቢይዝም የመብቱ ተጠቃሚ ሳይሆን ቀርቶ የሌሎች መጠቀሚያ እየሆነ ነው፡፡ የሀገሪቱንና የራሳቸውን ጉዳይ ወደ ጐን በመተው ለምዕራብ አውሮፓ ስፖርት ትኩረት ሰጥተዋል፡፡ በእርግጥ ወጣቱ መዝናናቱን ባንጠላም ቅድሚያ ለራሱና ለሀገሩ መስጠት አለበት እላለሁ፡፡ ይህችን ሀገር የሚረከበው ራሱ ወጣቱ ስለሆነ መብቱንና ጥቅሙን ለማስከበር ከፍርሃት ተላቆ መታገል አለበት፡፡

ተቃዋሚችም እርስ በርስ ከመከፋፈል ወደ አንድ በመሰባሰብ የተዘራውን በጐሳ የመከፋፈል የፖለቲካ መርዝ በማርከስ ሀገራችንን ከጥፋት ልንታደግ ይገባል፡፡ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግም ቢሆን ሁሉንም ነገር እኔ አውቃለሁ፣ፈላጭ ቆራጭነኝ ማለቱን ትቶ ሀገራችንን ከገባችበት ማጥ ውስጥ ለማውጣት በጋራ ሊመክር ይገባዋል፡፡

በሀገሪቱ ለተፈጠረው የፖለቲካ፣የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ቀውስ ቅድሚያ ተጠያቂው ራሱ ኢህአዴግ ነው፡፡ ተቃዋሚዎችም ብንሆን ከተጠያቂነት ማምለጥ ስለማንችል በህጋዊና በሠላማዊ መንገድ እስከተንቀሳቀስን ድረስ ከፍርሃት ተላቀን ወደ ሕዝቡ ወርደን ልንሰራ ይገባል እላለሁ፡፡

ጋዜጠኞችም የሀገሪቱንና የሕዝቡን ነባራዊ ሁኔታ ትክክለኛውን ለሕዝብ ማሳወቅና ማቅረብ ይጠበቅባችኋል፡፡ በእርግጥ ተፅዕኖዎች ቢደርሱባችሁም ታሪካዊ እና የዜግነት ኃላፊነታችሁን ልትወጡ ይገባል፡፡ለማንም ሳትወግኑ በድፍረት እውነታውን በመግለፅና ሀገራችንን ከጥፋት ለማዳን ለሚደረገው ጉዞ የበኩላችሁን ልትወጡ ይገባል፡፡

ሕዝቡም በየጓዳውና በየቤቱ ከማጉረምረም መብቱን መጠየቅና መድፈር ይኖርበታል፡፡ በአጠቃላይ መላው ሕዝብ በተለይም የሀገሪቱ ጉዳይ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ሁሉ በጋራ ነቅተን ልንመክርና ልንወያይ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ችግሩ ሁላችንንም ይነካናልና ዜጐች በሙሉ ከፍርሃትና ከዝምታ መውጣትና ለመብቶቻችንም መታገል ይገባናል እላለሁ፡፡ የአፍሪካ ቀንድ ሠላምና ፀጥታ ያገባናል የሚሉ ሀገሮችም ከገባንበት ቀውስ እንድንወጣ ሊያግዙን ይገባል፤ አለበለዚያ ችግሩ የመጨረሻ ደረጃ ከደረሰ መቆጣጠር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

# መንግሥት በሙስሊሙ ማህበረሰብ ...

ከገፅ 1 የዞረ

ሰነዱ “ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህዝበ ሙስሊሙ ውስጥ መነጋገሪያ የሆነ አንድ ጉዳይ ይስተዋላል:: የጉዳዩ አነጋጋሪነት ከጉዳዩ ባለቤቶች አልፎ ባለፉት ዓመታት የአዲስ ራዕይ ዕትሞቻችን ተከታታይ ጽሑፎች የዳሰናቸውን የከሰሩ ፖለቲከኞችን ትኩረትም ስቧል:: አንዳንዶቹም ዘወትር ውስጥ ውስጡን እያብሰለሰሉ አጋጣሚ ብቻ ለሚጠብቁለት የነውጥ ዓላማቸው አመቺ ሁኔታ እየተፈጠረ እንደሆነ ስለተሰማቸው ምክር ተግሳፅና ብይን ብጤ በመስጠትም በየጋዜጦች በሚያወጧቸው ጽሑፎች የውዥንብሩን አድማስ ይበልጥ ለማስፋት መታተር ጀምረዋል:: በጉዳዩ ዙሪያ በአመራራችንና አባላት ዘንድ የተሟላ ግልጽነት የለም::” በማለት ያትታል::

ሰነዱ ዜጎች ከሚሉት የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በተቃራኒ መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት ባለመስጠቱ የመጣ መሆኑን ለማመላከት “ከእስልምና እምነት በተያያዘ የተፈጠረውን ወቅታዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል በተከታታይ የአዲስ ራእይ ዕትሞች ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ አቅጣጫችንን ይበልጥ እያሰፋን አክራሪነትን የምንዋጋባቸውን አቅጣጫዎችና በኃይማኖት ሽፋን የሚካሄደውን የኪራይ ሰብሳቢዎች አሰላለፍ ያየንበትን ሁኔታ ማስታወስ ይገባል::” ካለ በኋላ “በመሆኑም በየደረጃው በአመራሩና አባላት ዘንድ የውይይት መድረኮች ከፍተን መግባባት በመፍጠር ሕዝቡን ከብዥታዎች አስወጥተን አክራሪዎችን በማጋለጥ ተባብሮ መንቀሳቀስ ይችል ዘንድ በፈፀምነውና ልንፈጽመው በሚገባን፤በተናፈሰውና በእውነታው፤እንደመንግሥትና እንደዜጎች በሚመለከተንና ለእምነቱ ባለቤቶችና ተቋሞቻቸው ብቻ መተው ባለባቸው ጉዳዮች ዙሪያ መነሻ የሚሆኑ ነጥቦችን ለመጠቋቆም ተሞክሯል::” ሲል ያብራራል::

መንግሥት በተለመደው የአብዮታዊዴሞክራሲ እይታ የተነተነው ሲሆን “አገራችን የራሳቸውን ኃይማኖት ህገ-መንግሥታዊ ሽፋን ሰጥተው ይፋ የሃገሪቱ ኀይማኖት አድርገው የሌላውን ያረከሱ መሪዎች የነበሩዋትን ያህል ፀረ-ሁሉም ዓይነት ኃይማኖቶች የነበረው የደርግ ሥርዓት ውስጥም አልፋለች::” በማለት ጉዳዩን ፖለቲካዊም ታሪካዊም ለማድረግ ጥሯል:: በተጨማሪም በቀድሞ መንግሥታት ከነበረው በጅጉ በተሻለ መልኩ ኃይማኖታዊ ነፃነቶችን መጠበቁን ጠቅሶ “ቀደምት ሥርዓቶች በተከተሉዋቸው የኃይማኖት ጭቆናዎች ምክንያት የተፈጠሩና ሥር ሰደው የቆዩ የፍትህ መጓደሎችን ለማረምም እጅግ አበረታች እንቅስቃሴ በማድረግ ረጅም ርቀት ተጉዟል:: የእምነት ቦታዎችን ለመገንባት የነበሩ ችግሮችን በመቅረፋችን ባለፉት 20 ዓመታት በሁሉም ኃይማኖቶች ዘንድ የእምነት መዳረሻ ቦታዎች በከፍተኛ መጠንና ፍጥነት ተስፋፍተዋል::” በማለት ከጣልቃ ገብነት ነፃ መሆኑን ለማሳመን ይሞክራል::

ሰነዱ የሙስሊምን ወቅታዊ እንቅስቃሴን ሲገልፅም “የዴሞክራሲ ስርዓታችን ሁሉም ዜጎች በእምነት ነፃነት እንዳላቸው ያስቀምጣል፤ዜጎች የራሳቸውን የእምነት ነፃነት ማስከበር ይችሉ ዘንድ የሌላውንም የእምነት ነፃነት ማክበር እንዳለባቸው ያስቀመጣሉ::” ካለ በኋላ የክርስትና ኃይማኖት እንቅስቃሴዎችንም “በተመሳሳይ መልኩ አንዳንድ ኦርቶዶክስ ክርስትያኖች ሌላው ቀርቶ የተለየ አመለካከት ያላቸው ክርስትያኖችም ቢሆኑ የሚከተሉት እምነት ክርስትና አይደለም ብለው ከማመን አልፈው፣እነዚህ የተለየ አመለካከት ያላቸው ዜጎች እምነታቸውን በነፃነት እንዳያራምዱ በተለያየ ሽፋን ማፈን ይከጅላቸዋል::” በማለት ይከሳል::

ሰነዱ በአጠቃላይ የሙስሊሙ እንቅስቃሴ ላይ ያተኮረ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ተገኘ ስለተባለው የአልቃይዳ ሴል ከወሃቢያ ጋር በማወዳደር “ከዚህ ጋር ተያይዞ አንዳንድ ኃይሎች በሀገራችን የሚያራምዱዋቸውን ፀረ-ህገ መንግሥት የሆኑ አቋሞች ከህገ-መንግሥቱ ጋር አስተሳስሮ የመግለጽ ጉዳይ ሊኖር ይችላል:: ለምሳሌ ማንም እንደሚያውቀው በእስልምና እምነት ስም የሚንቀሳቀስ ነገር ግን የእስልምና መሠረቶችን ከመናድ ጀምሮ ፀረ-ህገ መንግሥት አቋሞች የሚያራምድ ቡድን ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ::” ካለ በኋላ የበለጠ ሲተነትን “ከከዋርጂያ በተወሰነ ደረጃ የተለየ አቋም ያለው በዚህ ምክንያትም በከዋርጂያዎች ዘንድ እንደ ከሃዲ የሚቆጠረው ወሃቢያ ነው:: ወሃቢያ ከከዋርጂያ በተለየ ሁኔታ በእውቀት፤በመማር ያምናል:: ከዚህ ውጭ ባለው ፀረ-ዴሞክራሲና ፀረ-ህገ መንግሥት አቋሙ ከከዋርጂያ አይለይም:: ወሃቢያ በመሠረቱ የኃይማኖትና መንግሥትን መለያየት አይቀበልም:: ኃይማኖት ከመንግሥት ተነጥሎ መሄድ አይችልም:: መንግሥትም ኃይማኖትን ማገልገል አለበት የሚል አቋም አለው:: ወሃቢያ በበቀለበት ሳዑዲአረቢያና ቀጥሎ በተስፋፋበት ባህሬን ይህንኑ አቋም የሚያራምድ ነው:: ይኸው አቋሙ እንደኛ በመሰሉ የበርካታ ኃይማኖቶች ቤት በሆኑ ሀገሮች ቀርቶ ሙሉ በሙሉ ሙስሊም በሆኑትም የሺአዎችን፤የሱፊዎችን ህልውና በሐየወት በማጥፋት ጭምር በመፈታተን የሚታወቅ ነው:: ይህ አቋም ከእስልምና ጋር ምንም ዝምድና የለውም:: ይልቁንም የእስልምና አስተምህሮዎችን ይፃረራል:: ይህአቋም የፖለቲካ ይዘት ያለው አቋም ነው ይህን አቋም መተቸት እስልምናን መተቸት ሊሆን አይችልም::” ይላል::

በተቃውሞው ላይ የተሳተፉ በርካታ ሙስሊሞች ተቃውሟቸው ከወሃቢያነት ጋር ምንም እንደማይገኝና ጥያቄያቸው መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ መግባቱን እንዲያቆም እንዲሁም በመረጡዋቸው የመጅሊስ መሪዎች እንዲተዳደሩ መሆኑን አበክረው ተናግረዋል::

# ዴሞክራሲ በትግል የሚገኝ . . .

ከገፅ 5 የዞረ

: ምክንያቱም ሀገሪቱ ኢንጂነር ካላት ለእድገቷ ይጠቅማት ስለነበረ ነዉ:: የቅኝ ገዥዎቿ ዓላማ ግን ለሀገሪቱ እድገት አለመሆኑን ከዚህ መገንዘብ ይቻላል::

አባቶቻችን ነጻነታቸዉን ከቅኝ ገዢዎቻቸዉ ከጣሊያን ሳይሆን ከትግላቸዉ እንደሚያገኙት ያዉቁ ነበረ::ጣሊያን በቆየባት የ5 ዓመት ዕድሜ ለአንድ ቀን እንኳን ተረጋግቶ እንዲያድር አልፈቀዱለትም:: እዚህ በአርበኝነት እረፍት እያሳጡት በሌላ ጎኑ በዓለም መንግስት በኩል በዲፕሎማሲዉም ቢሆን ይህ ነዉ የማይባል ትግል አድርገዋል:: ውድ አንባቢያን አርቲስት ታደለ ገመቹ እንደነገረን እንደ ቀደምቱ አርቲስት ወሰን ዲዶ ሁሉም በሚችለዉ ይዋጋ ዘንድ ግድ ነው:: ነጻነት በትግል የሚገኝ እንጂ ከገዥዎች የሚገኝ የገና ስጦታ አይደለም:: ዛሬ አርቲስቶችም ስፖርተኞች፣እድር ዳኞች ወይም መምህራን እንሁን ላብአደሮች፤ ህዝባችን ተረጋግቶ መኖር እስካልቻለ ድረስ እኛ ተረጋግተን መኖር አንችልም:: ጎረቤቶቻችን ጦማቸዉን እያደሩ እኛ በልተን ለማደር ይቸግረናል:: ምክንያቱም ጎረቤት እየተራበ እኛ በልተን በሰላም ለመኖር አይቻልምና ነው::

ንቦችን ከቦታ ቦታ በመምራት ይዛ የምትሄደዉ አዉራዋ ንብ ነች::አዉራዉ ያልመራዉ የንብ መንጋ ከመበታተን ዉጭ ሌላ ምንም አማራጭ የለዉም:: ስለዚህ የተቃዋሚ መሪዎች አሁንም ህዝቡን በአግባቡ እንመራ ዘንድ ግድ ይለናል:: ምናልባት የዓለም መንግስታትም ይሁን ኃያላን ሀገሮች ሊያግዙን የሚችሉት እኛ ተጽዕኖ መፍጠር እስከቻልን ድረስ ብቻ ነዉ:: ኃያላን ሀገራት ምንጊዜም ቢሆን መርዳት የሚፈልጉት የኃይል ሚዛኑ ወዳጋደለበት ነዉ:: አባቶቻችን እነርሱ ጥቁር ሆነዉ ነጬን፣ ድሃ ሆነዉ ሃብታሙን፣ ደካማ ሆነዉ ኃያሉን በዓለም መንግስት ዘንድ በመቅረብ ጫና በመፍጠራቸዉና ኃያል መሆናቸውን በማስመስከራቸው የፍርዱ ሚዛን ወደ እነርሱ እንዲያጋድል አድርገዋል::ንጉሱ የተቻላቸዉን ሁሉ አድርገው ከስብሰባው ተገኝተው ሁኔታውን አስረድተዋል:: ነገሩን ችላ ብለዉ የተመለከቱትን የዓለም መንግስታትን ወቅሰዋል:: ነገሮችን ችላ ማለት ከታሪክ ተወቃሽነት እንደማያድናቸዉ ነግረዋቸዋል:: አሁን በእኛ ላይ የደረሰዉ ነገ በእናንተ እንደማይደርስ ርግጠኛ አትሆኑም ብለዋል::ይህንን በማለታቸዉ ሁሉም ነገሩን በጥሞና እንዲመለከተዉ አደረጉ:: የኃይል ሚዛኑንም ወደሀገራችን እንዲያዘነብል አድርገዋል::

አሁን ባለንበት ዘመን ከኢህአዴግ መንግስት ጋር የሚደረገዉን ትግል ከ199 በላይ የሰላማዊ ትግል ሥልት ባለበት ሁኔታ ሁለት ያህሉን ሳይጠቀሙ ኢህአዴግ ምህዳሩን እንዲያሰፋ መጠበቅ “ጨረቃ ድቡል ቦቃ ዳቦ ጣይልኝ” ከሚሉት የህጻናት ጨዋታ የተሻለ ነዉ ብሎ መገመት ያስቸግራል:: አብዘኞቻችን ፈረንጆች ጫና እንዲፈጥሩልን እንፈልጋለን:: ይህ ግን ፈጽሞ ስህተት ነው፤ ፈጽሞ ሊሆንም አይችልም:: ሀገር ቤት አንገት ደፍቶ ተቀምጦ አጋጣሚውን ሲያገኙ ዉጭ ሁኖ ኢህአዴግ እንዲህ ነዉ:: እንዲያ ነዉ ማለቱ:: ለትችት እንጂ ለለዉጥ አይጠቅምም:: መታገል በሀገር ነበር:: ያለትግል የተገኘ ድል በዓለምም ሆነ በሀገራችን አይገኝም:: ሎተሪም ቢሆን ለማግኘት ሎተሪ መቁረጥ ያስፈልጋል:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ባሳተመው “የአክሊሉ ማስታወሻ” መጽሐፍ ላይ ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ኤርትራን፣አፋምቦን፣ጋምቤላን እንዴት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ እንዳደረጉ እና የኢትዮ-ኬኒያን ድንበር እንዴት እንደከለሉ ማንበቡ እጅግ በቂና ሀገርን ከነድንበሯ ለትዉልድ ማቆየት ሀገርን ቆርሶ እንደመስጠት ቀላል እንዳልነበር ግንዛቤ ይሰጣል:: ዛሬም ቢሆን ኢህአዴግ እንዲስተካከል እና ዴሞክራሲ በሀገራችን እንዲሰፍን የሚፈልግ የተቃዋሚ መሪ ሁሉን ችሎ የኃይል ሚዛን ወደ ህዝቡ እንዲያዘነብል እንደንብ አዉራ ተከታዩን ሊመራ ይገባል:: ይህ ካልሆነ ግን ዴሞክራሲን ከአምባገነኖች በስጦታ ማግኘት እንደማይቻል ልናዉቀዉ ይገባል እላለሁ::

በርካቶች ሀገራቸዉን ነጻ ያወጡት በከፍተኛ መስዋዕትነት እንጂ በስጦታ አይደለም:: እነ ማህተመ ጋንዲ፣ ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ጆርጅ ዋሽንግተን፣ የደቡብ አፍሪካው ኔልሰን ማንዴላ፣....... እና የመሳሰሉትን ማስታወሱ ተገቢ ነዉ::

“ሁል ጊዜ ምህዳሩ ጠቧል” ብሎ ማማረሩ በቂ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስም “ፈልጉ ታገኛላችሁ ለምኑ ይሰጣችኋል አንኳኩ ይከፈትላችኋል” ነው ያለው:: ምንም ነገር ለማግኘት ስራ የግድ ነዉ:: ነጻነትንም የፈለገ ቢኖር ታግሎ ከአምባገነኖች መንጋጋ መፈልቀቅ እንጂ አምባገነኖች ዴሞክራሲን ይሰጡኛል ብሎ መመኘት የበሬ ብልት ይወድቃል ብላ በሬን ስትከተል ከዋለቸዉ ቀበሮ ጋር ተመሳሳይ ነዉ::

## እስክንድር ነጋን የሸለመው ድርጅት በሽብርተኝነት ይከሰሳልን”

ታዋቂው ጋዜጠኛና የፖለቲካ ተንታኝ እስክንድር ነጋ ባለፈው ሳምንት ፔን ኢንተርናሽናል ከተባለ ዓለም አቀፍ ድርጅት ተሸላሚ ሆኗል። የመረጃ አውታሮች እንደዘገቡት ከሆነ “እስክንድር እስከ ዛሬ ድረስ በሚዲያ ላይ ባደረገው አስተዋጽኦ የ2012 ዓለም አቀፍ ሽልማት ተሸላሚ ሆኗል።” ተብሏል።

ይህ ደግሞ እጅግ የሚያናድድ ጉዳይ ነው። ልማታዊ መንግሥታችን ሽብርተኛ በሎ ያሰረውን ግለሰብ ሁሉም ሽብርተኛ ብሎ እንዲያምንና እንዲቀበል ስንት ወጪ ወጥቶበት ዶክመንተሪ ፊልም የተሠራበትን ሰው ማበረታታት ድፍረት ነው። በፀረ-ሽብር አዋጁ መሠረት ሽብርተኛን ማበረታታት በሽብርተኝነት ያስከስሳል ያስቀጣል። የኢህአዴግን መልካም ገጽታ የሚያጎድፍ ነው። ለመሆኑ ኢህአዴግ መልካም ገጽታ አለው? ብላችሁ እንድትጠይቁኝ አልፈቀድኩላችሁም!! በመሆኑም በየደረጃው የተመደባችሁ የኢህአዴግ ባለሚሎች በነካ እጃችሁ ሞያችሁን ተጠቅማችሁ ፔን ኢንተርናሽናል ድርጅትን በሽብርተኝነት ክሰሱልን!!?

## “ፍሬው ኃይሉና ኦህዴድ”

ሥራ ፈቶች የማያወሩት ነገር የለም። ግማሹ በየመሸታ ቤቱ ተቀምጠው ስም ማውጣት ይወዳሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በየጫት ቤቱ ተቀምጠው ፍተላ ይወዳሉ። እነዚህ አምስት ለአንድ የተባለው የዕዝና የቁጥጥር አደረጃጀት ያላገኛቸው መሆናቸው ነው። በኢህአዴጋዊ አነጋገር በልማታዊ ሠራዊት ያልተደራጁ መሆናቸው ነው። ሰሞኑን ሥራ ፈቶች ዛሬ በህይወት የሌለውን ታዋቂውን የአኮርዲዮ ተጫዋቹን ፍሬው ኃይሉንና ኦህዴድን ያገናኙበት መንገድ ገረመኝ።

በቅርቡ በመከላከያ ኢንጂነሪንግ አገር ውስጥ ተገጣጥሞ አገልግሎት ላይ የዋለው ሁለት አካል ያለው ግዙፍ የከተማ አውቶቢስ አለ። ሁለቱ አውቶቢስ አኮርዲዮ በሚመስል በሚተጣፍና በሚዘረጋጋ ተያይዟል። ያን የሚተጣጠፍና የሚዘረጋ ቦታ ፍሬው ኃይሉ አሉት። ላዩ ላይ ሞተር የሌለውን ተጐታቹን አውቶቡስ ደግሞ ኦህዴድ አሉት። አውቶቢሱን በጥቅሉ ደግሞ “ፍሬው ኃይሉና ኦህዴድ” የሚል ስም ሰጡት። ይህስ በፀረ-ልማትና ፀረ ህዝብ አያስከስስምን?

### እርማት

በፍኖተ-ነጻነት ጋዜጣ 2ኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁጥር 38 ማክሰኞ ሚያዚያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም በወጣው እትም ርዕዮት ዓለሙ በህመም ላይ ናት በሚለው ርዕስ ሥር ሁለተኛው አንቀጽ 11 መስመር ላይ ርዕዮት ዓለሙ በአዲስ ፕሬስ ጋዜጣ፣በቼንጅ መጽሔትና በኤፍ.ኤም 96.3 ሬዲዮ ላይ በጋዜጠኝነት ያገለገለ ሳይሆን የሚለው ያገለገለች ስትሆን ተብሎ ይነበብ።

# አዲሱ ያለቀለት ፍርሃትና ጭንቀት

ብስራት ወ/ሚካኤል
afrosonb@gmail.com

አንዳንድ ስማቸውን መግለፅ ያልፈለጉ የፖለቲካ ሳይንስ ሊቃውንት ኢትዮጵያ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጅማሮ በአንድ ሰው መዳፍ ውስጥ ገብታለች ይላሉ፡፡ ይህም የሆነው በአንድ የሴራ ፖለቲካ ተሰጥዎ ባላቸው ግለሰብ ሲሆን እሳቸውም አቶ መለስ ዜናዊ እንደሆኑ ይስማማሉ፡፡ እኚህን ሰው ሲገልፁም ከፍተኛ የስልጣን ጥማት እንዳለባቸውና ለዚህም የሚሆን ዋጋ ከመክፈል የሚያግዳቸው ነገር እንደሌለ በማውሳት፡፡ ለዚህም አቶ መለስ የህወሓት ሊቀመንበር፣ የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት ፕሬዘዳንት፣ በመጨረሻም ፍፃሜ የሌለው የሚመስለውን የጠቅላይ ሚኒስትርነትን ቦታ በብቸኝነት እንዴት እንደያዙ ማስታወሱ በቂ ነው ይላሉ፡፡

የአቶ መለስ ደጋፊዎች በከፊል በሊቃውንቱ አስተያየት ይስማማሉ፡፡ ነገር ግን አቶ መለስ በስልጣን የናኙት በእሳቸው የስልጣን ጥማት ሳይሆን በሚሾሟቸው አመራሮች ስግብግብነትና ለሆድ ማደራቸው ያመጣባቸው መዘዝ ስንፍና ነው ይላሉ፡፡ ለዚህም ማሳያ የእሳቸው ከፍተኛ ተሻዕሚዎች በዕውቀትና ብቃት ሳይሆን ለእሳቸው ባላቸው ተዓማኒነት ስለሚሆን በራስ መተማመን ስሜት የላቸውም ሲሉ ይናገራሉ፡፡

በአንፃሩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እነኚህ እውቀትና ብቃት የሌላቸውን ተሻዕሚዎችም በቀጣይነት እንዲያገለግሉ ጥሩ የመያዣ ሰንሰለት ያበጁላቸዋል፡፡ ይህም ሙስና ሲሆን ተሻዕሚዎቹ ከነቅርብ ዘመዶቻቸው እንዲበለፅጉ አይቶ እንዳላየ ያልፏቸዋል፡፡ ከዚያም አንድ ቀን ወደ ህሊናቸው ሲመለሱ አንገታቸው ላይ ባረፈው የሙስና ቀንበር "የዘላለም ባሪያ" ይሆናሉ፤ ይሄም በተሻዕሚዎቹ ፈቃድ እንጂ በአቶ መለስ ሴራ አይደለም ሲሉ ይሞግታሉ፡፡

አንዳንድ ተቃዋሚዎች በበኩላቸው ሁለቱንም ሐሳብ ትክክል እንደሆነ በመጠቆም ሀገሪቱ እየታመሰች ያለችው በአቶ መለስ የሴራ ፖለቲካና በሾሟቸው አመራሮች የብቃት ማነስና የሙስና መዘፈቅ ነው በሚል ይስማማሉ፡፡ ከላይ ለተጠቀሱት ሐሳቦችም እንደ ምክንያት ያነሱት የአቶ መለስ አካሄድ ከሀገርና ከህዝብ ጥቅም ይልቅ ለስልጣናቸው በማድላት እንደሆነ፤ አመራሮቻቸውም የአቅም ብቃት ማነስ እንዳለ ሆኖ በኢህአዴግ ርዕዮተ ዓለም እምነት ስለሌላቸው ሊሆን እንደሚችልም ግምታቸውን ይሰጣሉ፡፡ ነገር ግን የአቶ መለስም ሆነ የኢህአዴግ አካሄድ ለሀገርና ለህዝብ ጠንቅ መሆኑን ሳያውቁ ቀርተው ሳይሆን የ "አባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ" የሚባለውን አጥፊ ብሂል እየተገበሩ የህዝብን ንብረት የሚያባክኑ ብኩኖች ናቸውም ይላሉ፡፡

የኢትዮጵያን የቅርብ ጊዜ ፖለቲካን አፅንዖት ሰጥተው የሚከታተሉት የፖለቲካ ሳይንስ ባለሙያ አቶ አንተነህ ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች እንዳሉ ሆነው በሀገሪቱ ላይ ያለው የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ምስቅልቅል የተፈጠረው በዋነኝነት የአቶ መለስና ሹማምንቶቻቸው ካለባቸው ጭንቀትና ፍርሃት እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ፍርሃቱም የመጣው በህዝባቸው ላይ የፈፀሙት ገደብ የለሽ እስር፣ ስቃይና ግድያ እንዲሁም የሀገርን ጥቅም አሳልፎ የመስጠት ያለፈ ታሪክ እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ ይህንንም ለመሸፋፈንና ለማደስ በሚል ሌላ ትልቅ ስህተት ውስጥ በመግባት "ካፈርኩ አይመልሰኝ" ዓይነት ነገር ነው የሚፈፅሙት ይላሉ፡፡

አንድ ስማቸው እንዳይገለፅ የፈለጉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የስነ ባህርይ (Psychology) ባለሙያ በበኩላቸው በተለይ አቶ መለስ ከፍተኛ የህሊና ቀውስ ውስጥ መዘፈቃቸውንና ከራሳቸውም ጋር እየተጋጩ እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ አሁን እየወሰዷቸው ያሉት ርምጃዎች በፓርላማ የሚሰጧቸው የንቀት ምላሾች እና ለረጅም ጊዜ ከመገናኛ ብዙኃን መራቃቸው አንዱ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡ አካሄድም ከቀጠለ ምናልባት የአቶ መለስም ሆነ የኢህአዴግ የስልጣን ፍፃሜ በቅርብ ሊሆን እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩም ስድብን፣ ቁጣንና ንቀትን እንደ ባህል እየቆጠሩት በአባሎቻቸው ሳይቀር ትችት እየተሰነዘረባቸው ስለሆነ በድንገት በግብታዊነት የሚወስዷቸው ርምጃዎች ሀገሪቱ ላይ አደጋ ሊፈጥር ስለሚችል ይህን ለመታደግ ተቃዋሚዎችም ነቅተው ሊከታተሉ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ በተለይ የአቶ መለስ አካሄድ በዚሁ ከቀጠለ አመራሮቻቸው ህዝቡን ሊከፋፍሉት ይችሉ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ህዝቡ በተለይም ሙስሊሙ እና ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ እንዳይከፋፍሏቸው በመጠንቀቅ በሀገራዊና በመብቶቻቸው ጉዳይ አንድ መሆን እንደሚጠበቅባቸው በመግለፅ ሀገሪቱን ከሚጐዳ ተግባር በመቆጠብ ትልቅ ሚና መጫወት እንዳለባቸው አስታውቀዋል፡፡ አክለውም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፈለገውን ኃይማኖት ቢከተልም ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ነው፤ ይሄ ደግሞ ሁሉንም ዜጋ በሀገሩ ጉዳይ እኩል የመወሰንና የመጠቀም እንዲሁም ሀገርን የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

አቶ እስማኤል የተባሉ የአዲስ አበባ ነዋሪ በበኩላቸው አቶ መለስ በግል የስልጣን ፍፃሜያቸው መድረሱን በሚያሳዩአቸው አዳዲስ የጭንቀት ነፀብራቆች እየገለጹ እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ አቶ ይገረም በበኩላቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከዚህ በፊት በተለያየ ጊዜ ለእሳቸው የሚመቿቸውን በመሰብሰብ እስከዚህ ደርሰዋል፡፡ አሁን ግን ከጐናቸው የነበሩትን በሙሉ ጨርሰው ፋይዳቢሶችን አጥር ማድረጋቸው እምነትን ያሳደረባቸው አይመስልም፡፡ ምክንያቱም በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅመው ነበር፤ ዛሬ ግን ሊደግሟቸው ባለመቻላቸው "ክርስቶስ ለስጋው አደላ" ዓይነት ፍርሃትና ጭንቀታቸው መቋቋም ሲያቅታቸው ኤርትራውያን በብዛት ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ እያደረጉ ይላሉ፡፡

በተለይ አቶ መለስ "ለኤርትራ ጥቅም" በተደጋጋሚ መድከማቸውና በእናታቸው ኤርትራዊ መሆናቸውን እንደ አጋጣሚ እየተጠቀሙበት እንደሆነ የሚስማሙ ወገኖችም አሉ፡፡ በአሁኑ ወቅትም ከዚህ በፊት ከእናት ሀገራቸው "ኤርትራውያን ናችሁ" ተብለው በህወሓት የተባረሩት አብዛኞቹ ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ተደርገዋል፤ የመጡትም የበፊት ንብረቶቻቸውን እንዲወስዱ ተደርጐ ልጆቻቸውም ያለምንም ህጋዊ የምስክር ወረቀት በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች እንዲማሩ መደረጉንም ያነሳሉ፡፡ በብዛት በመቀሌ፣ በአዲስ አበባና ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ከኢትዮጵያውያን ዕድሉ ተነጥቆ በዜጐች በጀት ኤርትራውያን እንዲማሩ መደረጉ አቶ መለስ ከትግራይም ሆነ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ይልቅ ለኤርትራውያን ማድላታቸው ሽፋን ፈልገው ይሆናል ሲሉ አቶ ክፍሎም ይናገራሉ፡፡ እንደ አቶ ክፍሎም ገለፃ ከሆነ ኢትዮጵያውያን ኤርትራውያንን ሂዱ አላልንም፣ ዛሬም እንወዳቸዋለን፤ ነገር ግን ያሰቃዩአቸውና ያንከራተቱአቸው ወገኖቻቸው አቶ መለስና አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ ከነ ቡድኖቻቸው ጋር በመሆን ነው ሲሉ የሁለቱን ሀገር መሪዎች ይወቅሳሉ፡፡

ከአስመራ ወደ አዲስ አበባ ከመጡት ኤርትራውያን መካከል ሳሚ የተባለው ወጣት በአቶ መለስና በአቶ ኢሳይያስ ውሳኔና አገዛዝ እጅግ እንዳዘነ እና እንደተማረረ ይናገራል፡፡ በተለይ ሻዕቢያና ህወሓት የአረብ ቅጥረኞች ሆነው ሳለ እኛን የአረብ ባሪያ አደረጉን፤ ሳንፈልግም ዜግነታችን ተከፍሎ ኤርትራዊናችሁ አሉን፡፡ አሁን ደግሞ የአቶ መለስ ጀሌዎች ኤርትራ ሆነው ወደ ኢትዮጵያ ግቡ እያሉ ይሰብኩና ያሰቃዩናል ይላሉ፡፡ ነገር ግን አቶ መለስና አቶ ኢሳይያስ የሚያራምዱት አቋምም ሆነ የሚከተሉት ስልት አንድ ዓይነት ነው፤ ሁለቱንም ስልጣናቸውን ይጠባበቃሉ፤ ጦርነት ቢፈጠር እንኳ ሆን ብለው የስልጣን ዕድሜያቸውን ለማራዘም እንጂ ለህዝቡ ጥቅም አይደለም፤ ኤርትራና ኢትዮጵያ ተለያይተው የመጣው ጉዳት እንጂ ጥቅም እንደሌለው ለ19 ዓመታት አይተናል፡፡ በዚህም የኤርትራም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ተጐጂ ነው የሆነው፤ ቢቻልን ሁለቱ መሪዎች ካልተቻለም አንዱን አስወግዶ ዛሬውኑ የህዝብ ፈቃድ ቢጠየቅ ወዲያው የምንዋሀድ ይመስለኛል ሲል የተሰማውን ስሜት ገልፃዕል፡፡ አያይዞም አቶ መለስ እኛን ወደዚህ እንድንመጣ ያደረጉን ምናልባት ከትግራይና ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ እምነት ስላጡና ስለፈሩ ሊጠቀሙብን አስበው ይሆናል፤ እኛ ግን ለአረብ ባሪያ እንድንሆን ላደረገን ጨካኝ ግለሰብ መጠቀሚያ መሆን አንፈልግም ሲል አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡ አሁን በክፍዎች ሐሳብ ለሁለት የተከፈለው የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ አንድ ለመሆን መጣር አለበት፤ ተለያይተንም ያገኘነው ጥቅም የለም ሲሉ በቁጭት ተናግረዋል፡፡

የማነ የተባለ ወጣት በበኩሉ ከምፅዋ በባሩንቱ በኩል ወደ አዲስ አበባ መምጣቱን ገልፆ መንገዱን ያመቻቹትና የመሩት ሰዎች የኤርትራ አመራሮች እንደሆኑና ምክንያቱን እንደማያውቅ በመጠራጠር ወደ ሌላ የአፍሪካ ሀገር መሰደዱን አውግቷል፡፡ ሁለቱ መንግስታት መሪዎች (አቶ ኢሳይያስና አቶ መለስ ላይ) የስልጣን ማብቂያ ፍርሃትና ጭንቀት ማንዣበቡን እንደታዘበና አሁን እርስ በርስ በተለያየ ስልት በውስጥ ግንኙነት በመፍጠርና አንድ በመሆን ስልጣናቸውን ለማስጠበቅ እየጣሩ መሆኑን ያወሳል፡፡ ሁለቱም አውቀው ተቃዋሚዎችን በተቃራኒ እንደሚደግፍ እና እንደሚያደራጁ በመጠቆም አዲሱ የአቶ መለስ ዜናዊና የአቶ ኢሳይያስ ፍርሃትና ጭንቀት ያለቀለት መሆኑን አስታውሷል፡፡

# አቶ መለስ ውሸትን እውነት የማስመሰል ክህሎታቸው እየከዳቸው ነው !

ሰለሞን ስዩም

ሚያዚያ 9/2004 ዓ.ም አቶ መለስ ዜናዊ "በፓርላማቸው" የተለመደውን ‹‹የተጠየቁ›› ጥያቄዎችን ባሻቸው መንገድ የመመለስ ትርዒት አካሂደዋል፡፡ ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት የመንግሥታቸው አደጋ መሆኑ ክፉኛ ያሳሰባቸው ቢመስልም በተለመደው ሁኔታ በቃል ብቻ በማውገዝ አልፈዋል፡፡ ለነገሩ ከዚህ የሚዘሉ ከሆነ እርምጃው ከቤታቸው መጀመሩ ይቀራል? ነገር ግን ማውገዝ ብቻ የሚበቃው አይመስለኝም፡፡ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ያዘጋጀውን የኢህአዴግ ባለሥልጣናት የንብረት መዝገብ ለህዝብ ይፋ ይደረግ፡፡ በመጀመሪያ ፀረ ሙስና ኮሚሽን የመዘገበው ትክክል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ሕዝቡ ይመረምራል፡፡ ሕዝቡ በየዕለቱ ከሚያየው ጋር ያነፃፅረዋል፡፡ መረጃው ትክክል ሆኖ ከተገኘም በህገ ወጥ መንገድ የተገኘው ገንዘብና ንብረት ለህዝብ ተመልሶ ሌቦቹ ትክክለኛ ፍትህ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ አሁንም ወደ ቤታቸው ማምራቱ መች ይቀራል፡፡

አቶ መለስ መንግስት የዋጋ ንረቱን ለመቀነስም እየሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የሥራ ዉጤቱ ግን የለም፡፡ መሠረታዊ ዕቃዎችን መንግሥት ከውጭ ያስመጣል ብለዋል፡፡ ታዲያ ምን አይነት የኢኮኖሚ ስርዓት ነው የገነቡት? በማዕከላዊ ፕላን የሚመራ ወይስ በነፃ ገበያ የሚሰራ ነው? የዋጋ ንረት መንስዔዎችን አሁን አማካሪዎቹ በደንብ አይናገሩም እንዴ? በሀገራችን ዋናው የዋጋ ንረት መንስኤ ብሔራዊ ባንክ በገፍ እያሳተመ ለመንግሥት የሚያቀብለው ገንዘብና ሌሎች ባንኮች ለመንግሥት የሚያበድሩት ከፍተኛ ብድር ነው፡፡ ካድሬዎቹም ጠቅላይ ሚኒስትሩም ብዙ ጊዜ የሚጠቅሷቸው መንስኤዎች ዓበይት ሳይሆኑ ንዑሶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከውጭ የሚዛመት የዋጋ ንረትን አንድ መንስኤ ትጠቅሳላችሁ፡፡ ይህ ደግሞ በመንግሥት መረጃም ከ5 በመቶ በልጦ አያውቅም፡፡ በውጭ ምንዛሬ ከውጭ ሀገር እቃዎችን ማስመጣት ስለሚቻል ይህ በዋጋ ንረት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ኢምንት ነው፡፡

ምርት ሁለት አሀዝ (double digit) ዕድገት አሳይቷል ባላችሁበት አንደበት፣ የዋጋ ንረቱ አንደኛውና ዋናዉ መንስኤ የምርት አቅርቦት ማነስ ነው ትላላችሁ! ይህ ከሆነ ምርት በሁለት ድጂት ቀርቶ የአንድ ድጂት አጋማሽ ድረስ አላደገም ማለት እኮ ነው፡፡

ድፍረት ባይሆን እኔ ምክር ልስጥ፤ የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶችን ወጪ ቀንሱ፤ ብሔራዊ ባንክን ጨምሮ መንግሥት ከማንኛውም ባንክ የሚበደረውን ገንዘብ መቀነስ አሊያም ጨርሶ ማቆም አለበት፡፡ የወለድ መጠንን ከፍተኛ በሚባል መጠን መጨመር፡፡ አሁን ካለበት 5 በመቶ (በባንክ ተቀማጭ ገንዘብ ላይ) ወደ ስምንት በመቶ፣ ከዚያም ሁኔታው እየታየ ወደ አሥር በመቶና ከዚያ በላይ ቢሆን ከግሽበቱ የባሰ ተፅዕኖ አይኖረውም፡፡ ከተቀነሰው የልማት ፕሮጀክቶች ወጪ ላይ በተለይ የኑሮ ውድነቱ ለናጠው የመንግሥት ሰራተኛ ደመወዝ ማዋል፡፡ ነገር ግን አቶ መለስ ይህንን ማድረግ አይፈልጉም፡፡ ምክንያቱም ኑሮ የፈለገውን ያክል ቢወደድ የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች ለውጥ ካሳዩ በነፃ ምርጫ ያላገኙትን የሕዝብ ፖለቲካዊ ይሁንታ (legitimacy) ይሰጠኛል የሚል አቋም ያራምዳሉና፡፡

ለመምህራኑ የተደረገውን የደመወዝ እርከን ማስተካከያ በተመለከተ አቶ መለስ ከመምህራኑ 99.9 በመቶ ተቀብለውታል ነው ያሉት፡፡ ይህች የይሁንታ ምጣኔ ከ99.6 በመቶ መብለጧ በጣም አስገርሞኛል፡፡ ኢህአዴግ በ2002 ምርጫ በ99.6 በመቶ አሸንፌአለሁ ብሎ ነበር፡፡ ታዲያ 99.9 በመቶው በሚቀጥለው ዓመት እንደሚደረግ በሚጠበቀው በአዲስ አበባ ምርጫ የሚያሸንፍበት መጠን ይሆን? የአቶ መለስ ካድሬዎች እና ሰላዮች የደረሷቸዉ መረጃ በእጅጉ የተሳሳተ መሆኑን መግለፅ የዜግነት ግዴታዬ ይመስለኛል፡፡ ዘንድሮ "አዲስ ዘመንንም አዲስ ነገርንም አላነብም" የሚሉበት ጊዜ አይደለም፤ ለማንኛውም የደረስዎት መረጃ የተገላቢጦሽ ነው፡፡ መምህራኑ በተደረገው እጅግ አነስተኛ የደመወዝ ማስተካከያ 99.9 በመቶው ነው የበሸቁት፡፡ እውነቱን ለመናገር እኔ መምህር ብሆን የምበሽቀው በጭማሪው ብቻ ሳይሆን በደመወዙም ጭምር ነው፡፡ በአዲስ አበባ በ1300 ብር (የተጣራ) ደመወዝ ከወር እስከ ወር መድረስ ይቻላል? ይቻላል ከሆነ ከእውነታው እጅግ ርቀዋል ማለት ነው፡፡ እኔ በበኩሌ 1300 ብር ለአስር ቀን እንኳ አይበቃኝም፡፡ የጫትና የመጠጥ ሱስ ያለብኝ እንዳይመስል ታዲያ! አልጠጣም፣ አልቅምም፤ ደግሞም አላጨስም፡፡ ሌላው አስገራሚ ነገር "ከመቼ ወዲህ ነው ህብረተሰቡ መምህራንን መቅጠርና ማባረር የመጀመረዉ?›› አቶ መለስ ማስመሰል እያቃታቸው ነው፡፡

አቶ መለስ ስለ ሀይማኖት የተናገሩት ለአብዛኞቹ ወዳጆቹ አልጣማቸውም፡፡ ሙስሊሙ በኢትዮጵያ እስላማዊ መንግሥት እናቋቁም ሳይሆን ሙስሊሙ ሙጅሊሱን ይምረጥ፤ የአወሊያ ት/ቤቶችም መወሰን ያለባቸው በህዝብ በተመረጠ ሙጅሊስ መሆን አለበት የሚል መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ክርስቲያኖችም የሚጠይቁት ቢሆን ተመሳሳይ ነገር መሆኑን አብዛኛው ምዕመን ያነሳል፡፡ መንግሥት ባለፉት 20 ዓመታት በኃይማኖት ጉዳይ ያራመደው ፖሊሲ ዛሬ ሊከፋፍለን ፍንጭ በማሳየቱ ንፁህ ነኝ ማለት የቱ ጋ ነው?

አቶ መለስ ውሸትን እውነት የማስመሰል ብቃታቸው እንደከዳቸው ያወቅሁት የጉረፈርዳ ተፈናቃዮችን ባነሱበት ጊዜ ነው፡፡ የአማሮቹ መፈናቀል ተራራ የሚያህ እውነት ሆኖ ሳለ አቶ መለስ ለመቀበል መቸገራቸው ምን ይባላል? ደን ጨፈጨፉ ማለት ከቦታው ይፈናቀሉ ነው ወይስ በህግ ፊት ይቀርባሉ? ለነዚህ ሰዎች የቸገረዉ እኮ በራሳቸዉ ሀገር የሌላ ሉዓላዊ ሀገር ድንበር እንደጣሰ እዚያ መገኘታቸዉ በራሱ ወንጀል መሆኑ እኮ ነዉ፡፡ ለነገሩ ሰዉየዉ ማስመሰሉ ትቷቸዉ መብረሩን ያወቅሁት አንዱን ጉዳይ ብቻ መናገራቸዉን እየረሱ ሲደጋግሙትና ከአፋቸዉ ይልቅ በእጅ መናገር ማስቀደማቸዉን ሳይ ነዉ፡፡

# የኢህአዴግ ሰምና ወርቅ ፖለቲካ

ጎይቶም ሸዊት

ፖለቲካና ኮረንቲ በሩቁ ነው የሚል ጓደኛ አለኝ፡፡ ግን ከእኔ ጋር ሲሆን ፖለቲካን "በቅርቡ ይፈተፍተዋል" በቀደም ምን አለኝ መሰላችሁ፤ "የኢህአዴግ ነገር ይገርማል፤ዳቦ ሲሉት ግድብ" ብሎ በሳቅ ተንፈራፈረ፡፡ አባባሉ አንድ አዲስ ሃሣብ አጫረብኝ፡፡ ኢህአዴግ የሚናገረው በሰምና ወርቅ የሆን እንዴ ብዬ አሰብኩ፡፡ ግድቡ ሰም ነው ወርቁ? ግድብ ወርቅ ቢሆን ኖሮ፣እንዲህ በግልፅ አይናገርም ነበር፡፡ ግድብ ልማትን ይወክላል፡፡ ስለዚህ ልማት ሰም መሆን አለበት፤ግን የሸፈነው ወርቅ ምን ይሆን?

ኢህአዴግ ራሱ ሰም ነው፡፡ የሕወሓት ሰም፡፡ በዚህ አግባብ ወርቁ ሕወሓት ነው፡፡ የሚገርመው ሕወሓት ራሱ በተራው ሰም ይሆንና ሌላ ነገር ይሸፍናል፡፡ ሕወሓት የአቶ መለስ ዜናዊ መሸፈኛ ሰም ከሆነ ጥቂት ዓመታትን አስቆጥሯል፤በተለይ ከ1993ቱ የሕወሓት መሰንጠቅ ጀምሮ፡፡ አቶ መለስ ዜናዊ ራሳቸው የሌላ ነገር መሸፈኛ ሰም ናቸው ብላችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ? ባይገርማችሁ፣አቶ መለስ የሻዕቢያ ሽፋን ሰም ናቸው ብዬ አምናለሁ፡፡ አሁንስ አይበቃም? አይበቃም፤ ሻዕቢያ ራሱ የሲ.አይ.ኤ. (CIA) ሽፋን ድርጅት ነው!

መንግሥቱ ኃ/ማርያም አወቁትም፣አላወቁትም፣በሲ.አይ.ኤ እና በሻዕቢያ ቁጥጥር ሥር ነበሩ! ኤርትራዊውን ዶ/ር አማረ ተክሌን የቅርብ አማካሪ አደረጉ፤ሌላውን ኤርትራዊ ብርጋዴዬር ጄነራል መስፍን ገብረቃልን ደግሞ ምክትል ኢታማጆር ሹም አድርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሎ ሻዕቢያን በናቅፋ ተራራ ላይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዳይደመሰሰው፣ኮ/ል መንግሥቱ ጦርነቱን አስቁመውታል! ኮሎኔሉ እነ ጀነራል ታሪኩ ላይኔን ረሸነዋል! አስረሸነዋል? ኢትዮጵያን ከማጥፋት ለማዳን የተንቀሳቀሱትን የግንቦት 8 (1981) መፈንቅለ መንግሥት ምርጥ መሪ ጀነራሎችን አስረሸነዋል! ያኔ ሻዕቢያ ሻፓኝ ከፍቶ ደንኪራ ይረግጥ ነበር! እኔ ደግሞ እውነተኛ ብሩህ አእምሮ የነበረውና ከሳንድኸርስት የእንግሊዝ የጦር አካዳሚ በአንደኝነት የተመረቀው የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ብርጋዴዬር ጀነራል ተስፋዬ ትርፌ ከተረሸኑት ምርጥ ጀነራሎች መካከል አንዱመሆኑን ሰምቼ በድንጋጤና በሐዘን ተውጬ ነበር! በጥቁር ዘርን በዓለም መድረክ ላይ ያስከበረው ጓደኛዬ ከንግሥት ኤልሣቤጥ የክብር ሻምላውን ሲቀበል፣አፍሪካውያኑን ብቻ ሳይሆን ነጮቹንም አስደምሟል፡፡ ትምህርት ቤት ሆነን ተስፋዬ ትርፌ አንድ ሰዓት ከሠላሳ ደቂቃ የተመደበለትን ፈትና በአርባ ደቂቃ ጨርሶ የመልስ ወረቀቱን ለአስተማሪው ሰጥቶ ከክፍል ሲወጣ እኛ የክፍል ጓደኞቹ ቢበዛ የፈተናውን ግማሽ ያህል ነበር የምናጠናቅቀው፡፡ እንግዲህ፣መንግሥቱ ኃ/ማርያም ያስረሸኑት እነዚህን የመሳሰሉ ምርጥ ጀነራሎችን ነበር፡፡ መንግሥቱ ኃ/ማርያም አወቁትም፣አላወቁትም የሻዕቢያን ድል እያመቻቹ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በመጨረሻም ለዚህ ውለታቸው ሲ.አይ.ኤ. በዝምባብዌ ጥገኝነት አግኝተው በአንፃራዊ ድሎትና ሠላም እንዲኖሩ አድርጓቸዋል!

አቶ መለስ ግድብ ሲሉ ልማት ማለታቸው ነው፡፡ ልማት የምን ሽፋን ነው? ልማት አምባገነንነትን ለመሸፈን የሚያገለግል ካባ ነው፡፡ የፖለቲካ ቅሌትን በኢኮኖሚ ልማት ለመጋረድ የሚከወን ትርኢት ነው! የይስሙላ ምርጫዎችን፣ከሕግ ውጪ የሚፈፀሙ ግድያዎችን፣እሥራትን፣ድብደባን፣የሰቆቃ ተግባራትን፣ከሥራና ከደመወዝ ማገድን፣ሙስናን፣ወዘተ. በልማት ሽፋን ለመደበቅ ኢህአዴግ እየሞከረ ነው፡፡ መጋቢት 22 ቀን 2004 ዓ.ም ጠ/ሚኒስትር ስለ አባይ ግድብ በቴሌቪዥን ማብራሪያና መግለጫ ሲሰጡ፣ለጥቂት ደቂቃዎች ሰማኋቸው፤አዳመጥኳቸው፡፡ የሀገሪቱ ጠ/ሚኒስትር የሆኑት አቶ መለስ ስለ አንድ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ዝርዝር ቴክኒካዊ ጉዳዮች ውስጥ ገብተው፣የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ሁሉ ለመመለስ መሞከራቸው በጣም ስለገረመኝ፣ኢቴቪን አጥፍቼ ወደ አልጀዚራ አዞርኩት፡፡ አቶ ምህረት ደበበ ሊሠሩ የሚችሉትን ሥራ ጠ/ሚኒስትሩ እንደ ሁነኛ የግድብ እና የኤሌክትሪክ ኢንጅነር የማይመለከቷቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ መሞከራቸው ምን ለመሸፈን ነው? በርካታ አንገብጋቢ ሀገራዊ ጉዳዮች ከፊታቸው ተደቅነው፣ስለ አንድ የልማት ፕሮጀክት ይኼን ያህል መጨነቃቸው ከምን የመጣ ነው? እንደ ጠ/ሚኒስትር እሳቸውን ሊያሳስቡ የሚችሉት ጥያቄዎች እየተባባሰ የመጣው የዋጋንረት፣የሙስሊሙ ሕብረተሰብ የመብት ጥያቄ፣የመምህራኑ የደመወዝ ጥያቄ፣ሥራ አጥነት፣ሙስና፣የመጠጥ ውሃ እና የመኖሪያ ቤት ችግር፣የዜጎች መፈናቀል፣የገዳማት መታረስና መቃጠል፣በኤርትራ ግዛት ውስጥ የተሰነዘረው ወታደራዊ ጥቃት አንድምታ፣በሱማሊያ እየተካሄደ ያለው የኢትዮጵያ ሠራዊት ጣልቃ ገብነት፣በሐሰት ውንጀላ የታሠሩት ዜጐች ሁኔታ፣ወዘተ. ናቸው ብዬ እገመታለሁ፡፡

ልማት ኢትዮጵያን ከመድረ ገፅ ለማጥፋት ለተሸረበው ሤራ ሽፋን ነው፤ ሰም ነው፡፡ ወርቁ ሙስና ነው፤ወርቁ ኢትዮጰያን ለማጥፋት የታቀደውን እኩይ ሴራ ማፋጠን ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ሕወሓት/ኢህአዴግ ‹‹ኦሮሚያ›› እያለ የሚጠራው የጐሣ ክልል የራሱ የኃይለ ማመንጫ ግድብ ካለው ፣ የራሱ የሲሚንቶ ፋብሪካ ካለው፣የራሱ የመስኖ ግድብ ካለው፣መንገዶች ከተሠሩለት፣ባንኮች ከተቋቋሙለት፣በራሱ ቋንቋ ከተናገረ፣በራሱ ፓርላማ ካለው፣የራሱ ባንዲራ ከተሰጠው፣የራሱ ፖሊስ ኃይል ካለው፣ወዘተ. ሕወሓት/ኢህአዴግ የክልሉን መገንጠል አፋጠነ ማለት አይደለምን? ሕወሓት/ኢህአዴግ የሚያካሂደው የልማት ሥራ ይህንን ዓቢይ ዓላማ ለማፋጠን ነው፡፡ ይህ ዓላማ ደግሞ የሕወሓት ዓላማ አይመስለኝም፡፡ ዓላማው ሕወሓት በሽፋንነት የሚያገለግለው የሻዕቢያ ብሎም የሲ.አይ.ኤ ዓላማ ነው!

ኢትዮጵያን የምንወድ ዜጐች መጀመሪያ ማረጋገጥ የምንፈልገው የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ ሕልውና ነው! በዚህም ምክንያት ቅድሚያ የምንሰጠው ለልማት ሳይሆን፣ለፖለቲካ ጥያቄ ነው፡፡ በመሆኑም፣ሕወሓት/ኢህአዴግ ልማት የሚለው ኢትዮጵያን ለመበታተን ለተሸረበው ሤራ ሽፋን (ሰም) ነው ብለን እናምናለን፡፡ የኢህአዴግን የፖለቲካ ሰምና ወርቅ በሚገባ ካልተገነዘብን፣ሳናውቀው ውድ ሀገራችንን በማጥፋት እየተባበርን ልንሆን እንችላለንና መጠንቀቁ አይከፋም፡፡ ሻዕቢያ የኢትዮጵያ መጠናከር የኤርትራን ሕልውና ይፈታተናል ብሎ ስለሚያስብ፣መዳረሻ ዓላማው አድርጐ የሚንቀሳቀሰው ኢትዮጵያን ከዓለም ካርታ ማስፋቅ ነው! ይህን የሻዕቢያን ዓላማ ለማሳካት የሚሞክረው ደግሞ በሕወሓት ውስጥ ሰርጐ የባው የሻዕቢያ ቡድን ነው! ያልጠረጠረ ተመነጠረ እንል የለ እንዴ?

በበኩሌ፣አንድ ትልቅ ተስፋ የሚሠጠ ኝ ጉዳይ አለ፡፡ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቢያንስ ሰማኒያ በመቶ ያክሉ ኢትዮጵያ እንድትጠፋ አይፈልግም፡፡ የኢትዮጵያን እንደ ቀድሞዋ ዩጐዝላቪያ ከዓለም ካርታ መፋቅን የሚቃወሙት ብሔረሰቦች ቁጥር ከፍተኛ ነው፡፡ የደቡብ ሕዝብ የኢትዮጵያን መገነጣጠል ፈፅሞ አይፈልግም፡፡ አማራ መቶ በመቶ የኤትዮጵያን መጥፋት ይቃወማል፡፡ የትግራይ ሕዝብ ቢበዛ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት የጠይቅ እንደሆን እንጂ፣ኢትዮጵያን ፈፅሞ የሚከዳ አይደለም፡፡ ከኦሮሞ ሕዝብ ቢያንስ ሃምሣ በመቶው የኢትዮጵያን መጥፋት አይፈልግም፡፡ ይህንን ስንደማምረው፣የኢትዮጵያን መጥፋት የማይፈልገው ሕዝብ ብዛት ከሰማኒየ በመቶ አያንስም! በመሆኑም፣አሁን ሥልጣን ላይ ቁጢጥ ብለው የኢትዮጵያን መጥፋት ለማፋጠን የሚዳክሩት ኃይሎች አናሳዎቹ ናቸው! ግን አናሳዎቹ ለሥልጣን እንዴት በቁ? ሠራዊቱን፣ደህንነትን እና ፖሊስን እንዴት ሊቆጣጠሩ ቻሉ? በእኔ ግምት እነዚህ ሁሉ በሽፍጥ ፖለቲካ እና በጥቅም የተደለሉ ተቋማት ናቸው! የሕወሓት/ኢህአዴግን የሰምና ወርቅ ፖለቲካ መፍታት ቀላል አይደለም፡፡ አቶ ኢሣያስ አፈወርቂ በራሳቸው "ሀገር" የሚያወግዙትን የብሔረሰብ ክልል ፅንሰ ሃሣብ በኢትዮጵያ እንዲተገበር ለምን ፈቀዱ? የዋሆች ለዚህ የሚሰጡት መልስ ኢትዮጵያ የሳቸው ሀገር አይደለችም፤ በሰው ሀገር ምን አገባቸው? የሚል ነው፡፡ ግን አቶ መለስ በኢትዮጵያ የሻዕቢያ ተጠሪ አለመሆናቸውን ለማሳየት ከሚቀርበው ማስረጃ ይልቅ፣ወኪል መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚቀርበው ማስረጃ በእጅጉ ሚዛን ይደፋል? ቅንጣት ታክል ኢትዮጵያዊ ስሜት ቢኖራቸው ኖሮ፣አሰብ ወደብን አሳልፈው ለሻዕቢያ ይሰጡ ነበርን? የጐሣ ክልል ፅንሰ ሃሣብ በመጨረሻ ኢትዮጵያን እንደሚያጠፋ ሳየውቁ ቀርተው ነው፡፡ በእኛ ኢትዮጵያውያን ላይ የጫኑብን? በዓለም የለለ የመገንጠል መብት በሕገመንግሥቱ ውስጥ ያስገቡት ኢትዮጵያን ስለሚወዱ ይመስላችኋል?

ለዚህም ነው የዛሬውን ርእሴን "የኢህአዴግ የሰምና ወርቅ ፖለቲካ" ያልኩት አቶ መለስ የሻዕቢያ ሽፋን (ሰም) ናቸው! በ1993 ሕወሓት ከሁለት ሲሰነጠቅ፣የነበረው ፍልሚያ በ "ቫይረሶች"እና በ "አንቲ-ቫይረሶቹ" ደግሞ አፍቃሪ-ኢትዮጵያ የሆኑት የትግራይ ልጆችና የሌሎች ብሔረሰቦች አባላት ነበሩ፡፡ "አንቲ-ቫይረሶቹ" በጦር ሜዳ ሻዕቢያን ድባቅ መተው ሲመለሱ፣ጦርነቱን ሲቃወሙ የነበሩት "ቫይረሶች" ከቤት ሳይወጡ "አንቲ ቫይረሶቹን" ከሥልጣን አባረሯቸው! እጅግ አስገራሚ የታሪክ ምፀት የሏል ይህ ነው! ግን ለሲ.አይ.ኤ. ምን ይሳነዋል?

ለማጠቃለል፣የኢትዮጵያን ሕልውና ከምድረ ገፅ ለማጥፋት እየሠራ ያለው በሕወሓት ውስጥ የተደበቀውና የበላይነቱን የያዘው የሻዕቢያ ቡድን ነው! እንዲያውም እንደሚወራው ከሆነ፣ይህ ቡድን ሕወሓትን ራሱን እያጠፋው ነው! ኢትዮጵያን የሚወዱ ወገኖች በሙሉ ይህን ሁኔታ ለመቀየር ብርቱ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በሕወሓት/ኢህአዴግ ሰምና ወርቅ ፖለቲካ መደናገር የለብንም፡፡ የኢትዮጵያ ሕልውና ከልማት መቅደም እንዳለበት ግልፅ ነው፡፡ አሁን ባለው የፖለቲካ ሁኔታ ልማት ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተቀየሰው ስልት ሽፋን (ሰም) ነው! የዋሆቹ የኢትዮጵያ አርቲስቶች "ልማት ለማት" "ግድብ ግድብ" እያሉ ማቀንቀናቸውና ዳንኪራ መርገጣቸው ሊያሳስበን ይገባል፡፡ እነዚህ በሕዝቡ ዘንድ ያላቸውን ታዋቂነት ተጠቅመው፣ራሳቸው ተታልለው ሕዝቡን ሊያታልሉት ይችላሉ! ራሳቸው ተታልለው ሕዝቡን እንዳያታልሉት መጠንቀቅ ይገባናል፡፡ በዘመነ መለስ ልማት የአምባገነንነት ሽፋን ነው፡፡ አምባገነንነትን የሚፈልጉት ደግሞ ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈቃድ ውጪ የኢትዮጵያ መንግሥት (the state of Ethiopia) እንዲከስም ለማድረግ ነው! እስከዛው ግን "ቫይረሶቹ" በሙስና ከፍተኛ ሀብት እየዘረፉ ከሀገር በማሸሽ፣ወደፊትም ተንደላቅቀው ለመኖር እንደሚፈልጉ መርሳት የለብንም! የኢህአዴግን የሰምና ወርቅ ፖለቲካ በሚገባ ተገንዝበን ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን በሕብረት እንነሳ!

## አቶ መለስ ይፋ ያደረጉት . . .

ከገፅ 3 የዞረ

በርከን ማስተካከያው ደስተኛ ናቸው ይሉናል፡፡ በርካታ መምህራን በዚህ አህዛቸው ተበሳጭተዋል፡፡ ምናልባትም የተገላቢጦሽ በደመወዙ ያልተደሰተው 99.9% ይሆናል ይላሉ፡፡

እንደ አቶ መለስ ከሆነ በሀገሪቱ ካሉት ወደ 400.000 የሚሆኑ መምህራን ውስጥ ወደ 500 የሚሆኑት ብቻ በማስተካከያው አልተደሰቱም፡፡ እናም አቶ መለስ እነዚህኑ የደመወዝ ጭማሪ ጠያቂዎች "የማስተማር ብቃትና ፍላጐት የሌላቸው ናቸው፡፡" ይላሉ፡፡ "በተማሪዎችና በወላጆቻቸው የማስተማር ብቃት የሌላቸው ናቸው ተብለው በሌሎች መምህራን እንዲተኩ ጥያቄ ሲቀርብ መልስ አለመስጠታችን ነው ስህተቱ፡፡" በማለት ለማብራራት ይሞክራሉ፡፡

"የማስተማር ፍላጐትና ብቃት የሌላቸው፡፡" የሚለውን አስምሩልኝ፡፡ አቶ መለስ ይፋ ያደረጉት የመምህራን ማባረሪያ ስትራቴጂም ይሄው ነው፡፡ ሰውየው ዝም ብለው አልተናገሩትም፡፡ ለእያንዳንዱ የስርዓታቸው ተቃዋሚና ተቺ የማጥቂያ ስልት በማበጀት የተካኑ ናቸው፡፡ ሁሌም እጅ ለመጠምዘዝ መጠመዘዣ ስልት ያበጃሉ፡፡ እነሆም የመምህራኑ የመሞቻ ስልት ይፋ ሆነ፡፡ "ችሎታ የሌላቸው . . ." የሚል፡፡

ለፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች "ሽብርተኛ" የሚል ወጥመድ እንደተበጀላቸው ሁሉ የመብት ጥያቄ እያነሱ ለሚያስቸግሯቸው መምህራን ደግሞ "የማስተማር ብቃት የሌለው እና በወላጆችና ተማሪዎች ጥያቄ የተባረረ፡፡" በሚል አዲስ ቀይ ካርድ እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡ ስለዚህ ነው አቶ መለስ "አባሯቸው ስንባል ዝም ማለታችን ነው ጥፋቱ" የሚሉት፡፡ ጠ/ሚኒስትሩ ይፋ ያደረጉት ስትራቴጂም ይሄው ነው፡፡

መምህር ቁመላቸው የማስተማር ነፃነትን በተፃረረ መልኩ መምህሩ ተማሪ መስሎ በተቀመጠ ካድሬ ይመረጃል፡፡ ይገመገማል፡፡ መጪው ጊዜ የባሰ ጠቁሮና ከስሎ ተሰማው፡፡ ይሄንም በጠ/ሚኒስትር መለስ ንግግር ጉበት የመሰለ ፊቱ ያሳብቅ ነበር፡፡ ግን ግን መጪው ጊዜ ምን ይሆን?

## ዴሞክራሲን ማምጣት ያቃተው . . .

ከገፅ 3 የዞረ

እስከ ምሽት የሚወራለት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ኮስማና ነው፡፡ ኮስማና ቁሳዊ ልማት የሕዝብ መውደድን አይገዛም፡፡ ልማታዊ መንግሥት ልማታዊ ባለሀብት፤ ልማታዊ አርሶአደር፣ ልማታዊ ጋዜጠኛ፣ ልማታዊ አርቲስት፣ ልማቲዊ ወዘተ ቢሉ የሕዝብ መውደድ፣ የሕዝብ ልብ አይገዛም፡፡

በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ ለምሳሌ የጠቀስኩት ሀብታሙ አቶ ሀብታሙ ማፍቀር ባለመቻሉ ፍቅርን አጥቷል፡፡ የኢህአዴግ መንግሥትም ይህን አደረግኩልህ ያን አደረግኩልህ፤ ይህን አሳደግኩልህ፣ ያን አሰፋሁልህ እያለ የቁሳዊ ልማት ዝርዝር በማነብነብና ከዚህ በላይ ምን ትፈልጋለህ? በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ልቡን እንዲሰጠው ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡ ግን "ይቀራል!" ይላል፡፡ የሚቀረው ነፃነት ነው፡፡ የሚቀረው ዴሞክራሲ ነው፡፡ ሌላም ሌላም ብዙ የሚቀር ነገር አለ፡፡ ቁሳዊ ልማት ብቻውን የኢትዮጵያ ሕዝብን ልብ አይገዛም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ የሚገዛው የተሟላ ልማት ነው፡፡ የተሟላ ልማት መሠረቱ ደግሞ ነፃነት ነው፤

በነገራችን ላይ አቶ መለስ ዜናዊ በ2002 ምርጫ ማግሥት መስቀል አደባባይ ለወጣው የኢህአዴግ ታሪካዊ ሠልፈኛ በአደረጉት ታሪካዊ ንግግር ፓርቲያቸው በምርጫው በ99.6 በመቶ ማሸነፉ በልማቱ የሕዝቡን ልብ የመግዛቱ ማስረጃ ነው ብለዋል፡፡ የሕዝቡ ልብ ተሰረቀ እንጂ አልተገዛም፡፡

# የአርበኞች ማህበር በሙስና ታምሷል ተባለ

- "አመራሩ በሙስና ተዘፍቋል"
- "አርበኞች በረሃብ እያለቁ ናቸው"
- "ማህበሩ በህገ ደንቡ እየተመራ አይደለም"
- "ማህበሩን የሙሰኞች ቡድን ተቆጣጥሮታል"

"የጥንት የኢትዮጵያ አርበኞች ማህበር ጥቂት አመራር አባላት በቡድን ተደራጅተው ከፍተኛ ሙስና እየተፈፀመ ከመሆኑም በላይ አመራሩ ለአቅመ ደካማ አርበኞች በስማቸው የሚመጣውን ርዳታ በአግባቡ እያከፋፈለ ባለመሆኑ አረጋውያን በረሃብ እያለቁ ናቸው፡፡" ሲሉ የማህበሩ አባላት ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ፡፡

የማህበሩ አባላት ዝግጅት ክፍላችን ድረስ በመምጣት በያዙት ሰነድ በመደገፍ እንደሚያስረዱት ከሆነ በርካታ የምዝበራ ተግባራትን ያብራራሉ፡፡ አባላቱ በመነሻነት የገለጹት የማህበሩን ገቢ በማስረዳት ነው፡፡ ገቢውን ሲዘረዝሩ "ደርግ የወረሰብንን ቤቶች ኢህአዴግ መልሶልናል፡፡ የተመለሰልን ቤት በዓመት 840 ሺ ብር የሚከራይ ሲሆን 240 ሺውን የተወሰኑ የአመራር አባላት ለግል እየተከፈፈሉት 600 ሺውን ብቻ ለማህበሩ ገቢ እንዲሆን አድርገዋል፡፡ ማህበሩ የኪራይ አከራይ ግብር ለመክፈል ሲኬድ የ840 ሺ ብር ኪራይን 600 ሺ ብር ተብሎ በመመዝገቡ በማህበሩ ላይ 70 ሺ ብር ቅጣት ተወስኖበታል፡፡ ቀደም ሲል ማህበሩ ከመንግሥት በዓመት 500 ሺ ብር ድጐማ እናገኝ የበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በዓመት አራት ሚሊዮን ብር ይሰጠናል፡፡ መንግሥት ሦስት መኪና ሰጥቶናል፡፡ ከተለያዩ አካላት የድጋፍ ርዳታ ይመጣል፡፡ ሆኖም ግን ለአባላቱ አይደርስም፡፡" በማለት በቁጭትና በሐዘን ይገልጹታል፡፡

አባላቱ እንደሚሉት "የማህበሩን ገቢ አረጋውያን የማህበሩ አባላትና ወራሽ ልጆቻቸው ሳይሆኑ ጥቂት በሙስና የተባ ደኑ የማህበሩ አመራር ለግላቸው እየተካፋፈሉ ለየግላቸው ፎቅ እየገነቡ ናቸው፡፡ ለመኪና ማስጠገኛ፣ ለነዳጅ እየተባለ በዓመት በጀት በመበጀትና በየወሩና በየዕለቱ ሌላ ተጨማሪ ወጪ በማውጣት ከፍተኛ ምዝበራ ይከናወናል፡፡ ዝቅተኛው የአባላቱ ወራዊ ድጐማ በወር 150 ብር ሲሆን አመራሩ በወር ከ2 (ሁለት) ሺ እስከ ስድስት ሺ ብር ይከፋፈላሉ፡፡ ምንም ዓይነት ድጐማ የማያገኙ አባላት አሉ፡፡ 29 አባላት የድጐማ ጭማሪ ተከልክለዋል፡፡ ለአንድ ወር ሥራ ማስኬጃ ብለው አንድ ሚሊዮን ብር ወጪ አድርገው ለግል ጥቅም አውለውታል፡፡ ለሥራ ጉዳይ እያሉ ያለ ምንም ሥራ ወደ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች እየሄዱ ከዋናው መ/ቤትና ከቅርንጫፍ መ/ቤቱ ሁለት ጊዜ አበል ይቀበላሉ፡፡ ፕሬዝዳንቱ ሥራም ካለ በመኪና መንቀሳቀስ ሲገባቸው፤ለአውሮፕላን ትኬት መግዣ ለአበል እያሉ በረሃብና በእርዛት ከሚሰቃዩ አረጋውያን አርበኞች አፍ እየነጠቁ ለግል መዝናኛቸው እያዋሉት ነው፡፡ ለፕሬዘዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ስጦታ፣ለሙክት መግዣ፣ለውስኪ መግዣና ለሽልማት ተብሎ 4900 ብር ወጪ ሆኗል፡፡ ስጦታው አባላት ተወያይተውበትና አምነውበት ቢሰጥ ተቃውሞ የለንም፡፡ ለእሳቸው ተሰጥቷል ብለንም አናምንም፡፡ በስማቸው ግን ምዝበራ ተከናውኗል፡፡ በብጹህ ፓትርያርኩ ስም ገንዘብ ወጪ ተዳርጐ ተበልቷል፡፡ በመሠራት ላይ ባለው ህንፃ ስም ከፍተኛ ሙስና እየተፈፀመ ነው፡፡ በህንፃው ስም ሦስት የተለያዩ ውሎች ተደርገዋል፡፡ ከውሉ በላይ ቅድሚያ ክፍያ እየተባለ ወጪ ተደርጐ ተሰጥቷል፡፡ አሁንም ተጨማሪ ብር 700 ሺ እንዲወጣ ታዟል፡፡ ይህ ህንጻ የመላው አገሪቱ ህዝብ ንብረት ነው፡፡ የቀድሞ ሂሳብ ሹም የማህበሩን ገንዘብ ዘርፋ አሜሪካን እንድትገባ አመራሩ አመቻችቷል፡፡" በማለት በርካታ ማስረጃዎችን በመደርደር ያስረዳሉ፡፡

ጉዳዩን ለጠ/ሚኒስትሩ ጽ/ቤት፣ ለፀረ-ሙስና፣ለፖሊስ፣ለማህበራዊ ሚኒስቴር፣ለፕሬዝደንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስና ለሚመለከታቸው አካላት በሙሉ አሳውቀናል፡፡ የሚሉት የማህበሩ አባላት እየደረሰብን ነው ያሉትን በደል በስፋትና በምሬት ይገልጹታል፡፡ "ማህበሩ በህገ ደንቡ መሠረት ጠቅላላ ጉባዔውን አያደርግም፡፡ አመራሩ የምርጫ ዘመኑን ጨርሶ በጉልበትና በሙስና ሥልጣኑን ይዞ ተቀምጧል፡፡ አብዛኛው የማህበሩ አባላት በእርጅና አይናቸው የማያይና የደከመ ጆሯቸው የማይሰማ በመሆኑ በስማቸው እየተፈፀመ ያለውን አያውቁም፡፡ የማህበሩ ፕሬዝዳንት ከህግ በላይ ሆነው ጥቂት የዝርፊያ ቡድን አቋቁመው በአምባገነንነትና በማን አለብኝነት ከፍተኛ ወንጀል እየፈፀሙ ናቸው፡፡ መንግሥት ጩኸታችንና አቤቱታችንን ሊሰማን ይገባል፡፡ ወንጀለኞች በህግ ሊጠየቁ ይገባል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ለአቅመ ደካማ አረጋውያን 25 የኮንዶሚኒየም ቤት በነፃ ተሰጥቷል፡፡ ለአባላቱ አልደረሰም፡፡ አመራሩ ሽጦ ለውጦ ለጥቂት አመራሮች ተከፋፍለውታል፡፡" ሲሉ ይዘረዝራሉ፡፡

አቤቱታ አቅራቢዎቹ አባላት ስለማህበሩ አባላት ሲናገሩ "በርካታ የማህበሩ አባላት በኑሮ ውድነቱ በረሃብና በችግር እየተጐሳቆሉ ናቸው፡፡ በቅርቡ አቶ ብሩ ያለውና አቶ ውብነህ አበራ የተባሉ የማህበሩ አባላት በረሃብ ሞተዋል፡፡ በርካታ የማህበሩ አባላት ዛሬም በረሃብ እየተሰቃዩ ናቸው፡፡ በስማቸው የሚመጣውን ገንዘብ አይሰጣቸውም፡፡ በ2000 ዓ.ም ከአዲስ አበባ መስተዳድር ለማህበሩ 1643 ሺ ብር ቢሰጥም ለአባላቱ አልደረሰም፡፡ የኦሮሚያ መንግሥት ለአርበኞች መጦሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ቢሰጠንም የማህበሩ አመራሮች ግንባታውን አስቁመዋል፡፡ ምን አርበኛ አለ፡፡ አርበኛው አልቋል፡፡ አርፋችሁ ተቀመጡ፤አያገባችሁም፡፡ እያሉ ያንጓጥጡናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአርበኛው ስም ገንዘብ እየተቀበሉ ለግል ጥቅም ያውላሉ፡፡" ካሉ በኋላ በመጨረሻ የሚመለከተው ሁሉ የማህበሩ አባላት ላይ እየደረሰብን የለውን ግፍና በደል ሰምታችሁ ርዱን፡፡ እኛ አቅመ ደካማ ነን፡፡ ጉልበተኞች በራሳችን ገንዘብ ኃላፊዎችን በገንዘብ በመያዝ ለችግር ተጋልጠናል፡፡ ህይወታችንን አትርፏት፡፡ ለአገራችን የደከምን፤የደማን፤ የቆሰልን ነን፡፡ ከመሃላችን የወጡ ሙሰኞች ቆዳችንን ገፈው ርቃናችንን አስቀሩን፡፡ የማህበሩ ገንዘብና ንብረት የእኛ ብቻ ሳይሆን የመላው አገሪቱ ዜጐች ነው፡፡ ሁሉንም ይመለከታል፡፡ ህንፃውንም ገንብቶ ለመጨረስ ወጣቱም፣ የመከላከያ ሠራዊቱም፣የፖሊስ ሠራዊቱም ይመለከተዋል፡፡ ነገ የእነሱ ንብረት ነው፡፡ በህንፃው ስም አመራሩ ከባንክ ገንዘብ የተበደረው ህንፃውን ለሌላ ዕዳ እየዳረገ ነው፡፡ ሁላችሁም ንብረታችሁን ከዕዳ አድኑት" ሲሉ ጥሪያቸውን በማቅረብ ሐሳባቸውን ደምድመዋል፡፡ ከማህበሩ ፕሬዚዴንት ሀሳብ እንዲሰጡበት ያደረግነዉ ጥረት በወቅታዊ ጤንነታቸዉ ሳይሳካ ቀርቷል፡፡

# የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን የረሷቸው መሪ

በብሩክ ከበደ

የኢ/ፌ/ዴ/ሪ/ፕሬዝዳንት የሆኑት ክብር ፕሬዝደንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ በህክምና ምክንያት ከአገር ከወጡ ወራትን እያስቆጠሩ ነው፡፡

ፕሬዝዳንቱ በሳንባ ምችና በስኳር ህመም ምክንያት በሃገር ውስጥ በሚገኙት ጦር ኃይሎችና የኮሪያ ዘማቾች መታሰቢያ ሆስፒታል ህክምናቸውን እየተከታተሉ ቢቆዩም ሌላ የተሻለ ህክምና ለማግኘት ወደ ሳዑዲአረቢያ መጓዛቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ፕሬዝዳንቱም ከሃገር ከወጡ ጥቂት ቀናት በኋላ አርፈዋል የሚል ጭምጭምታ በአዲስ አበባ እንደተናፈሰ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በዜና እውጃው ላይና በህትመት ዳሰሳ ፕሮግራሙ የሃሰት ወሬ ነው ሲል ማስተባበያ ከመስጠቱ ውጪ የፕሬዝዳንቱ ጤንነት በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ እስከ ዛሬ የዘገበው ነገር አለመኖሩ ሰሞኑን በከተማ ውስጥ የመነጋገሪያ ርዕስ ከፍቷል፡፡

ሁኔታውንም በቅርብ የታዘቡ አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የተፎካካሪ ፓርቲ አባል እኚህ ሰው እስከ ዛሬ አገር አልመሩም እንዴ? ሲሉ የቀረበላቸውን ጥያቄ መልሰው ይጠይቃሉ፡፡ ሌላ በንግድ ሥራ የተሰማሩ ግለ ሰብም የአንድ አገር መሪ ሲታመም በየቀኑ ሆስፒታል ስላለው ሁኔታ የሃገሩ ሚዲያ በምስል የተደገፈ ዘገባ ማቅረብ የተለመደ ነው፡፡ ለዚህም የቬንዙዌላው ሁጐቻቬዝና የኩባው ፊደል ካስትሮ በታመሙ ጊዜ የነበራቸውን ሽፋን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የኛው መሪ ግን እሳቸውም እንደ ሕዝባቸው መረሳታቸው ያስገርማል ብለዋል፡፡

ሌላው እንደ በፊተኞች ሁሉ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ጡረተኛ ለየት ያለ መልስ ሰተውኛል፡፡ እሳቸው (ፕሬዝዳንቱን ማለታቸው ነው) በአገሬ ጉዳይ ሲናገሩም ሆነ ሲያናግሩ አይቻቸው ስለማላውቅ በውስጤ ምንም ትዝታ የለኝም፡፡ አስታውሻቸውም አላውቅም፡፡ ይህ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስሜት በሙሉ ይመስለኛል ብለዋል፡፡

## ዶ/ር ፍሰሃ እሸቱ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ሽግግር ም/ቤት ምስረታ ጥሪ አቀረቡ

የቀድሞ ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ባለቤት ዶ/ር ፍሰሃ እሸቱ "በደል በስራዬ ነፃነት አጥቻለሁ፣ ደርሶብኛል" በማለት ሀገር ከለቀቁ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ባደረጉት ጥሪ "ለነፃነታችን ስንል የሽግግር ምክር ቤቱን በማቋቋም ሰዎች እንዲሳተፉ" ሲሉ ጥሪ አቀረቡ፡፡ ዶ/ር ፍሰሃ ለሁሉም ነገር መፍትሄው በያንዳንዳችን እጅ መሆኑን አመላክተው በዋነኝነት የባለቤትነት ስሜት ማዳበር እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል፡፡ "አቶ መለስ አንድም ቀን ሀገራችን ብለው አያውቁም" ያሉት ዶ/ሩ እንደ መሪ "ሀገራችን፣ሕዝባችን በማለት ከአንድ የድርጅት ኃላፊ (CEO) ጋር እንኳ መስተካከል ነበረባቸው" ብለዋል፡፡ በመሆኑም ዋነኛ ግባቸው ሰዎች መጀመሪያ ሕዝቡ አለቃ፣በርሃብ ሕዝቡ ተጨቆነ፣አማራ አለቀ የሚለው "ተበደልኩ፣ነፃነት አጣሁ በማለት ወደ ራሳቸው እንዲወስዱ እንጥራለን" ብለዋል፡፡

ሌላው ትኩረታቸው የነበረው ኢትዮጵያውያን የትም ሆነው መታገል እንደሚችሉ ለማስረዳት ሲሆን "ትግል በሀገር ውስጥ ካልሆነ ዋጋ የለውም የሚለው፣ጨረቃ ላይ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ቢኖር ስለ መብቱ አይታገል ከሚለው አባባል ጋር ይስተካከላል" በማለት አስረድተዋል፡፡ በሌላ በኩል "ጊዜው አሁን ነው" ያሉ ሲሆን "አሁን እከሌ አጥፍቷል፤እከሌ እንዲህ አድርጓል የምንልበት ሳይሆን ሁላችንም ለነፃነታችን የምንነሳበት ነው" በማለት ተናግረዋል፡፡ "ሕይወታቸውን ለሰውት ሰማዕታት ሙሉ ክብር ከመስጠቴም በላይ እንደነሱ ህይወቴን ብሰጥ ፍላጎቴ ነው" ያሉት ዶ/ር ፍሰሐ አላማቸውን ሲያስተዋውቁ "የምናነሳው ጉዳይ ሁላችንንም አንድ የሚያደርገን ነው፤እኛ ስለመሬት ጉዳይ፣ሊፈጠር ስለሚገባው መንግሥት፣ከዚያ በኋላ ሊፈጠር ስለሚገባው ዴመክራሲ፣እንዴት አድርጎ ሕዝቡ መደራጀት እንዳለበት፣ ወደፊት በምትገነባው ኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር፣ኃይማኖትና የፖለቲካ ጉዳይ ትኩረት የለንም" ካሉ በኋላ "በአንድ ነጥብ/ ጉዳይ ላይ ብቻ ገብተን መታገል እንፈልጋለን፣ያንም ማንም ሊነጥቀን የማይችለውን ነፃነታችን ናት፤ምክር ቤቱን ለማቋቋም ያሰብነውም ለዚሁ ነው" ብለዋል፡፡

የምክር ቤቱ አላማ ግልፅ መሆኑን የገለፁት አመቻቹ ዶ/ር ፍሰሃ "በዚህ ዙሪያ የሚገናኙ ኢትዮጵያውያን ባርነታችን አንገሽግሾናል፤ነፃነታችን ናፍቆናል፤ገብተን እንታገል ለሚሉ ሰዎች ጥሪ ማቅረብ ነው" በማለት ገልፀው ለዚህ መሳካት የመደራጀትን አስፈላጊነት አብራርተዋል፡፡ "መደራጀት የሚያስፈልገው ትግሉን ለማቀናጀት ነው" ያሉ ሲሆን ትግሉ ውስጥ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተለያየ አመለካከት ያሏቸው ሰዎች ከመካተታቸውም በላይ አማራ፣ኦሮሞ፣ትግሬ፣ጉራጌ፣ክርስቲያን፣ሙስሊም፣የተማረ፣ያልተማረ ቢኖርም አንድ የሚያደርገን የነፃነት ፍላጎት ነው" በማለት አብራርተዋል፡፡ በመጨረሻም ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ለዚህ "የነፃነት ትግል" የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሽግግር ምክር ቤት" ባሉት ድርጅት ሥር እንዲቀላቀሏቸው ጥሪ አቅርበዋል፡

# ዕውቀትና እምነት "የልማታችን" ተጨባጭ መጠን

በበለጠ ጐሹ ወ/ሚካኤል

ለኢህአዴግ ልማት ማለት ፕሮጀክቶችን መጀመር በራሱ፣ማገባደድና ማጠናቀቅ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት (ኢሬቴድ) የልማት ፕሮፖጋንዳ የተመሠረተው በዚህ ላይ ነው፡፡ ግልገል ጊቤ ፕሮጄክት ተጀመረ፣ሥልሳ በመቶ ተጠናቀቀ፤ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ በቀደም ተመርቆ ተከፈተ፡፡ ጊቤ 3 ፕሮጀክት 46 በመቶ ተከናወነ፤ለአዲስ አበባ የባቡር መስመር ግንባታ የቻይና መንግሥት ብድር መስጠቱን ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ገለፁ፡፡ ለአርሲ ገበሬዎች 200,000 ኩንታል ማዳበሪያ በብድር ተከፋፈለ" ወዘተ.ወዘተ፡፡ ጋዝ ጋዝ የሚል አሰልቺ ፕሮፖጋንዳ!

ችግሩ ያለው ኢህአዴግ ልማት ምን እንደሆነ አለማወቁ ላይ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ፣ልማት ማለት አራት ፍሬ ነገሮችን ያካተተ ፅንሰ ሃሣብ ነው፡፡ አራቱ የልማት መሠረቶች ኢትዮጵያ የምትባል የጋራ የሀብት ቋት (resource pool)፣ፍትሐዊ የመሬት ድልድል፣ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ሥልጠና ፍትሐዊ፣ትክክለኛ የብድር ሥርዓት ናቸው፡፡ እነዚህ የልማት መሠረቶች በኢኮኖሚክስ የምርት መገኛዎች ተብለው ከተሰየሙት ከመሬት፣የሰው ኃይልና ካፒታል (Land, labor/enterprise and capital) ጋር የተቆራኙ መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር የእነዚህ ሁሉ የሀብት መሠረቶች (ቋት) ስለሆነች፣የእሷን ህልውና ሳንጠብቅ ስለ ኢትዮጵያ ልማት ማውራት አንችልም፡፡ ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ሕልውና ጥያቄ እንዲነሳበት አይፈልግም፡፡ ምክንያቱም ሀገሪቷን እያጠፋት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ትልቅ የሀብት ንዑስ ቋት የነበረችዋን ኤርትራ ከነወደቦቿ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም ብሎ አስገንጥሏል፡፡ ይህን በማድረጉ በእኛ በኢትዮጵያውያን ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ኪሣራ ከማድረሱም በላይ፣የቀረችዋም ኢትዮጵያ የሕልውና ጉዳይ እጅግ አሳሳቢ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በተለይ እኛ ኢትዮጵያውያንን ሳያማክር ራሱ ባረቀቀው ሕገ-መንግሥት መሠረት ለጐሣ ክልሎች "የመገንጠል መብት ሠጥቻለሁ" በማለቱ እያካሄድኩ ነው የሚለው ልማት ራሱ የማን ልማት እንደሆነ ለማወቅ ያስቸግራል! "የትግራይ ነፃ ሪፓብሊካን" ልማት ነው ወይስ "የኦሮሚያ ነፃ ሪፐብሊካን" ልማት የሚያካሂደው?!

ለዚህም ነው ኢህአዴግ "ልማት!ልማት!" እያለ ከማደንቆሩ በፊት እየካሄደ ያለው የማን ልማት እንደሆነ በግልፅ ማሳወቅ አለበት ብለን የምንከራከረው፡፡ ኢትዮጵያ የምትባለውን የጋራ ቋታችንን ኢህአዴግ ስለተረተራት ሀብቷ በየአቅጣጫው እየፈሰሰ ነው፡፡ (በቅርቡ የኢህአዴግ ባለሥልጣናትና ደጋፊዎቹ 8.5 ቢሊዮን ዶላር ከሀገር እንዳሸሹ የተገለፀውን ያስታውሷል!) በመሆኑም፣ አንድ ነገር በጣም ግልፅ እየሆነ መጥቷል፤ኢህአዴግ አካሄዳለሁ የሚለው ልማት የኢትዮጵያ ልማት አይደለም! ሁለተኛው ነጥብ፣ለኢህአዴግ ልማት ማለት ጥቂት የመንግሥት የልማት ሥራዎችን መጀመር፣ማገባደድና ማጠናጠቅ ከሆነ፣በዚህም ረገድ የልማት ውጤቱ እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም አሁን በኢትዮጵያ ተንሠራፍቶ ካለው የሥራ አጥነት መጠን አኳያ፣ከጥቃቅን እስከ ትላልቅ ሥራዎች በአንድ ጊዜ እስከ ሁለት መቶ ሺ የልማት ፕሮጀክቶች ተወጥነው ተግባራዊ ሊሆኑ ሲችሉ፣ወደ ሰው ኃይል ገበያው በየዓመቱ የሚገቡትን ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሠራተኞች ለማስተናገድ ደግሞ በየዓመቱ እስከ አርባ ሺ (40,000) የቢዝነስ ፕሮጀክቶችን ማከናወን ይቻላል! ይህ ሊሆን የሚችለው ግን "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" እና "ልማታዊ መንግሥት" የሚል አባዜ በተጠናወተው የኢህአዴግ መንግሥት ሥር ሳይሆን፣በተለይ ለግሉ የኢኮኖሚ ክፍል ከፍተኛውን የልማት ሚና በሚሰጥ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት አስተዳደር ብቻ ነው! ኢህአዴግ "ልማታዊ መንግሥት?ማለት ምን እንደሆነ አያውቅም፡፡ ትክክለኛው የልማታዊ መንግሥት ትርጉም ራሱ መሥራት የሚገባውን ሁሉ እየሰራ ግን ለግሉ የኢኮኖሚ ክፍል አስፈላጊውን ሁሉ አመቺ ሁኔታ (enabling environment) የሚፈጥር መንግሥት ማለት ነው፡፡ በዚህ መልክ የተቀረፀ መንግሥት ልማታዊ ሳይሆን ኮሚውኒስት መንግሥት ነው! የዚህ ዓይነት መንግሥት ደግሞ በተለይ ከሶቭዬት ሕብረት መፈራረስ በኋላ አሁን የሰው ልጅ በደረሰበት የሥልጣኔ ደረጃ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ተረጋግጧል! በአልባኒያው ኮሚኒስት ፓርቲ አምሳል የተቀረፀው ማሌሊት ተሸፋፍኖ ከተደበቀበት ምድር ቤት በጓሮ በር እየገባ ይሆን እንዴ?!

ሌላው የልማት መሠረት ፍትሐዊ የመሬት ድልድል መሆኑ ከላይ ተገልጿል፡፡ ይህ ንድፈ ሐሳብ ሶሻሊስታዊ ወይም ኮሚውኒስታዊ ሊመስል ይችላል፤ ግን ለፍትሐዊ ካፒታሊዝም ዕድገት ራሱ አስፈላጊ ነው፡፡ ካፒታሊዝም ማለት በነፃ ገበያ በነፃ መወዳደር ማለት ከሆነ፣የማንም የሥራ ውጤት ያልሆነውና ተፈጥሮ የለገሰን መሬት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ሳይከፋፈል፣ዜጐች እንዴት በእኩልነትና በነፃ መወዳደር ይችላሉ? በሌላ አገላለፅ፣በጠመንጃ ኃይል አሥር ሺ ጋሻ መሬት የያዘ ነፍጠኛ ባላባት እንዴት ግማሽ ሄክታር ማሳ በጭሰኝነት ከያዘ ምስኪን ገበሬ ጋር በነፃና እኩል እየተወዳደረ ነው ማለት እንችላለን? ለዚህም ነው፣"መሬት ላራሹ" ብለን ሠላማዊ ሠልፍ የወጣነው! የደርግ መንግሥት የባላባቱን ሥርዓት አፈራርሶ፤ግን ይመራበት የነበረው አይዲኦሎጂ ሶሻሊዝም ኮሚውኒዝም ስለነበር፣"መሬት የመንግሥት ሀብት ነው" በሚል መርህ ለገበሬው የጠቀሜታ መብት (use rights) ብቻ ነበር የሰጠው፡፡ እንግዲህ፣ከአይዶሎጂው አኳያ በወቅቱ ይህን ስህተት ነው ለማለት አያስደፍርም ነበር፡፡ ከሶቤት ሕብረት መፍራረስ በኋላ ግን የአይዶሎጂው ዋና አእምሮአዊና ሚሊተሪ ምሶሶ (Intellectual and military power) ስለወደቀ፣በተግባራዊ ስኬታማነቱ የታወቀው ካፒታሊዝም የበላይነቱን እንደሚይዝ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነበር፡፡ እናም፣ኢህአዴግ "መሬት የመንግሥት ብቻ ነው" የሚለው የትኛውን የአይዲኦሎጂ መሠረት ይዞ ነው? ይህን ጉዳይ በተመለከተ ኢህአዴግ ምንም ዓይነት ንድፈ ሃሳባዊ መሠረት የለውም! ኢህአዴግ መሬት የመንግሥት ብቻ ነው ያለው የደርግ መንግሥት በጠቀሜታ መብት መልክ ለሕዝብ ያከፋፈለውን መሬት ከሕዝብ ነጥቆ ለራሱ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ለውጭ ኒዎኮሎኒያሊስት ኃይሎች በማከፋፈል ዘመናዊ ፊውዳሊዝምን እንደገና ሊጭንብን አስቦ እንደሆነ እስካሁን የወሰዳቸው ርምጃዎች በቂ ማስረጃዎች ናቸው! በየከተማው ግንባር ቦታዎች ከድሃው ሕዝብ ተነጥቀው ለኢህአዴግ ሁነኛ ሰዎች እየተሰጡ (በሊዝ ሽፋን) በከተማ ልማት ሰበብ ትላልቅ ፎቆች ተሠርተዋል!? እየተሰሩም ነው! በገጠር ደግሞ ገበሬውን በማፈናቀል ጭምር ሰፋፊ መሬቶች ለዘመኑ ኒዎኮሎኒያሊስት ኃይሎችና ወኪሎች በርካሽ ዋጋ እየተቸበቸቡ መሆናቸውን በአሁኑ ጊዜ የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም፡፡ በአጭሩ፣ጥቂት የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ኒዎኮሎኒያሊስቶች መሬታችንን ተቀራምተው እኛን መሬት አልባ እያደረጉን ነው! የኢኮኖሚ ባርነትና ጭሰኝነት እንደገና እየተጫኑብን ነው!

ሦስተኛው የልማት መሠረት ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ሥልጠና መሆኑም ከላይ ተገልጿል፡፡ እንደሚታወቀው የሀብት ማፍሪያዎች መሬት፣የሰው ኃይልና ካፒታል ናቸው፡፡ የሰው ኃይል ካልተማረና ካልሰለጠነ የማምረት ችሎታውና አቅሙ እጅግ ውሱን ይሆናል፡፡ ኢህአዴግ እንደሚለው ሳይሆን፣የሶሻል ሳይንስ ትምህርቶች በተለይ የፖለቲካ ሳይንስና ኢኮኖሚክስ ወሳኝነት አላቸው፡፡ ትክክለኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት ካልተዘረጋ በስተቀር ሌሎች ሙያዎችና ትምህርቶች ሁሉ የሚያስገኙት ውጤት ከሚጠበቀው በታች እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡ በሌላ በኩል፣የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ፈፅሞ ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም፡፡ ኢህአዴግ ግን ይህን መሠረታዊ መርህ ወደ ጐን በመተው፣ለይስሙላ በየአለበት የሚገትራቸውን የዩኒቨርስቲ ሕንፃዎች ከሞላ ጐደል የራሱን ካድሬዎች ማሠልጠኛ አድርጓቸዋል! በመሆኑም፣አብዮታዊ ዴሞክራሲን የሚያቀነቅኑ የፖለቲካ ሳይንስ ተማሪዎች ያፈራ ሲሆን፣የልማታዊ መንግሥትን ትርጉም በደንብ የማያውቁ ኢኮኖሚስቶች ደግሞ በአደባባይ እንዲዋሹ በልዩ ስኬል ወፍራም ደመወዝ እየተከፈላቸው ነው! የሐሰት አሓዛዊ መረጃዎችን እያቀነባበሩ ኢኮኖሚው በ11.5 በመቶ አድጓል/የዋጋ ንረቱ የዕድገት ውጤት ነው፤የገንዘብ መጠን መብዛት የዋጋ ንረት መንስዔ ሆኖ አያውቅም (አሁን አሁን እውነቱ አፍጦ ሲመጣ ጠ/ሚኒስትሩ ጭምር ይህንን እያመኑ ነው!)፤ "በኢትዮጵያ ላለፉት ሃያ ዓመታት ረሀብ የለም (ግን የወቅቱ ድርቅ ባስከተለው ረሀብ ምክንያት በየቀኑ አሥር ሕፃናት እንደሚሞቱ የተባበሩት መንግሥታት ሪፖርት ያመለክታል)፤የዋጋ ንረቱ የመጣው የውጭ ምንዛሬ ክምችት በመብዛቱ ነው፤ለውጭ ዜጐች (ኢንቨስተሮች) መሬት የሰጠነው፡፡ ገበሬውን ሳናፈናቀል ነው፤ወዘተ" እያሉ ሽምጥጥ አድርገው ይዋሻሉ!

ሦስተኛው የሀብት ማፍሪያ ካፒታል መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ መሬት ራሱ እንደ ተፈጥሮአዊ ካፒታል (natural capital) ሊቆጠር ይችላል፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አዲስ የገንዘብ ካፒታል (ወደ ቁሳዊ ካፒታል ሊቀየር የሚችል) የሚገኘው በራስ ቁጠባ ገንዘብ እና ከባንክ ብድር ነው፡፡ የራስ ቁጠባ ገንዘብ የሚፈለገውን ቁሳዊ ካፒታል (physical capital) ለማግኘት ስለማይበቃ ዋናው የገንዘብ ካፒታል ምንም የባንክ ብድር ነው፡፡ ይሁንና ይህንንም ኢህአዴግ በከፍተኛ ደረጃ ተቆጣጥሮታል፡፡ የመንግሥት ባንኮች (ብሔራዊ ባንክ፣የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣የልማት ባንክና ኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ) ሙሉ በሙሉ በኢህአዴግ መንግሥት ቁጥጥር ሥር ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣በኢትዮጵያ ትልቁ ባንክ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብድር የሚሰጠው በአብዛኛው በኢህአዴግ ትዕዛዝ (directed credit) ነው፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኢህአዴግ መበልፀጊያ ድርጅት መሆኑን ለመረዳት የትላልቅ ተበዳሪዎችን ስም ዝርዝር ማየት ብቻ ይበቃል! በነፃ ገበያና በነፃ ውድድር ሥርዓት የባንክ ብድር መስጠት ያለበት በአዋጪነት እና በብድር ማስያዥ (Feasibility and collateral) መርሆዎች ነው፤ ኢህአዴግ ግን በትዕዛዝ ራሱ ብድር የወስዳል፤ደጋፊዎቹ ብድር እንዲያገኙ ትዕዛዝ ይሰጣል!

ለማጠቃለል፣ኢህአዴግ "ልማት ሲል"፣የጋራ

ወደ ገፅ 13 ዞሯል

# የኃይማኖት ነፃነትና . . .

ከገፅ 2 የዞረ

አብዛኞቹ ተንታኞች ከገመቱት በተቃራኒ እየተጓዘ ነው፡፡ በሙስሊሙም በክርስቲያኑም ዘንድ የሀይማኖት መነቃቃቱ የተፈጠረው ዘመናዊነትን ባጣቀሱ፣ ዘመናዊ ትምህርት በደንብ የቀሰሙና በመንግሥትም ሆነ በግል በቂ የሙያ ልምድ ያላቸው ከተሜዎች ዘንድ መሆኑ ይነገራል፡፡ ይልማ በክሪ የተባሉ ፀሐፊ "Confidence of the muslim population in the current Ethiopian government's plummenting" በተባለ ጥናታቸው "ሽማግሌዎቹ ወግ አጥባቂዎች ወይም መሃይሞቹ ገበሬዎች" (Aging conservatives or illiterate peasants) የሚለው አባባል ያለፈበት ነው" ይላሉ፡፡ ይልማ ባክሪ በሙስሊሞች ዘንድ "ወጣቶቹ ሀይማኖተኞች፤ ወላጆቻቸው አለማውያን ናቸው" ሲሉ ይደመድማሉ፡፡ በመሆኑም መንግስት ባለው እንቅስቃሴ በመደናገር ለጣልቃ ገብነት ከሚሮጥ ጉዳዩ ካለው የወቅቱ ሁኔታ አንፃር ማጤን እንዳለበት ይናገራሉ፡፡

«ቤተ ክርስቲያን እጅ ሰጥታለች»

ከአፄ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ በተካሄዱት ስምንት የቤተ ክርስቲያናት "የዞፋንፍንገላዎች" ውስጥ የቤተ ክርስቲያኒቱ ካህናት እና ምዕመናን ንቁ ታሳታፊዎች እንደነበሩ በደርግ ዘመን የቤተክህነቷ ሥራአስኪያጅ የነበሩት ሰው ጽፈዋል፡፡ አፄ ኃይለ ሥላሴ በህገ መንግሥታቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ ጠባቂ ንጉሠ ነገሥቱ መሆናቸውን ደንግገዋል፡፡ አቡነ ቴዎፍሎስ አይቪንድ ኤዲ (oyvind eide) "Revolution and Religion in Ethiopia" በተባለ መፅሐፋቸው ውስጥ "ቤተ ክርስቲያን ከሌለች መንግሥት አይኖርም፤ መንግሥትም ከሌላ ቤተ ክርስቲያን አትኖርም፡፡ በአትዮጵያ ቤተ ክርስትያንና መንግሥት አንድ እና አንድ ናቸው" ማለተቸው ተፅፏል፡፡ በአዲስ አበባ የአውሮፓ ህብረት አምባሳደር ቲም ክለርክ ድህረ ምርጫ 97 ዓ.ም የነበረውን ውጥረት ለማርገብ 5 ኪሎ መንበር ፓትሪያሪክ ገብተው የተረዱት ተቋሙ የፖለቲካ ውጥረቱ አካል እንጂ መፍትሄ ያለመሆኑን ለቀድሞው ቅንጅት አመራር ማስረዳታቸው ይታወሳል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና መምህር የሆኑት ዶ/ር ዳኛቸዉ አሰፋ የዚህን ችግር በኢህአዴግ ርዕዮተ አለም ውስጥ እንድናስስ ይመክራሉ፡፡ እንደ ዶ/ሩ አባባል የዚህ አተያይ የመጀመሪያ ሰለባ ራሱ የኢህአዴግ ፓርቲ መሆኑን ገልፀው «ቤተ ክህነትም ተሰልፋለች» ብለዋል፡፡ «ሙስሊሙ አከባቢ ግልፅ ባይሆንም በቤተክርስቲያን በኩል ቄሶቹ ከቅዳሴ በኋላ ስለ ልማት መስበክ ይጀምሩና ይህም በመፅሃፉ አለ ይሉናል፤ አሁንስ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መደበቂያም አጥተናል» ሲሉ ያማርራሉ፡፡ በገጠር አከባቢ በአላትንና ሰንበታትን እንዲያከብሩ የሰበኩ ቄሶች በካድሬዎች ተወስደው መታሰራቸውን ፍኖተ ነፃነት ለማወቅ ችላለች፡፡ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ለአባይ ግድብ ቦንድ መግዣ መቀስቀሻ የሚደጋገም አንድ የክርስትና የሀይማኖት አባት ንግግር በናቱ ማህፀን ካለ እስከ አረጋዊ ያለ ኢትዮጵያዊ ለአባይ ግድብ ካላዋጣ ኢትዮጵያዊነቱን መካዱን የሚደመድም ነው፡፡

አንድ ሀገር አንድ ሀይማኖት= አንድ ሀገር አንድ አብዮታዊ ዴሞክራሲ

የኢህአዴግ መንግሥት ተቺ የሆኑ አብዛኛዎቹ ምሁራን በአንድ ነገር ይስማማሉ፡፡ ኢህአዴግ በሀገሪቷ የመረጃ ክፍተት ለመፍጠር ይጥራል፡፡ የዚህ አላማ ዋነኛ ግብ በመንግሥት ቁጥጥር ስር ሆኖ የመንግሥትን ሀሳብ ብቻ የሚያቀነቅነው ሚዲያ የተለየ ተደማጭነት እንዲያገኝ ነው፡፡ ዋነኛ የመንግሥት ሀሳብ ሆኖ የሚቀርበው ደግሞ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮተ ዓለም ሲሆን ሌሎች ማናቸውም አማራጮች በትዕግስት እንደማይታለፉ ተቺዎቹ ይናገራሉ፡፡ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ይህንን ጉዳይ "መንግሥት ‹አንድ ሀገር አንድ አይዲዮሎጂ› እያለ እንዴት ‹አንድ ሀገር አንድ ሃይማኖት› የሚሉትን ሊተች ይችላል?" በማለት ይጠይቃሉ፡፡ አብዛኛዎቹ ተቺዎች አክራሪነት የወቅቱ አለም አቀፍ አጀንዳ እየሆነ ቢመጣም ባለው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የኢህአዴግ ሁሉን ነገር የመቆጣጠር አባዜ ነገሩን ሳያጋግለው እንዳልቀረ ይነገራሉ፡፡ "ጥቂትም ቢሆኑ የክርስትያን መንግሥት ለመመስረት የሚንቀሳቀሱ አሉ" ስለፊዎች ነውጠኞች ናቸው፤ አብዛኞቹ የአልቃይዳ አባላት የስለፊ ተከታዮች ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ተገኘ የተባለዉ ሴል ከዋርጂያ መባሉን ሰሞኑን የወጣ የመንግስት ሰነድ ያብራራል፡፡ እነዚህ ቡድኖች «በሙሉ ሰለፊዎች ሲሆኑ አላፊዎች በሙሉ ግን አልቃይዳዎች አይደሉም» ያሉት አቶ መለስ አብዛኞቹ ባሌና አርሲ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል፡፡

# የፍትህና የነጋድራስ ጋዜጣ ዋና አዘጋጆች ዛሬ ለብይን ይቀርባሉ

የእነ አንዱዓለም አራጌ የክስ መዝገብ በመታየት ላይ በነበረበት ወቅት ዐቃቢ ህግ ለፍ/ቤቱ ባቀረበባቸው አቤቱታ የፍትህ ጋዜጣና የነጋድራስ ጋዜጣ ዋና አዘጋጆች የጽሁፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ዐቃቢ ህግ በፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ላይ ተጨማሪ አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን የጋዜጣው ዋና አዘጋጅም የጋዜጣውን ህግ አማካሪ አማክሮ መልስ እንደሚሰጥ ለፍ/ቤቱ አስረድቷል፡፡

ቀደም ሲል ዐቃቢ ህግ ለፍ/ቤቱ ባቀረበው አቤቱታ "ፍትህ ጋዜጣና ነጋድራስ ጋዜጣ የዐቃቢ ህግን ሞያዊ ብቃት የሚሸረሽር፤ በፍርድ ሂደቱ ላይ ጥላ የሚያጠላ፤ ህብረተሰቡ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ እምነት እንዲያጣ የሚያደርግ ጽሑፍ አሳትመው በማሰራጨታቸው ቀርበው ያስረዱልኝ" በማለት አቤቱታ አቅርቦ ነበር፡፡ የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ተመስጌን ደሳለኝና የነጋድራስ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ሱራፌል ግርማ መልሳቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

አዘጋጆቹ ባቀረቡት ጽሑፍ እንደገለጹት "አትመን ያወጣነው ጽሑፍ ተከሳሾች በፍ/ቤት ለችሎቱ ያቀረቡትን ጽሑፍና የቃሊቲ ማረሚያ ቤት በአቶ አንዱዓለም አራጌ ላይ በጋዜጣው ላይ ለሰጠው መግለጫ ሰሙ በጋዜጣው ላይ የተጠቀሰው አቶ አንዱዓለም አራጌ በፕሬስ ህጉ መሠረት የሰጠውን መልስ ነው" በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የግራና ቀኙን ክርክር የሰማው ችሎት ብይን ለመስጠት በዛሬው ዕለት ቀጠሮ ይዟል፡፡ በተጨማሪ ዐቃቢ ህግ በፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ላይ ላቀረበው አቤቱታ አዘጋጁ ዛሬ የጽሁፍ መልስ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

## የዓለማችን ግዙፍ ኩባንያዎች ተወካዮችና ታዋቂ ኢኮኖሚስቶች አዲስ አበባ ሊሰበሰቡ ነው

በዓለም ላይ ያሉትን ግዙፍ ካምፓኒዎችን የሚያንቀሳቅሱና የዓለም ታዋቂ የኢኮኖሚ ምሁራን እንዲሁም ተመራማሪዎችና የአገር መሪዎች አዲስ አበባ ሊሰበሰቡ መሆኑ ተገለፀ፡፡ ይህ የተገለፀው ባለፈው ዐርብ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት በዋቢሸበሌ ሆቴል በተዘጋጀ የውይይት መድረክ ላይ ነው፡፡ በመድረኩ ላይ እንደተገለፀው ኢትዮጵያ የዓለምን የኢኮኖሚ ፎረምን እንድታዘጋጅ በተሰጣት መሠረት ዝግጅቷን እያጠናቀቀች ነው ተብሎአል፡፡

ሰብሰባው ከ15 ቀን በኋላ ለሦስት ቀን የሚከናወን ሲሆን ከ700 በላይ ተሳታፊዎች በጉባኤው ላይ ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ጉባኤው መሪዎች ለሚወስኑት ውሳኔና ለሚወስዱት እርምጃ አጋዥ የሆኑ ሐሳቦች የሚፈልቅበት ነው ተብሎአል፡፡ መድረኩ ነፃ ውይይት የሚደረግበት ሲሆን ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ችግር የሚፈለግበት እንደሚሆን ተገልፃዕል፡፡

በ1971 እ.ኤ.አ በአንድ ጀርመናዊ ፕሮፌሰር የተቋቋመው የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ሲሆን በዓመት አንድ ጊዜ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ እስከ ዛሬ ስብሰባው የሚደረገው በኢኮኖሚ ባደጉና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ እንድታዘጋጅ እድል ተሰቷታል፡፡

## የአቶ መለስ መልስ ሙስሉሞችን ማስቆጣቱ ታወቀ

ሚያዝያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ ወቅታዊውን የሙስሊሞች እንቅስቃሴ በተመለከተ በሰጡት ማብራሪያ ሙስሊሙ ያለውን ቅሬታ ገለፀ፡ ፡ አርብ ማያዚያ 12/08/04 ዓ.ም የጁመዓ አጋጣሚን በመጠቀም በአንዳንድ መስጂዶች የተቃውሞ ድምፆች መሰማታቸው ታወቀ፡፡ የአንዋር መስጊድ ተገኝቶ የነበረዉ የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ሪፖርተርም ይህንኑ መታዘብ ችሏል፡፡ የተቃውሞ ምንጭ ከነበሩት ጉዳዮች አንዱ ጥያቄው የተጠየቀበት አካሄድ በራሱ ሰላማዊና ሕገመንግሥታዊ ጥያቄዎችንን ወደ የጥቂት ኃይሎች አክራሪነት፣ምንም ምክንያት ሳይኖራቸው መንግሥት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል የሚሉ ቡድኖችና፣ የፖለቲካ አላማቸውን በኃይማኖት ስም ለማሳካት" የሚሉ መጥፎ ምሪቶች /bad leadings/ እንደነበሩበት በማንሳት ነው፡፡

መንግሥት ራሱን ለመከላከል "መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም" የሚለውን የህገ-መንግሥት አንቀፅ በመጥቀስ በጉዳዩ እንደሌለበት ለማስረዳት ቢሞክርም የሕግ መኖር ብቻውን አንድን ነገር ከምንጩ ባለመከላከሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ጉዳያቸዉ ወሳኝ እንደ ነበር ባለፉት ጊዜያት ያስተዋሉት ጉዳይ እንደሆነ ተናግረዋል፡ ፡ በተጨማሪም ጠ/ሚ/ሩ "በአንዳንድ ትንተናቸው በእስልምና የሌለውን የአስተሳሰብ መስመር / School of thought/ ለመቁጠር ደርሰዋል ሲሉ ያማረሩ ሲሆን በራሳቸው ትንተና አህባሽ ሱፊይ ነው የተባለውም በታላላቅ የእስልምና ዩኒቨርስቲዎች ጭምር ብያኔ ተሰጥቶበታል" ብለዋል፡፡

በዕለቱ በአወሊያ የተገኘው ሙስሊም ከአንድ ሚሊዮን በላይ መሆኑ የተሰማ ሲሆን እስከ 9 ሰዓት በከፍተኛ ድምፅ ተቃውሞ እንዳሰሙ የውስጥ ምንጮች ተናግረዋል፡፡ የተቃውሞው ማዕከል የነበረው መጂሊሱ ተመርጦ አያውቅም የሚለው ሲሆን በተለይ ሼህ ኤሊያስ ሬድዋንን የተካው ቡድን የሽግግር መሆኑ ተነግሮ የነበረ ቢሆንም ዛሬም ተረጋግቶ መቀመጡ እንደ ሆነ ተገልጿል፡ ፡ በሌላ መልኩ "አህባሽን በቀድሞ መዋቅሮቻችን እየተጠቀሙ ከመስበካቸውም በላይ አንዳንድ ዑላማዎችን የአህባሽን ስልጠና ካልወሰዱ ከመስጂድ እንደሚያባርሩ እናውቃለን" ሲሉ አማረዋል፡፡

## የርዕዮት ዓለሙ ፍርድ በይግባኝ ሊታይ ነው

በሽብርተኝነት ተከሳ 14 ዓመት እስራትና 33 ሺ ብር ቅጣት የተወሰነባት ጋዜጠኛና መምህርት ርዕዮት ዓለሙ ፍርድ በይግባኝ ሊታይ መሆኑን ወላጅ አባቷ ጠበቃ ዓለሙ ጌቤቦ አስታወቁ፡፡ ጠበቃ ዓለሙ ጌቤቦ በተለይ ለፍኖተ-ነፃነት ጋዜጣ እንዳስታወቁት "የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት በሰጠው ፍርድ ቅር በመሰኘታችን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ጠይቀን ነበር፡፡ የይግባኙን አቤቱታ ሲመረምር የከረመው ጠ/ፍ/ቤት መዝገቡ ያስቀርባል ብሎ ብይን በመስጠቱ የይግባኙን አቤቱታ ለማየት መዝገቡን ለግንቦት 29 ቀን 2004 ዓ.ም ተቀጥሯል፡ ፡" ብለዋል፡፡

ርዕዮት ዓለሙ በጡቷ ላይ በተፈጠረ እጢና በጨጓራ ህመም ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በተመላላሽነት እየታከመች ስትሆን ጡቷ ቀዶ ጥገና እንደሚያስፈልገው በሐኪም መወሰኑ ታውቋል፡፡

## አንድነት ፓርቲ ስልጠና ሊሰጥ ነው

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስራ አስፈፃሚ ለአዲስ አበባ የፓርቲው የወረዳ አመራር አባላት የአንድ ቀን ሙሉ ስልጠና ሊሰጥ መሆኑን አስታወቀ፡፡

ስልጠናውም እሁድ ሚያዝያ 21 ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት ጀምሮ በፓርቲው ዋና ጽ/ቤት አዳራሽ እንደሚካሄድ ተጠቁሟል፡፡

በተለይ ስልጠናውን ያዘጋጀው የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ህዝብ ግንኙነት ክፍል ሲሆን ስልጠናውም ትኩረት ያደረገው ለየወረዳዎቹ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች ተጨማሪ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እንደሆነ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡

## ኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በሞግዚት እየተመራ እንደሆነ ተጠቆመ

በሕዝብ ብዛትና በቆዳ ስፋት የመጀመሪያውን ደረጃ የሚይዘው የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በሞግዚት እየተመራ እንደሆነ የመረጃ ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡

ታማኝ የመረጃ ምንጮቻችን እንደሚሉት "ክልሉ በህገ መንግሥትና በህጋዊ የህዝብ ተወካዮች በሚመሠረት ክልላዊ የመንግሥት አስተዳደራዊ መዋቅር እንዳለው ቢታወቅም በየደረጃው የተቀመጡት ባለሥልጣናት በሙስና በመዘፈቅ፣ኢ-ፍትሐዊ ውሳኔ በመወሰን፣በቡድን በመደራጀት ወደ ተለያየ አቅጣጫ በመጓተት አለመግባባት ይታያል፡፡ የክልሉ ፕሬዝዳንት አጀንዳ ለማስያዝ የማይችሉበት ሁኔታዎች አሉ፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ከክልሉ ውጪ ባለ ግለሰብ የክልሉ መስተዳድር በትዕዛዝ እየተመራ ነው፡፡" በማለት በቅሬታ ይገልጻሉ፡፡

የውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደሚሉት "የክልሉ ፕሬዝደንት እንደማንኛውም የኦህዴድ አባላት የተዛባ የፖለቲካ አመለካከት፤ኢ-ፍትሐዊ የአስተዳደር መርህን የሚከተሉ፤ጎጣዊ የጎሳ አመለካከት አለባቸው እየተባሉ ቢታሙም በግለኝነት፣በራስ ወዳድነትና በሙስና የማይጠረጠሩ ናቸው፡፡ እንዲያውም ሙሰኞችን አምርረው በመታገላቸውና አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰዳቸው የሙሰኞቹ ቡድን ህይወታቸውን እስከማጥፋት ሙከራ ያደረጉባቸው ከመሆኑም በላይ በድርጅቱ ሥራ አስፈጻሚ ውስጥ አጀንዳ እንዳያሲዙ ሁሉ ተጽኖ ስለሚደረግባቸው በክልሉ መስተዳድር አመራር ላይ ተጽኖ ፈጣሪ መሆን አልቻሉም፡፡" ሲሉ ያብራራሉ፡፡

ምንጮቻችን አያይዘውም ሲዘረዝሩ "በአሁኑ ጊዜ ክልሉን የሚመሩት የክልሉ ፕሬዝዳንት አቶ አለማየሁ አቶምሳ ሳይሆኑ ጠ/ሚኒስትሩ ጽ/ቤት የሚገኙት አቶ ገ/ተንሳይ ወ/ተንሳይ የተባሉ ግለሰብ ናቸው፡፡" ይላሉ፡፡ "ከዚህ በፊት አቶ ሰለሞን ተስፋዬ (ሰለምን ጢሞ) ኦህዴድ ጽ/ቤት ቢሮ ከፍተውና ተቀምጠው ድርጅቱንም የክልሉን የመንግሥት አመራር እግር በእግር እየተከታተሉ፣እየገመገሙና አመራር እየሰጡ ይመሩ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ አቶ ገ/ተንሳይ ወ/ተንሳይ ቢሮአቸውን ጠ/ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ውስጥ አድርገው ከዚህ በፊት ሰለሞን ጢሞ ሲሰራ የነበረውን ሥራ ተክተው እየሠሩ ናቸው፡ ፡ በክልሉ ውስጥ ተደማጭነትና ተቀባይነት ያለው የክልሉ ፕሬዘዳንት ትዕዛዝና መመሪያ ሳይሆን የአቶ ገ/ተንሳይ መመሪያና ትዕዛዝ ነው፡፡ ስለዚህ ዛሬም ኦሮሚያ በሞግዚት አስተዳደር እየተመራ ነው፡፡ " በማለት ቅሬታቸውን ይገልጻሉ፡፡ በጉዳዩ ላይ የክልሉን ፕሬዝዳንት አቶ አለማየሁ አቶምሳንና የአቶ ገ/ተንሳይ ሐሳብን ለማካተት ያደረግነው ሙከራ ለጊዜው አልተሳካል፡፡

## ዕውቀትና እምነት . . .

ከገፅ 12 የዞረ

የሀብት ቋት (resource pool) የሆነችዋን ኢትዮጵያ ተርትሮና "በመገንጠል ሙብት" ሽፋን ሀብቱ በየአቅጣጫው እንዲፈስ አድርጐ ስለሆነ፣እያካሄድኩ ነው የሚለው ልማት "የኢትዮጵያ ልማት" ለመሆኑ ማረጋገጫ የለም! የደርግ መንግሥት በጣለው መሠረት ላይ ፍትሐዊ የመሬት ድልድል በማድረግ ፈንታ ከዜጐች የመሬት ይዞታቸውን በኃይል እየነጠቀ ለጥቂት አባላቱና ደጋፊዎቹ በመስጠቱ፣ሕዝቡን መሠረት ያደረገ ልማት (broad-based development) ሳይሆን እያካሄደ ያለው፣ዓይን ያወጣ የጥቂቶች ዝርፊያና ምዝበራ ነው! በተመሳሳይ፣ኢህአዴግ የዘረጋው የትምህርት ሥርዓት የትምህርት ጥራትን የሚያዳክም እንደመሆኑ፣ውጤቱ "የተማሩ ሥራአጦችን" ማብዛት ሆኗል! ካፒታልንም በተመለከተ፣ከላይ እንደተገለፀው ነው፡፡ በመሆኑም፣ኢህአዴግ እያካሄደ ያለው ልማት ሳይሆን ዝርፊያ ነው! በውጭ ዕርዳታ የተሠሩትና እየተሠሩ ያሉት ጥቂት መሠረተልማቶች ይህንን ሀገር አቀፍ ግዙፍ የዝርፊያ ተግባር ለመሸፋፈን ጭምር ያገለግላሉ፡፡ የኢህአዴግ የልማት ፕሮፖጋንዳ የሚያነጣጥረውም እነዚህ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴለቪዥን ድርጅት በየቀኑ ለሚያሰራጨው ጋዝ-ጋዝ ለሚል የልማት ፕሮፖጋንዳው እነዚህን እንደ አቢይ ግብዓት ይጠቀምባቸዋል! በሀገራችን እውነተኛ ልማት የሚካሄደው ልማት ኢትዮጵያዊና ሕዝባዊ ሲሆን ብቻ ነው! ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ኢህአዴግ ለአለፉት ሃያ ዓመታት ያዋቀረው የዝርፊያ ሥርዓት ሲፈራርስ ነው! የኢህአዴግ የልማት ፕሮፖጋንዳ እንደቆርቆሮ የሚጮህ ቱልቱላ ነው!

# የጠቅላይ ሚ/ሩ ውርጅብኝ በመምህራን ላይ

መ/ር ቀለሙ ሁነኛው
kelmhun@yahoo.com

በ25ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ ላይ ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ ከአባላቱ ለቀረቡት ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ የንግግራቸው ማሳረጊያ የመምህራን የደመወዝ ርከን ማስተካከያ ጉዳይ ነበር፡፡ በየትኛውም አገር አንድ መሪ የሚያደርገው ንግግር በጉጉት ይጠበቃልና ሁሉም ሰዓቱ እስኪደርስ “አቶ መለስ ዛሬስ ምን ይሉ ይሆን?” በሚል ሀሳብ መጋራቱ አልቀረም፡፡ ሁላችንም እንደ ተከታተልነው ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች (መልሱ አጥጋቢ ቢሆንም ባይሆንም) ምላሽ የሰጡት አቶ መለስ ብዙ ጉዳዮችን በደምሳሳው ነካክተው አልፈዋል፡፡ በጣም የሚገርመውና ሁል ጊዜ ጥያቄ የሚሆንብን እሳቸው ስህተትም ይሁን ትክክል በተናገሩት ሀሳብ ላይ ክርክር ማድረግ አለመቻሉ ነው፡፡ ሁልጊዜ እሳቸው የፈለጉትን ይናገራሉ እኛ የማንፈልገውን እናደምጣለን፡፡ የስለጠነ ዴሞክራሲ የሰፈነባቸው አገራት ፓርላማ ጭቅጭቁና ንትርኩ ያስቀናል፡፡ የእንግሊዝ ፓርላማ የጠቅላይ ሚ/ር ዴቪድ ካሜሮንን ንግግር ካፋቸው እየነጠቁ ሲሞግታቸው ማየት ምንኛ መታደል ነው፡፡ እኛ ግን የአቶ መለስን ንግግር እንደ እግዚአብሔር ቃል እንደ እ/ር ቃል የግድ ለመቀበል እንገደዳለን፡፡ “ይሄኛው ጥያቄ አልተመለሰም” ብሎ ደግሞ መጠየቅ አይቻልም፡፡ እሳቸውም የመሰላቸውን ሀሳብ ከሰነዘሩና የልባቸውን ከተናገሩ በኋላ በሰላም ይሸኛሉ፡፡

አቶ መለስ በሚያዝ 9/2004 የፓርላማ ማርፈጃቸው የመጨረሻው ምላሽ ከመምህራን የሙብት ጥያቄና የስራ ማቆም አድማ ጋር የተያያዘው ንግግራቸው ነበር፡፡ በርግጥም የኢትዮጵያ መምህራን መ/ር ከ4 ዓመታት በፊት የጠየቀው የደመወዝ ጭማሪ ሳይሆን የርከን ማሻሻያ ነው፡፡ የደመወዝ ጭማሪ አይደለም፡፡ ኑሮው የተወደደው ለሁሉም ዜጋ በመሆኑ ከሌሎች የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች የተለየ ለመምህራን የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግ አልተጠየቀም፡፡ ነገር ግን መምህራን የአገልግሎት ዘመናቸው እየጨመረ ሲሄድ በተመሳሳይ የት/ት ደረጃና የአገልግሎት ዘመን ካላቸው የሌሎች ሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤት ሠራተኞች የደመወዝ ርከኑ ወደኋላ ይጎተታል፡፡ በተያያዘም የመምህራን ስድስት የርከን ደረጃ ላይ ሲቆም የሌሎች የመንግስት ሠራተኞች እስከ ዘጠኝ ደረጃ ይዘልቃል፡፡ ይህ ከፍተኛ የሆነ ልዩነት መፈጠሩ መምህራንን ሲያስከፋና ሞራላቸውን ሲያላሽቅ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

አቶ መለስ በፓርላማ ንግግራቸው እንዳሉት የካቲት 2 ቀን/2001 ዓ.ም ከመላው አገሪቱ ከተወጣጡ 3ሺህ መምህራን ጋር ውይይት ባደረጉበት ወቅት ነበር እሳቸው የመምህራን ማህበር ስላስጠናው ጥናት ያወሱት፡፡ ግብአት እንዲሆንም ለሚመለከተው ክፍል እንደመሩት አስረግጠው ተናግረዋል፡፡ ግና ምን ያደርጋል? የውሃ ሽታ ሆነ፡፡ ዓመታት ተቆጠሩ፡፡ ምላሽ የለም፡፡ ማህበሩም አባላቱን በተለያዩ ምክንያቶች በሰበሰበ ቁጥር እንደ ውዳሴ ማርያም የሚደግመው ይህንኑ ነበር “ጠቅላይ ሚ/ሩ ግብአት እንዲሆን ለሲቪል ሰርቪስ መ/ቤት መርተውታል” የሚል ጥናቱ በኤሊ ላይ ተጭኖ ከጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ወደ ሲቪል ሠርቪስ መ/ቤት ቢላክ ይህን ያህል ጊዜ አይፈጅም፡፡ ብቻ በጥቅሉ የአንድ ሹመኛ የጠረጴዛ ኪስ ውስጥ ተወርውሮ የቆየ ይመስላል፡፡

ይህ ቆይታና ለጥናቱ ምላሽ መነፈጉ ነበር የድሬዳዋው የመምህራን ማህበር ጉባኤ ያስተላለፈውን የአቋም መግለጫ የወሰደው፡፡ የማህበሩ አመራሮች እስከ ጥር 30/2004 ዓ.ም ድረስ መንግስት ለጥያቄው ምላሽ እንዲሰጥ በቀነ ገደብ ጠየቁ፡፡ ከዚያ በኋላ ነው በጥናቱ መሠረት የመምህራን ጥያቄ ምላሽ እንዳገኘ ተደርጎ አዋጁ የተነገረው፡፡ በተለይም የት/ት ሚ/ር ዲኤታው አቶ ፋአድ ኢብራሂም የፌዝ ፈገግታን ተላብሰው “የመምህራንን ሕይወት የሚለወጥ፣ ፍልሰትን የሚያቆም፣ ለሞያው ክብርን የሚያጎናፅፍ” ሲሉ በመምህራን ላይ የተሳለቁት፡፡

ኢህአዴግ ጠቅልሎ በያዛቸው የሕትመትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች ያልሆነውን ሆነ ብሎ መግለጫ ሲሰጥ ሀይ ባይ የለውም፡፡ የሚያግደው ሕግ የለም አገሪቱ በተለያዩ ውስብስብ ችግሮች ውስጥ ተዘፍቃ ኢቴቪ በሙዚቃ ማዕበል ያናወጠናል፡፡ ጥጋብን ይሰብከናል፡፡ በጋ ከክረምት የልምላሜን ፀዳል የተላበሱ መስኮችን ያሳያናል፡፡ በረሀማ ሥፍራዎች ምንጭ ሲፈልቅባቸው ያስቃኘናል፡፡ በምኞት ዓለም፣ በህልም አለም ያኖረናል፤ ኢቴቪ ለፋሲካ በአል ዝግጅት የተጠመዱት የኢህአዴግ ልማታዊ ጋዜጠኞች ከድሬደዋ፣ ከአዋሳ፣ ከቢሾፍቱ እንደ አሸን የፈሉ ዘፋኞችን አርቲስት በሚል የእንግሊዝኛ ቃል እያሞካሹ የኢህአዴግን የልማት እንቅስቃሴና ቁርጠኛ አመራር ሲደሰኩሩልን ዋሉ፡፡ በበዓሉ ዋዜማ በየገበያው የተበተኑት ደግሞ “ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ” እንዲሉ የበግን ዋጋ ዝቅተኛው 500 ብር እንዲሆን ነገሩን፡፡ የበሬም ዋጋ 5000.00ብር በእርግጥ ከዛሬ አስር አመት በፊት የዘገቡትን ከፋይል ውስጥ አውጥተው ከሆነ ትክክል ናቸው፡፡ በዘንድሮው ፋሲካ በግ እስከ ብር 500.00 መገኘት ቢችል እያንዳንዱ መምህር በግ ለመግዛት ይዳዳው ነበር፡፡

ወደ ዋናው ሀሳቤ ልመለስ፡፡ መምህራን ከእርከን ማስተካካያው ይልቅ ያበሳጫቸውና ቁጣቸውን ያጋጋለው በኢህአዴግ ሹመኞች የተሰጠው መግለጫና ለማህበሩ ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ የሰማይና የምድር ያህል መራራቁ ነው፡፡ ይህ ድርጊት ያስቆጣቸው መምህራን አቶ መለስ እንዳናናቁት (እንዳጣጣሉት) ሳይሆን በአዲስ አበባ እንኳን ከ31 ት/ቤቶች በሆኑ እልህና ሳግ እየተናነቃቸው የአቋም መግለጫዎችን በማውጣት ወደ ሚመለከተቸው ክፍሎች አዥጎድጉደውታል፡፡ አቶ መለስ ግን ይህን ሀቅ ሊሰውሩ ሞከሩ፡፡

### የአቶ መለስ ግልፅ ስህተቶች

ስህተት አንድ፡- 99.9% የሚሆነው መምህር በእርከን ማስተካከያው ረክቷል፡፡ እጅግ በጣም የሚያሳዝን አባባል ነው፡፡ እንደሳቸው አገላለፅ ከ500 የማይበልጡ መምህራን እንዳኮረፉና ከሁለት የማይበልጡ ት/ቤቶች እንደተዘጉ አድርገው የመምህራንን የሙብት ጥያቄዎች አጣጣሉት፡፡ አቶ መለስ እነዚህ ሁሉ መምህራን መደሰታቸውን በየትኛው መመዘኛ ለኩት? እንዴትስ አዋቂ ኩሎ ቢሆኑ ነው 99.9 ፐርሰንቱ በደስታ መቀበሉን ያረጋገጡት? መምህሩ 60 እና 70 ብር ተጨመረ መባሉ ሲገርመው አቶ መለስ ደግሞ በርከን ማስተካከያው ምክንያት “ሀያም ሠላሳም ብር ሊያገኝ የሚችል ይኖራል” ሲሉ ይባስ ብለው የመምህሩን ቅስም ሰበሩት፡፡

የተከበሩ አቶ መለስ ኢህአዴግ ምርጫ ሲያሸንፍ 99.9% መምህራንንም በደመወዝ እስኬል ማሻሻያ ሲያንበሸብሽ የሚደሰተው የመምህር ቁጥር 99.9%፡፡ እስቲ ይሁና፤ እንዲያው ለመሆኑ ከ350 ሺህ በላይ መምህራን አለመደሰታቸውን መግለጽ የሚገባቸው የሥራ ማቆም አድማ በማድረግ ብቻ ነበርን? ህገ መንግስታዊ መብቶቹን ተጠቅሞ ለመቃወም የኢህአዴግ የማስፈራሪያ መንገዶች ከመቼውም በላይ ዜጎችን እያስጨነቀ ይገኛል፡፡ በየጊዜው በፓርላማ የሚፀድቁ ህጎችም ሆኑ ከፓርላማ ውጭ በጥቂት ባለ ስልጣናት የሚደነገጉት አያላውሱ! አያስተነፍሱ! ብቻ ነጋ ጠባ እህህን እያማጡ ተሸመድምዶ መኖር የእኛ የኢትዮጵያውያን እጣ ፈንታ ሆኗል፡፡ የተከበሩ አቶ መለስ ዛሬም ደግሜ እነግርዎታለሁ፡፡ እባክዎትን ጓዳዎን ይፍትሹ! ከበታች ሹማምንትዎ ነጋ ጠባ የሚደርስዎት ሪፖርት 99.9% ውሸት ነው! ቅጥፈት ነው! ከሕዝብ ጋር የሚያቃቅርዎት አልፎም በህዝብ ዘንድ እንዲጠሉ የሚያደርግዎት ነው፡፡ እርስዎ በፓርላማ እንደተናገሩት 99.9% የሚሆኑ መምህራን በርከን ማስተካከያው ደስተኛ ቢሆኑ ኖሮ የኢትዮጵያ ቴሊቪዥን ነጋ ጠባ የመምህራንን የደስታ ንግግር በማስደመጥ ያሰለቸን ነበር፡፡

ስህተት ሁለት፡- ምድረ ነውጠኛ ት/ቤት ብጥብጥ ተነሳ በሚል ስለማራገባቸው የመምህራን ጥያቄ የሙብት ጥያቄ እንጂ የነውጥ ናፋቂነት ጉዳይ አይደለም፡፡ ጥያቄው የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች ፍፁም ያከበረ ነው፡፡ በአንቀጽ 42/ለ ላይ እንደተጠቀመው የስራ ማቆም አድማ ማድረግ ሕገ መንግስታዊ መብት እንጂ ሽብርተኛ፣ ነውጠኛ የሚያሰኝ አይደለም፡፡ አቶ መለስ በንግግራቸው የመምህራንን ተራ የስራ ማቆም እንቅስቃሴ ከሻዕቢያ፣ ከኦነግ ከኦብነግና ከግንቦት 7 ጋር ሊያይዙት ሞክረዋል፡፡ “ብርቱ” የሚል ድጋፍም ለመምህራን እንደተሰጠ በመቁጠር ነበር የተናገሩት፡፡ ይሄ ግን ዜጎችን በፍርሃት ቆፈን ማሸማቀቅ ነው፡፡ ህገ መንግስቱ ለዜጎች ያጎናፀፈውን ዴሞክራሲያዊ መብቶች በአደባባይ የመጣስ ያህል ነው፡፡ ዜጎች በደላቸውን ለመግለፅ በሞከሩ ቁጥር እያንዳንዷን ርምጃ ከአሸባሪ ቡድኖች ጋር ማያዝ ከየትኛው ዓለም የተኮረጀ አካሄድ ነው? ከየትኛው የፖለቲካ ፍልስፍና ዘርፍስ ይመደባል? ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ? ከልማታዊ መንግስት? ወይስ ከነጭ ካፒታሊዝም? ገና ለገና ኢህአዴግን የሚቃወሙ የውጭም ሆነ የአገር ውስጥ ድርጅቶችና ፓርቲዎች አንድን ክስተት ለማራገብ ቀዳዳ እንዳያገኙ በሚል ዜጎች ህገ መንግስታዊ መብታቸውን ተጠቅመው በሰላማዊ መንገድ እንዳይታገሉ ማደናቀፍና በፍርሃት ማሸማቀቅ ፍጹም የሆነ ኢ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ነው፡፡ መምህራን ብጥብጥን የሚናፍቁ ዜጎች አይደሉም፡፡ አርቀው የሚያሰቡ ምሁራን ናቸው፡፡ ሰውን ያህል ፍጡር ከዕውቀት መስከ ዳግም የሚፈጥር እንጂ በሽብርተኝነት የሚፈረጅ አይደለም፡፡

ስህተት ሦስት፡- ከመንግስት የተሰጠው ማብራሪያ ውስንነት ነበረው፡፡ ይህ አባባል ከተሰጠው መግለጫ ክብደት አንፃር የሚኒስትር ዲኤታዎች የአደባባይ ስህተት ለመሸፈን እንደሞከረ ይቆጠራል፡፡ አቶ መለስ ሊያስተውሉ የሚገባቸውን ቁጣውን የቀሰቀሰው ከርከን ማሻሻያው ገንዘብ ማነስ ይበልጥ በብዙሃን መገናኛዎች በተለይም በኢቴቪ የተሰጠው መግለጫ ነው፡፡

- የመምህራንን ኑሮ ሙሉ በሙሉ የሚቀይር
- የሙያውን ክብር የሚመልስ
- የመምህራንን ፍልሰት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚያስቆም

የተከበሩ አቶ መለስ እርስዎ እንደተናገሩት የሃ እና የሠላሳ ብር ጭማሪ ይህን ያህል ግነት ያስፈልገው ነበር ወይ? እርስዎ የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ በፓርላማ በተነሳ ቁጥር “በኑሮ ውድነቱ ላይ ደመወዝ መጨመር በእሳት ላይ ቤንዚን እንደመጨመር ነው፡፡ ይልቅ ወሳኙ ነገር የገበያውን ዋጋ ለማረጋጋት መሥራት ነው” እያሉ ይነግሩን አልነበረም እንዴ? የመምህራን የርከን ማሻሻያ ይህን ያህል ተጋኖ መነገሩ በኑሮ ውድነቱ ላይ ውሃ የሚቸልስበት?

ስህተት አራት፡- ህዝቡ ብቃትና ፍላጎት የሌላቸውን መምህራን እንድናስወግድ የነገረንን መስማት ነበረብን፡፡ ይሄ ትልቁ ስህተት ነው፡፡ በአዲስ አበባ ዙሪያ በየት/ቤቱ ከተሰበሰቡ ወላጆችም ሆኑ ተማሪዎች እንዲህ አይነቱ ሀሳብ አልተሰነዘረም፡፡ በነገራችን ላይ ብቃት የለውም የተባለውን መምህር ያፈራው ማን ነው? ለምንስ ብቃት አነሰው? እውነት ብቃት የለውምን? ብቃት እንደሌለው እየታወቀ ዩኒቨርሲቲው “ከነ ሙሉ ክብሩና ከነሙሉ ጥቅሙ ጋር . . . “ በሚል ዐ.ነገር እንዴት ሰርተፍኬት ሰጠው? ለነዚህ ጥያቄዎች ፀሐፊው ለጊዜው መልስ የለውም፡፡ ግን ይሄ አባባል ለኢትዮጵያ መምህራን ትልቅ ስብራት ነው፡፡ በርግጥ ኢህአዴግ ለትምህርት መስፋፋት የሰጠው ትኩረት በብርቱ ያስመሰግነዋል፤ ያሸልመዋልም፡፡ እውነት ነው በመላው አገሪቱ የተገነቡት ግዙፍ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች ተማሪዎችን ተቀብለው የማስተናገድ አቅማቸው በእጥፍ ጨምሯል፡፡ ግና ምን ዋጋ አለው? ምሩቃኑ በአቅም ማጣት ርጉማን ከሆኑ ልፋቱ ሁሉ ከንቱ ነው፡፡ የአገሪቱም ገንዘብ ሜዳ ላይ እንደፈሰሰ ይቆጠራል፡፡

ሌላው ፍላጐትን የተመለከተው ጉዳይ ነው፡፡ እውነት ለመናገር ዛሬ ወደ ከፍተኛ የት/ት ተቋም የሚገቡ ተማሪዎች መምህር የመሆን ፍላጐት እንዳላቸው ሲጠየቁ እንዴት እንደሚያንገሸግሻቸው ሲናገሩ ይደመጣል፡፡ በርግጠኝነት 5 ፐርሰንት እንኳን ወደ ሞያው የሚሰማራ ወጣት ማግኘት የሚያስቸግር ይመስላል፡፡ ከምክንያቶቻቸው ዋነኞዎቹ የመምህራን ጎስቋላ ኑሮ፣ የደመወዙ አነስተኛ መሆን፣ ዘወትር የተለያየ ባህሪን ከተላበሱ ተማሪዎች ጋር መነታረክ ለሥራው የሚደረገው ዝግጅት አድካሚነት . . . ወዘተ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ያለ ፍላጎቱ ሥራ ይዞ ህይወትን ለማኖር ወደ ሞያው ለመግባት የሚገደደውን የወጣት ኃይል ዩኒቨርስቲዎችን ያውቁታል፡፡

በሌላ በኩል ተማሪዎች ዩኒቨርስቲ ሲገቡ ካስመዘገቡት ውጤት አንፃር በየደረጃው ሲደለደሉ ወደ መምህርነት ሞያ እንዲሰማሩ የሚገደዱት አነስተኛ ነጥብ ያላቸው ናቸው፡፡ ከፍተኛ ነጥብ ያላቸው ወደ ህክምናውና ምህንድስና ሞያ ይመደባሉ፡፡ የነገውን ሀኪምና መሀንዲስ ለማፍራት ግን የዛሬው መምህር ብቃት ወሣኝ እንደሆነ ከአቶ መለስ በላይ የሚረዳ ያለ አይመስለኝም፡፡

ሌላው በጣም አስገራሚው ጉዳይ አንድ መ/ር ብቃትና ፍላጐት ይኑረው አይኑረው ወላጆች በምን መስፈርት አወቁት? ሁሉም የተማሪ ወላጅ የትምህርት ኤክስፐርት (ባለሞያ) ተደርጎ ከተወሰደ አስገራሚ ነው፡፡ አይደለም በየክልሉ ከአዲስ አበባ ነዋሪ የተማሪ ወላጆች መሀከል ሰንቶቹ ናቸው ስለ ልጆቻቸው ትምህርት ተቆርቁረው ክትትል የሚያደርጉት? ምናልባት በጣት የሚቆጠሩትን ማግኘት ይቻላል፡፡ እነሱም የተማሩ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ ስንቱ ወላጅ ነው “ዛሬ ምን ተማርክ? ውጤትህ ምን ይመስላል? ለምን አታጠናም?” እያለ ልጆቹን የሚቆጣጠረው?

ክቡር ጠቅላይ ሚ/ር በእርስዎ አገላለፅ የአዲስ አበባ አስተዳደር የህዝቡን ድምፅ መስማት አልቻለም “. . . እነ እገሌ ልጆቻችንን በደንብ አያስተምሩልንምና የተሻሉ መምህራንን አምጡልን . . .” ሲል አስተዳደሩ ርምጃ ባለመወሰዱ ወቅሰዋል፡፡ ለህብረተሰቡ ጥያቄ (በርግጥ የወላጆች ጥያቄ መሆኑ የተደረገልዎትን ሪፖርት አምነው ከተቀበሉ) ምላሽ የሚሰጠው መምህራን በርከን ማስተካከያው ቅሬታቸውን በድምጽ አልባ ጫጫታ ባሰሙበት ሰሞን ነውን? ይሄ የበቀልን ዘገር እንደመስበቅ ይቆጠራል፡፡

ስህተት አምስት፡- መምህሩ በደመወዝ መጠኑ ባይረካም በርከን ማሻሻያው ረክቷል፡፡

ሲከፈለው የቆየው ደመወዝ ያላረካው በርከን ያገኘው ዝቅተኛው ብር 63.00 እና 142.00 ያረካዋል ማለት የሚቻል አይመስለኝም፡፡ ደመወዙና ርከኑ ልዩነት የላቸውም፡፡ በደመወዙ የተስተካከለው ርከን የደመወዙ አንድ አካል ነውና፡፡ እርስዎ እንዳሉት የርከን ቢሆን እንኳን የሌላው መንግስት ሠራተኛ የርከን ጣሪያው 9 ደረጃ ሆኖ ሳለ የመምህሩን ከ6 ወደ 7 ደረጃ አሻሽሎ ረክቷል ማለት ግን አይቻልም፡፡

ከሁሉም በጣም የሚያስገርመው የርከን ማስተካከያውን በተመለከተ እስከአሁን ዝርዝር መመሪያ ተዘጋጅቶ አለመተላለፉ ለመምህራን እየተነገረ ባለበት ሰዓት ጠቅላይ ሚ/ሩ “መምህራን ተደስተዋል” ማለታቸው ነው፡፡ በጋዜጣዊ መግለጫው የተበሳጩ መምህራንን በየት/ቤቱ ተገኝተው ለማወያየት የሞከሩ የአዲስ አበባ መስተዳድር ሹመኞች “የአፈፃፀም ዝርዝር መመሪያው እስኪወጣ ታገሱ” የሚል የማረገጊያ ሀሳብ በመሰንዘራቸው መምህራን ይህን እየጠበቁ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በዘለለ ተደረገ ከተባለው የርከን ማስተካከያ ጭማሪ መምህራን ሰባራ ሳንቲም አልደረሳቸውም፡፡ አቶ መለስ ግን መምህሩ 20ም ትሁን 30 ብር የተባለችውን ኪሱ ሳይከት ቅስም የሚሰብር ንግግር ማድረጋቸው አሳዛኝ ነው፡፡ ሕዝብን በፍቅር እንጂ በማስፈራራትና በዛቻ ማስተዳደር ከቶም አይቻልም፡፡ አቶ መለስ ንግግር ባደረጉ ቁጥር ከአንደበታቸው የሚወረውሯቸው ቃላት የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚጋፉ የሰዎችን ክብር የሚጎዱ መሆኑን ቢያስተውሉ ይበጃል፡፡

ፈጣሪ የሳምንት ሰው ይበለን! አሜን!

የተከበሩ አቶ መለስ እርስዎ እንደተናገሩት የሃ እና የሠላሳ ብር ጭማሪ ይህን ያህል ግነት ያስፈልገው ነበር ወይ? እርስዎ የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ በፓርላማ በተነሳ ቁጥር “በኑሮ ውድነቱ ላይ ደመወዝ መጨመር በእሳት ላይ ቤንዚን እንደመጨመር ነው። ይልቅ ወሳኙ ነገር የገበያውን ዋጋ ለማረጋጋት መሥራት ነው” እያሉ ይነግሩን አልነበረም እንዴ? የመምህራን የርከን ማሻሻያ ይህን ያህል ተጋኖ መነገሩ በኑሮ ውድነቱ ላይ ውሃ የሚቸልስበት?

# ይህቺ ሀገር የሚያስፈልጓት ግን የሌሏት

የኢትዮጵያ ፖለቲካ የአደባባይ ምሁራን ጠኔ እንደመታው እየተነገረ ነው፡፡ ከ1960ዎቹ ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ የተለያዩ አስገራሚ ተናጋሪዎች ብቅ ብቅ ብለው የጠፉበት ‹የኢትዮጵያ አደባባይ› በዘመነ ኢ.ህአዴግ ደግሞ ከ1997 ጀምሮ ምሁራን ከአደባባይ መጥፋታቸው እያነጋገረ ነው፡፡ የሆኖ ሆኖ የምሁራን መጥፋት የወጣቱን ትውልድ በተለያዩ ሱሶች መያዝና፣ በኢ.ህአዴግ አድርባይነት መንደፍና ፍርሃት ማባባሱ እየተገለፀ ነዉ፡፡ በዚህ የጠኔ ዘመን ንግግር በማድረግ አንድ ለናቱ ሆነው እየወጡ ያሉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲው ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ጃለታ ሲሆኑ በ14/08/04 ዓ.ም አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ተገኝተው በዋነኝነት "ወጣትነትና የሀገር ፍቅር" ላይ ያደረጉትን ንግግር ሰለሞን ስዩም እንሚከተለዉ አጠናቅሮታል፡፡

ዶ/ር ዳኛቸው ንግግራቸው ከርዕሱ በመወጣት በሦስት ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ሂስ በመስጠት ጀመሩ፡፡ ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ ሚያዚያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተገኝተው በሀይማኖታዊ ንቅናቄ ላይ በሰጡት ማብራሪያ ማህበረ ቅዱሳን አካባቢ "አንድ ሀገር አንድ ኃይማኖት" የሚሉ መኖራቸውን ብለዉ መተቸታቸው ኢ.ህአዴግ "አንድ ሀገር አንድ አይዲዮሎጂ" ባይል እንደነበር አንስተዋል፡፡ የኢትየጵያ ህዝብ "ሀገር የጋራ ኃይማኖት የግል ነው" ማለት የጀመረው ድሮ መሆኑን ያወሱት ዶ/ር ዳኛቸው "አንድ ሀገር አንድ ኃይማኖት" ማለት ከህገ መንግሥቱ ይፃረራል ማለት ሰውን መግደል በራሱ ችግር ኖሮት ሳይሆን ህጉ ስለማይፈቅድ ነው እንደማለት ነው" በማለት አቃርነዋል፡፡ በመጨረሻም ቀድሞም ኢ.ህአዴግ "በኃይማኖት ጉዳይ ቸር የሆነው በስልጣኑ የማይመጣ ስለመሰለው እንጂ ለስልጣኑ የሚያሰጋ ከሆነማ እጁን ከመስደድ አይታቀብም" ነበር ብለዋል፡፡

በመቀጠል ከደቡብ ኢትዮጵያ ስለተፈናቀሉት የአማሪኛ ተናጋሪዎች ያወሱት ምሁሩ አሜሪካውያን "illegal aliens" (ህገወጥ መጤዎች) የሚሏቸው አሉ፡፡ እነዚህ ከውጭ ሀገር በህገ ወጥ በመምጣታቸው በዚያ ቦታ መገኘታቸው ብቻውን ወንጀል ነው፡፡ ነገር ግን አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ሽጉጥ እንደያዘ የኢሚግሬሽን መኮንን "ህገ ወጥ ሰፋሪዎች በመሆናቸው ወደ ሀገራቸው ይሂዱ (ይጠረዙ /deport) ማለቱ ገርሞኛል" ይላሉ፡፡ "እንዴት በራሳቸው ሀገር እዚያ መገኘታቸው ወንጀለኞች ያደርጋቸዋል" ያሉት "ለዚህ ሁሉ ያበቃን የህገ መንግሥቱ አንቀፅ ሳይሆን የህገ መንግሥቱ ቀልብ ነው" ብለዋል፡፡ የህገ መንግሥት ቀልብ ማለት የሚያጠነጥንበት ጊዜው/focus) ሲሆን በኛ ህገ መንግሥት "ብሔር ብሔረሰቦች" የሚለው ጠርዝ የያዘ የክልሎች ሁኔታ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በሦስተኝነት ያነሱት የመምህራኑ ጉዳይ ሲሆን የአቶ መለስን "modus Operandi" በመተንተን ነበር የጀመሩት፡፡ ባድመ ተዋግተን አሸነፍን፡፡ በህግ ፊት ግን ተሸነፍን፡፡ ነገር ግን ባድመ ተፈርዶልናል ከተባለ በኋላ አቶ መለስ ነገሩን መቀየር ነበረባቸው፡፡ ነገር ግን ተሸንፈናል ከማለት "እኛ የተዋጋነው ሻዕቢያን ወደ ህግ ፊት ለማምጣት ነው" ማለት የአቶ መለስ ዘዴ ነበረች፡፡ "ይህ ማለት" ይላሉ ዶ/ር ዳኛቸው "ዘነበችን ስትወድ ኖረህ በመጨረሻ እምቢ ስትልህ ከበደችን ወስደህ እኔ ድሮም ሰው ዘነበች አለ እንጂ ከበደችን ነበር እምወደው እንደማለት ነው" ብለዋል፡፡ ኢ.ህአዴግ ያልተሳኩ ፖሊሲዎች ሲገጥሙትም ሁሌ "አቀራረቡ ስህተት ስለነበር አልተረዳችሁትም እንጂ እውነታው ይህ ነው" በማለት ማስቀየስ እንደሚወድ ገልፀዋል፡፡ ዛሬ ደሞዝ ሲጠይቁ "ድሮም እኮ ጥሩ አልነበሩም፤ መባረር ነበረባቸው ማለት ቢያንስ ከጨዋ አይጠበቅም" ያሉት ምሁሩ "ዋናው የአቶ መለስ ክህሎት የደመወዝ እርከን ተደርጎ ተቃውሞ በመነሳቱ አልገባችሁም እንጂ የደሞዝ ጭማሪ ሳይሆን የእርከን ማስተካከያ ነው ያደረግነው ብሎ መንሸራተተ መሆኑን ይፋ አድርገዋል፡፡

## "እውነት ማለት የኔ ልጅ"

ወደ ዋና ርዕሳቸው የገቡት በዚህ ንዑስ ርዕስ ነበር፡፡ በወቅቱ የዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ ግጥም በዶ/ር ዳኛቸው ለማጣቀሻነት የተነበበ ሲሆን ፕላቶ metastrophy ከሚሉት ቃል ጋር ትሄዳለች ብለዋል፡፡ ፕላቶ "we convert the known in to unknown" ማለቱን አውስተው የምናየውንና የምንሰማውን አዙረን ማስተዋል እንዳለብን ተናግረዋል፡፡ ዶ/ር ዳኛቸው ይህን ያሉበት የራሱን ሀሳብ ብቻ ፈልገን በመፈለጉ ይመስላል፡፡ በመሆኑም መስማት ችግር እንደሌለው የሰሙትን ሁሉ ማመን ግን ሞት መሆኑን በአንክሮ ተናግረዋል፡፡ በሌላ በኩል ማኪያቬሊ ብሔርተኝነት (Nationatism) ፀጋ (vertve) ቢሆንም በመውሰድ ሳይሆን በመለማመድ /በመማር የሚገኝ መሆኑን መናገሩን ጠቅሰዋል፡፡ በዶ/ር ዳኛቸው እይታ የአሁኑ ወጣት ሀገራዊ ፍቅሩ የቀዘቀዘው የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግስትና የደርግ መንግሥት የኢትዮጵያ ሀገርንም (state) የኢትዮጵያ መንግሥትንም (gov't) የሚወዱ ቢሆንም የአሁኑን ግን መንግሥትን የሚወድ ሀገርን ግን የሚጠላ ቡድን ስልጣን በመያዙ ወጣቱ ምንም መማር እንደማይችል ነው፡፡ ለምሳሌ ሲያስረዱ በስልጣኑ በመምጣቱ ለባድመ 70 ሺህ ህይወት ለአሰብ ግን ምንም ያለመገበራችን ጥቅም ለሀገር በመሆኑ እንደሆነ አሳይተዋል፡፡ "መንግሥት የሚወደው ኢ.ህአዴግ ችግሩ ከኤርትራ መንግሥት ጋር ብቻ መሆኑን ሲናገር እኛ ሀገር ወዳዶች ግን ችግራችን አሰብን ከወሰደብን ሀገር ጋር ነው" ሲሉም አነፃፅረዋል፡፡

በጫት በቅጠል ተሸንፏል፡፡ የኢትዮጵያ "body politic" ወጣቱ ሆኖ ሳለ በጫት መክቷል" ካሉ በኋላ ስርዓቱ የባንዲራ ቀን ለማክበር ሲነሳ አንድም ባንድራዋን የኖሯትን አባቶች ሳያስብ በእንቶ ፈንቶ ይጨርሰዋል" ብለዋል፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ስለ ኦህዴድ ያነሱት ዶ/ር ዳኛቸው በባንድራ ቀን ስንት የአድዋ ጀግኖች እያሉ ሀገሪቱን በሚያከል ማህበራዊ ሽፍታ (social bandit) ቀኑን መሞከራቸው "የሰው ልጅ ከመወለዱ በፊት ያለውን ታሪክ ካላወቀ እድሜ ልኩን ህፃን ሆኖ ይኖራል የሚለውን ተረት ያስታውሰኛል" ሲሉ ተሳልቀዋል፡፡

## መሪ ወይስ ‹‹ስልጣን››

አብዛኞቹ ዴሞክራሲ ሀገራት ከመሪ አገዛዝ ወደ ተቋማዊ ባለስልጣን (Authority) አገዛዝ መሄዳቸው ይታወቃል፡፡ ባለፉት 20 ዓመታት ኢትዮጵያ ግን መሪ በመፍጠር መጠመዷ ታይቷል፡፡ በሩሲያ ኮምኒስት ፓርቲ አንዱ የሀሊዮት ሰው የስታሊን ሁኔታ ሳያምረው ሲቀር "መሪ መፍጠር የለብንም፤ ስልጣን ነው መገንባት ያለብን" ሲል አንገቱ ተቀላ፡፡ በኢትዮጵያም አቶ መለስ በመሪነት ሲፈጠሩ ፓርቲዋም ጭምር ስለዛ እንደነበረች ዶ/ር ዳኛቸው ያስረዳሉ፡፡ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ በመጀመሪያዎቹ 10 ዓመታት ከሕዝብ የመለየት ስራ ሠራ፤ በቀጣዮቹ 10 ዓመታት ፓርቲውን ሰበረ፣ በሦስተኛው መለስን ለዚህ አበቃ" የሚሉት ዶ/ር "ታምራት ላይኔን አውርጃለሁ፣ አዲሱ ለገሰን ደግሞ ሾሜያለሁ ብሎ ቤቱ ሲገባ ሁሉ ነገር ገብቶኝ ነበር" ይላሉ፡፡ "አፄ ኃይለ ሥላሴ በፊውዳል ም/ቤታቸው ይህንን አይችሉም፤ ስንት ነገር ውድቅ ሆኖባቸዋል፤ ኢቴቪ ተመለከቱ ሚኒስትሮች ቀርበው ትንሽ ያወራሉ፤ ጋዜጠኛው ተወካዮች በአስፈፃሚው ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር መሆናቸውን አማረዋል፡፡

የአፄ ኃይለ ሥላሴን ዘመን ለማነፃፀሪያ ያነሱት ምሁሩ ካባ የለበሱ ደጃዝማች ሚኒስቴሮቹን "ሂድና ለንጉሱ ንገራቸው፤ በምንም ድጋፍ አልሰጠውም" እስከ ማለት ይቃወሙ እንደነበር አንስተው ተጨማሪ የፈለገ የፊት አውራሪ አመዴ ለማን የህይወት ታሪክ እንኳ ቢያነብ ስለዚህ ብዙ እንደሚረዳ አሳስበዋል፡፡ የኢ.ህአዴግ ጣልቃገብነትን ሲያወሱ ድሮ እንደ ተከበረ አምባ የሚቆጠረው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አሁን መደፈሩን ገልፀው "እነ ጁነዲን በየስድስት ወሩ እየመጡ ለምን ፕሬዚዴንቱን ከጀርባ እንደሚተነፍሱበት ሊገባኝ አልቻለም" ብለዋል፡፡ በመጨረሻም የዩኒቨርሲቲውን፣ የቤተክርስቲያኑንና የመስጂዱን መደፈር አንስተው "ይህ ሁሉ አሁን ኢትዮጵያ "የመሪ ሀገር (leader state) መሆኑ ነው" ሲሉ ገልፀዋል፡፡

የመረጃ ክፍተት (information vacum)

የመሪ ሀገር መርህ የመገናኛ ብዙሃኑን መቆጣጠር ነው፡፡ ሌላ ሀሳብ እንዳይደመጥ አፍኖ በክፍተቱ መጠቀም ነው፡፡ አንድ ሰዓሊ የመጀመሪያ ስራው ካንቫሱን (ነጭ ቀልም በመቀባት ከተለያዩ ቀለማትና አባጣ ጎርባጣ ነፃ ማድረግ ነው፡፡) መንግሥትም ይህንኑ እያደረገ መሆኑን ያወሱት ዶ/ር ዳኛቸው "ከንግዲህ ፍትህና ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን በማጥፋት አሊያም ጋዜጠኞቹን ወደ ወህኒ በመከተት የራሱን ብቸኛ ሀሳብ ለማድረግ ይጥራል" ይላሉ፡፡

ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ የመፍትሄ ሀሳቦችን አስቀምጠዋል፡፡ አንደኛ ያሉት በሀሳብ መሻገር (የሀሳብ የበላይነት) መሆኑን አምነው የኢ.ህአዴግ ሀሳብ የሚገዳደር ንግግሮች (counter speeches) የግድ እንደሚሉ አፅንኦት ሰጥተዋል፡፡ ምሳሌ ያረጉት "መሬት ላራሹ" የሚለው መፈክር ከወቅቱ የስርዓቱ አስተሳሰብ አልፎ የሄደ ስለነበር ማሸነፉን ነው፡፡ ነገር ግን "ጋዜጦችን መታገስ ያልቻለ መንግሥት ሬዲዮማ በዕድሜ አላስብም" በማለት ተናግረዋል፡፡ ሌላው መፍትሄ ያሉት አቅጣጫ ማግኘት ሲሆን "የጠራ አቋም ይዞ ግብ ስለመንደፍ የሚናገር ሀሳብ ነበር›› ብለዋል፡፡

በንግግሮች መመሠጥ ቀላል ስራ እየሆነላቸው የመጡት ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ የአንድ ሀገር ዴሞክራሲ ለማበብ ምን ይጠይቅ እንደሆነ ተጠይቀው ሲመልሱ "ፈረንጆች ነፃነት በመፈለግ አይበልጡንም፤ ዴሞክራሲ የሚሰርፅበትን ተቋማት በመገንባት ግን በልጠዉናል" ያሉ ሲሆን "በኢትዮጵያ ግን ተቋማቱ የመንግሥት ፎቶ ኮፒ ናቸው" ብለዋል፡፡ ሌላው ነገር ስልጣን ላይ ያለው ቡድን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር ያለው ተነሳሽነት መሆኑን አውስተው ስልጣኑን ለመልቀቅ ፍላጎት ከሌለው "ዴሞክራሲ 400 ሺህ ወታደሮች ከሌሏት መሸነፏ ግድ ነው" ካሉ በኋላ ይህ የአለም ታሪክ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

**ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ የመፍትሄ ሀሳቦችን አስቀምጠዋል፡፡ አንደኛ ያሉት በሀሳብ መሻገር (የሀሳብ የበላይነት) መሆኑን አምነው የኢ.ህአዴግ ሀሳብ የሚገዳደር ንግግሮች (counter speeches) የግድ እንደሚሉ አፅንኦት ሰጥተዋል፡፡ ምሳሌ ያረጉት "መሬት ላራሹ" የሚለው መፈክር ከወቅቱ የስርዓቱ አስተሳሰብ አልፎ የሄደ ስለነበር ማሸነፉን ነው፡፡ ነገር ግን "ጋዜጦችን መታገስ ያልቻለ መንግሥት ሬዲዮማ በዕድሜ አላስብም" በማለት ተናግረዋል፡፡ ሌላው መፍትሄ ያሉት አቅጣጫ ማግኘት ሲሆን "የጠራ አቋም ይዞ ግብ ስለመንደፍ የሚናገር ሀሳብ ነበር> > ብለዋል፡፡**

የኢ.ህአዴግን ስጋት ሲገልፁ "ኢትዮጵያ ጥንታዊት ሀገር (ancient polity) በመሆኗ ህዝቧ ያለ መንግሥት የመኖር ባህሉ ስር የሰደደ መሆኑን ገልፀው ዛሬ የጥንቷ ኢትዮጵያ ከኢትዮጵያውያን ቀርቶ ከመረብ ማዶም ሊፋቅ ያለመቻሉን ምሳሌ በመጥቀስ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ ዶ/ሩ አንድ ኤርትራዊ ጓደኛቸው ከአስመራ ውጭ አንዳንድ ሰዎች የኢትዮጵያን ባንድራ ደብቀው መያዛቸውን አይቶ እንደነገራቸው በማቅረብ የኢ.ህአዴግን የሀገር ጠንቅነት ተንትነዋል፡፡ ዶ/ሩ ክልላዊነት ለተጠናወተው ኢ.ህአዴግ "ከደቡብ የተባረሩት ሰዎች እንደ መንግሥት ትክልል ነው፤ እንደ ሀገር ግን ፍፁም ወንጀል ነው" ሲሉ አነጻፅረዋል፡፡

የዘመኔ ወጣት የለዉጥ ማዕከል ነበር፡፡ የአሁኑ ብዙ ያወራል፤ መለስ ከሆኑ ሲጠግቡ ካላቆሙ ማንም ጣልቃ አይገባባቸውም፡፡" ይላሉ፡፡

የህግ የበላይነት ወይስ የህግ አውጭ የበላይነት?

በአብዛኞቹ ሀገራት ሲሰለጥኑ ከሰዎች አስተዳደር ወደ ህግ አስተዳደር ይመጣሉ፡፡ ኢትዮጵያ ግን ለህግ አስተዳደር የተጠጋችበት ጊዜ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ መሆኑን በብሽቀት መንፈስ ይናገራሉ፡፡ አሁን ግን የህግ አውጭው የበላይነት /አስተዳደር (rule of legislature) በመስፈኑ የሰዎች አስተዳደር (rule of men) በጓሮ በር ሰተት ብሎ መግባቱን እንደሚያመለክት አብራርተዋል፡፡ "አቶ መለስ ለፓርላማ ልከው ያላለፈላቸው ረቂቅ ባለፉት 20 ዓመታት አልታየም" ያሉት ምሁሩ አብዛኞቹ

አደገኛ አምባገነን

በአምባገነኖች ያለ ህገ መንግስት ራሱን እንኳ የማይከላከል ካለመሆኑም በላይ ተደጋግሞ የተነበበ ወረቀት ከመሆን እንደማይዘል ገልፀዋል፡፡ የብሔር ብሔረሰብ እኩልነትም አብሮ ለመኖር ዋስትና እንደማይሆን አርስቶትል ጭምር መናገሩን ያወሱት ዶ/ር መጨመር ያለበት ግብዓት እንዳለ አሳስበዋል፡፡ አማኑኤል ካንት መንግሥት ራሱን አዋቂ፣ ህዝቡን ቂል አርጎ ሲያስብ "ለናንተ ስል ነፃነታችሁን ይዣለሁ" ከሚለው ጋር ኢ.ህአዴግ አንድ ነዉ ብለዋል፡፡ በሌላ በኩል ፈረንጆች "free & fair" ምርጫ የሚሉት በምርጫው ቀን ብቻ የሚደረገውን ሁኔታ ብቻ እንደማይወስን ያወቀው ኢ.ህአዴግ ካሁኑ "የንፅህናው" መረጃ የሚሆኑ ቪዲዮ ለመሰብሰብ መልካቸውና ሀሳባቸው ከማያምሩት ጋር ክርክር ቢጤ መጀመሩን አውስተዋል፡፡




አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)

የገቢ ማሰባሰቢያ የራት ፕሮጋራም

አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ለማድረግ በቁርጠኝነት እየታገለ ይገኛል፡፡ ለትግሉ ስኬት የእርስዎ ድጋፍ ወሳኝ ነው፡፡

የአንድነት ፓርቲ የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ የራት ዝግጅት ፕሮጋራም አዘጋጅቷል፡፡ ለመግብያ ባለ 1,000፣ 500ና 300 ብር መግቢያ ካርዶች ተዘጋጅተዋል፡፡

በራት ፕሮግራሙ ላይ ታዋቂ ግለሰቦች ንግግር ያደርጋሉ፡፡ የእራት ግብዥው ግንቦት 24 ቀን፣ 2004 ዓ.ም. ይደረጋል። የሆቴሉ ስም ግንቦት 13 ቀን 2004 ዓ.ም. በሚወጣው ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ላይ ይገለፃል፡፡

በውጭ ሀገር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያኖች በሀገር ውስጥ በሚኖሩ ቤተሰቦችና ጓደኞች አማካኝነት ካርዱን መግዛት ትችላላችሁ፡፡

ለተጨማሪ መረጃና ካርድ ለመግዛት በሚከተለው አድራሻ ይጠቀሙ፤
በቢሮ ስልክ ቁጥር 011-840-08-11
በተንቀሳቃሽ ስልክ 091-161-84-34
ኢ-ሜል፡
andientfinance@yahoo.com
ወይም andinet@andinet.org

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
የሂሳብ ቁጥር፡ 510
ንብ ባንክ ዑራኤል ቅርንጫፍ

ለዴሞክራሲ ስርዓትና ለህግ የበላይነት መመስረት፣ ሁላችንም ካርዱን በመግዛት ድርሻችንን እንወጣ!

# በአፍሪካ የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ የተደረገው ምክክር ተጠናቀቀ

በዓለማችን አሳሳቢ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል የከባቢ አየር ብክለት እያሳደረ ያለው ተፅዕኖ አነጋጋሪ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በተለይ ካደጉ ሀገሮች ወደ ከባቢ አየር የሚደረገው የካርቦን ልቀት በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ላይም ከፍተኛ ተፅዕኖ በመፍጠሩ የአፍሪካ ካርበን ፎረም የአህጉሪቱን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚል ለ3 ጊዜ ያህል በተለያዩ ሀገሮች መክረዋል፡፡

የአራተኛው የአፍሪካ ካርበን ፎረም በኢትዮጵያ እንዲዘጋጅ ከተወሰነ በኋላ አዲስ አበባ በሚገኘው የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን አዳራሽ ከሚያዝያ 10-12 ቀን 2004 ዓ.ም ዓለም አቀፍ ጉባኤ ተካሂዷል፡፡ በጉባዔው ላይም የአፍሪካንና የተባበሩት መንግስታትን ጨምሮ ከተለያዩ የዓለማችን ሀገሮች የመጡ ምሁራን ተገኝተው ከሚመለከታቸው ጋር መክረዋል፡፡

ለ3 ቀናት በቆየው ምክክርም አፍሪካን ከባቢ አየር ብክለት ለመታደግ ሀገሮቹ ከካርበን ልቀት ነፃ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ማበረታታትና ማገዝ እንዲሁም የአረንጓዴው መድረክን መፍጠር እንደሚያስፈልግም ተጠቁሟል፡፡ ይህንንም ለማገዝ ቃል የገቡ ያደጉ ሀገሮችም የገቡትን ቃል በአግባቡ እንዳልፈፀሙና አሁንም ቢሆን መፈፀም እንዳለባቸው በውይይቱ ላይ ስምምነት ተደርሶ የጉባዔው ምክክር ተጠናቋል፡፡

# በኦሮሚያና . . .

ከገፅ 1 የዞረ

የአካባቢው ነዋሪዎች አክለውም “ አካባቢው ሠላም እንዳይሆን ህብረተሰቡም ተግባብቶና ተዛዝኖ እንዳይኖር የኢህአዴግ ካድሬዎችና የደህንነት አካላት በየጐሳቸው ግጭት እንዲፈጠር ካነሳሱ በኋላ ከወስጥ ይወጣሉ፡፡” ካሉ በኋላ “ለተፈጠረው ግጭት፣ ለጠፋው ህይወትና ለወደመው ንብረት ተጠያቂዎቹ የአካባቢው ኃላፊዎችና ሥርዓቱ ነው፡፡” ብለዋል፡፡

ምንጮች አያይዘውም ሲገልጹ “በአሁኑ ወቅት አካባቢው በከፍተኛ ጥበቃ ውስጥ ይገኛል፡፡ ጉዳዩ ወደ ወጪ እንዳይወጣ ተብሎ ማንም ሰው ወደዚህ አካባቢ እንዲገባ አይፈቀድም፡፡ የችግሩ ፈጣሪዎች የማይመለከታቸውን ሰዎች ተጠያቂ ለማድረግ እና ራሳቸውን ከተጠያቂነት ለማዳን እየተሯሯጡ ይገኛሉ፡፡ እጃቸው በጉዳዩ ውስጥ የሌሉ የመንግሥት ኃለፊዎች ጉዳዩ በገለልተኛ አካል ተጣርቶ አጥፊዎቹ ለህግ እንዲቀርቡ እንዲደረግልን በአካባቢው በተደጋጋሚ የሚከሰተው ግጭት የመጨረሻ እልባት ያገኝ ዘንድ የሁለቱ ክልል መንግሥታትና የፌዴራሉ መንግሥትም ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሰራ ጥሪያችንን አቅርቡልን፡፡” በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ለአካባቢው ኃላፊዎችና ለፌዴራል ጉዳዮች በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት ያደረግነው ጥረት ለጊዜው አልተሳካም፡፡

# በጋሞ ጐፋ ዞን . . .

ከገፅ 1 የዞረ

ያሰባሰብናቸው መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ህዝቡ ማንነቱ እንዲታወቅለት ያቀረበው ጥያቄ ከክልል፣ ከዞንና ከወረዳ በመጡ ኃላፊዎች “መሎ” የሚባል ብሔር የለም የሚል ውሳኔ በመወሰኑ ህዝቡ ተቋውሞውን በሰላማዊ መንገድ ገልፃል፡፡ ሆኖም የአካባቢው ታጣቂዎች ለተቃውሞ በወጣው ህዝብ ላይ ተኩስ በመክፈታቸው ከህዝቡ መካከል ሁለት ሰዎች ተገድለዋል፡፡

የአካባቢው ምንጮችም በሰጡት አስተያየት ህዝቡ በሰላማዊ መንገድ ባቀረበው ተቃውሞ ላይ ተኩስ ከፍተው ግድያ የፈፀሙት አካላት በቁጥጥር ስር ውለው ህጋዊ እርምጃ ካልተወሰደ የሟቾችን አስክሬን ላለመቀበል በመወሰኑ ከሦስት ቀን ላላነሰ አስክሬኖቹ በጤና ጣቢያ እንደተቀመጡ አስረድተዋል፡፡ አክለውም ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የወረዳው የፖሊስ አዛዥ እና አንድ ሌላ ታጣቂ በግድያው ተጠርጥረው መያዛቸውን ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም የአካባቢው ህዝብ የማዳበሪያ እዳ በአንድ ጊዜ እንዲከፍል እንዲሁም ተጨማሪ ማዳበሪያም በግዳጅ እንዲገዛ በአካባቢው አስተዳደር እና በፖሊስ መገደዱን በመቃወም “የካድሬዎች መግቢያ” ያላቸውን ዋና ዋና የመኪና መግቢያ መንገዶች በመዝጋት ተቃውሞውን የገለፀ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት አካባቢው በፀጥታ ኃይሎችና ደህንነቶች መከበቡን ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡

በደቡብ ክልል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በማዳበሪያ ዕዳ ምክንያት በሚወሰዱ እርምጃዎች መንስኤ በርካታ ዜጐች ህይወታቸውን ማጣታቸውንና መሰወራቸውን አቶ ዳንኤል ሺበሺ አስታውሰዋል፡፡ ስለጉዳዩ ለማጣራት የዞኑ አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳይ መስሪያ ቤቶች ጋር ጥረት ብናደርግም ለጊዜው አልተሳካም፡፡